ፍኖተ
# ነፃነት
ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!
ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 52 | ዋጋው፡- 6 ብር


አቶ ጥላሁን እንደሻው

## እኛ የምንታገለው ለሥርዓት ለውጥ እንጂ ለግለሰብ አይደለም

6

## በቃሊቲ ወህኒ ቤት ድንገተኛ ፍተሻ ተደረገ

11

## ሁለት መቶ ኢትዮጵያውያን በኮንቴይነር ተጭነው ከሀገር ሊወጡ ሲሉ ተያዙ

11

## በተቃውሞ የተሳተፉ ሙስሊሞች በጅምላ እየታሰሩ ነው ተባለ

11




## የድህረ መለስ ዜናዊ ኢህአዴግ ምን መልክ ይኖረው ይሆን?

2

### አንድነት በወከባ ውስጥ ሆኖ በፈረንሳይ ለጋሲዮን ህዝባዊ ስብሰባ አደረገ

- ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበሩ አባላት በተከታታይ ቀናት ታግተው ነበር

13

### የሙስሊሙ ብስለት፣ የመንግስት ክስረት፣ የኢቲቪ ቅጥፈት

3

### እነ ናትናኤል መኮንን ወደ ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ተዛወሩ

-አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር ለብቻቸው ታሰሩ

15

### ከመንግሥት መረጃ የማግኘት መብት አለን!

4

### መድረክ ወደ ግንባር መሸጋገሩን አበሰረ

- ግንባሩ አዲስ የአመራር አባላት መርጧል

11

### ክቡር ሚኒስትር እባክዎትን በአይ.ሲ.ሲ ንስሀ ሣይገቡ እንዳያርፉ

7

### “በመጪው አርብ ጋዜጣችን ለአንባቢያን ትደርሳለች በሚል እምነት በመስራት ላይ ነን”

የፍትህ አዘጋጆች

11

### አቶ መለስ ሃኪም ይረፉ አላቸው ህዝቡ ግን “ይረፉ” ካለ ቆይቷል!

9

አቤ ቶክቻው

ዳሰሳ

**ኢህአዴግን በዘሬው መልኩ በመፍጠር ረገድ አቶ መለስ ዜናዊ የተጫወቱት ሚና ቀላል የማይባል ነው፡፡ አሁን የመለስ ዜናዊ ዘመን እያለፈ ይመስላል፤ ሰለሞን ስዩም የድህረ መለስ ዜናዊ ኢህአዴግ መልክ እና ሰላማዊ የስልጣን ሽግሽግ ውልውል ቢኖርበትም በርግጠኝነት ግን የዘመነ መለሱን ጥንካሬ አይዝም ይላል፡፡**

# የድህረ መለስ ዜናዊ ኢህአዴግ ምን መልክ ይኖረው ይሆን?



ሰለሞን ስዩም

## መለስ ብቻቸውን ኢህአዴግ ናቸው!

የኢህአዴግ መስራች ከሆኑት ፓርቲዎች የበላይ የሆነው ህወሓት በተለይም በጣምራ አመራር (collective leadership) ይታወቅ ነበር፡፡ ከ1971 ዓ.ም በፊት ሁለት ደረጃዎች ለነበሩት የህወሓት አመራር ሁለተኛው ረድፍ ላይ ተቀምጠው የነበሩት መለስ ዜናዊ በዓመቱ በተካሄደው የድርጅቱ ኮንግረስ ወደ መጀመሪያው ረድፍ አመራር መጡ፡፡ ከዚያ ቀደም የመጀመሪ ረድፍ የነበሩት አባይ ፀሐዬ፣ ስብሃት ነጋ፣ አረጋዊ በርሄ፣ ግደይ ዘርዓ ፅዮንና ስዩም መስፍን ነበሩ፡፡ መለስ ዜናዊ ወደነኚህ የመጀመሪያ ደረጃ አመራር የመጡበት ምክንያት በወቅቱ ኮንፍረንስ የተወሰነው ሶሻሊስት ፓርቲ የመመስረት ዕቅድ ነበር፡፡ ማዕከላዊ ኮሚቴው ይህን የሶሻሊስት ፓርቲ እንዲመሩ የሰየማቸው አቶ መለስ ዜናዊ ውሳኔው የጦር ሜዳ ውሎ ቀንሶላቸዋል፡፡ ቀጥሎም የካድሬ ት/ቤት ዋነኛ ተዋናይ፣ አንባቢና የሀሳብ አመንጪ ሆኑ፡፡

በ1977 ዓ.ም ማሌሊትን ለምስረታ ሲያበቁ ከድርጅቱ ሊቀ መንበር አቶ ዓባይ ፀሀዬ ቀጥለው ሁለተኛውን ደረጃ ያዙ፡፡ ሌላው የመለስ ዜናዊን ደረጃ ከፍ ያደረገው በምስረታው ወቅት ከግዳይ ዘርዓ ፅዮን ጋር የአይዲዮሎጂ ግጭት መፍጠራቸው ነበር፡፡ በወቅቱ የድርጅቱ ሊቀ መንበር ድጋፍ የተቸራቸው መለስ ዜናዊ ግደይን ካስባረሩ በኋላ እየገነኑ ወጡ፡፡ በ1983 ዓ.ም የመንግስት ስልጣን ሲይዙ የአቶ መለስ አስፈላጊነትና ከጣምራ አመራር መጥቆ የመውጣት አዝማሚያ ታየ፡፡ የፖለቲካ ተክለ ስብዕናቸውን ለመገንባት የተለያዩ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ የነበሩት አቶ መለስ የመጨረሻዎቹን ቋጥኞች ስልጣን በጨበጡ በ10 ዓመታት ውስጥ ከረበቷቸው፡፡ በ1993 ዓ.ም ህወሓትን ለሁለት የሰነጠቀው የውስጥ ግጭት የመለስ ዜናዊ ተቀናቃኞችን ያለ ፖለቲካ ስልጣን በተናቸው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መለስ ዜናዊ ማለት ኢህአዴግ፣ ኢህአዴግ ማለት መለስ ዜናዊ ሆኑ፡፡

ባለፉት 20 ዓመታት ኢህአዴግን ሲከታተሉ እንደቆዩ የሚናገሩት ዶ/ር ሙሉ አበራ ‹‹መለስ ራሱ ስርዓት (system) ሆኗል፡፡ መለስ ችግር ሲገጥመው ስርዓቱን ችግር ይገጥመዋል›› ይላሉ፡፡ አርባ አመት ሙሉ ፖለቲካ ያስተማሩት ዶ/ሩ ‹‹መለስ ኢህአዴግን ሲሰራ ፖለቲከኛ እንዳይወጣ ተከላክሏል›› ሲሉ ይተቻሉ፡፡ በፓርቲው ውስጥ አንብበዋል የተባሉት እነ ተወልደ ወልደማርያም፣ አለምሰገድ ገብረአምላክ፣ አውአሎም ወልዱ፣ ገብሩ አስራት፣ አልተረፉም፡፡

በተቃራኒው አሁን ያሉትን እነ አለቃ ፀጋዬ በርሄ፣ አባይ ወልዱ፣ ደብረፅዮን ገብረሚካኤል፣ ቴዎድሮስ አድሃኖምን የመሳሰሉት የፖለቲካ ተክለ ቁመናቸው የወረደ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ‹‹ኢህአዴግ ካድሬ ብቻ አለው›› የሚሉት አንድ አስተያየት ሰጪ ‹‹እነኚህ የተባለውን ብቻ የሚደግሙ እንጂ የሚፈጥሩም፣ የሚጠይቁም አይደሉም›› ይላሉ፡፡

በአስተያየት ሰጪው ትንተና ‹‹ሽመልስ ከማል፣ ሬድዋን ሁሴን፣ ተፈራ ደርበው፣ ቴዎድሮስ አድሃኖም›› በዚህ ምድብ ናቸው፡፡ በተለይ ህወሓት ተተኪ የሌለው መሆኑን አብዛኞቹ ሰዎች ይስማሙበታል፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው በተቃራኒ ኢህአዴግ የመተካካት ፖሊሲ በመንደፉ ምንም ችግር አይመጣበትም የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች አሉ፡፡ መለስ ዜናዊ በተለይ በግንባሩ ሊከሰት የሚችለውን የስልጣን ሽኩቻ ለመቀነስ ም/ጠ/ሚኒስትሩን ከደቡብ መምረጣቸውን ዋቢ በማድረግ ይከራከራሉ፡፡ ስሜ መጠቀስ የለበትም ያሉ አስተያየት ሰጪ በበኩላቸው ‹‹መለስ ከማንም በላይ በኤርትራዊ አጀንዳ መጠመዱን ህወሓት ባያውቅም ስልጣን እና ጠመንጃ በእጁ ነው፤ ኢኮኖሚውንም ወደ መቆጣጠሩ ገብቷል፤ ምንም ቢፈጠር ስልጣኑን በሆነ መንገድ ያለችግር ያስኬዳሉ›› ይላሉ፡፡ አስተያየት ሰጪው ጉዳዩን “in this line of reasoning ነው ማየት የሚቻለው›› ይላሉ፡፡

የሆነው የብዝበዛው ድርጊት እንዲቀጥል የተመቻቸ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀነቀኑ ቡድኖች ጦር ሜዳ ሲዋጉ እርሳቸው መፈንገያ የሚሆናቸውን ቦና ፓርቲዝም ይፅፉ እንደነበር ይነገራል፡፡ ባሸናፊነት የተደመደመውን ጦርነት አሰብ ድረስ በመሄድ የመደራደሪያ ካርድ እንዳይሆናቸው መከላከላቸውም ይነገራል፡፡ በመቀጠልም ‹‹በህግ ስም አስነጠቀን›› ይላሉ፡፡

‹‹Business as usual››

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህፓርቲ የህዝብ ግንኙነት የሆኑት ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ



መቀሌ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር የሆኑት አቶ መምሬ ውለታው (ስም የተቀየረ) ‹‹የድህረ መለስ ኢህአዴግ መልካም አጋጣሚ ይኖረዋል›› ይላሉ፡፡ በመለስ ዙሪያ ያሉትን ሰዎች በመዘርዘር ምሳሌ የሚሰጡት አቶ መምሬ ኤርትራዊ የኋላ ታሪክ ያላቸውና በመለስ ዙሪያ ወሳኝ ሚና ያላቸውን ሰዎች በማባረር ኢትዮጵያዊነትን መላበሱን ይሞግታሉ፡፡ ‹‹ህጉን በማጠላለፍ እያወጣ የሚያሳስረው ፋሲል ናሆም ነው፤የም/ጠ/ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ታኮ አምባሳደር ብርሃነ ገብረ ክርስቶስ ናቸው፤ የበሬ ወለደ መረጃ የሚያቀብለንና የቤተ መንግስት ሚዛን አስጠባቂ የሆነው ሰው አቶ በረከት ነው፡፡ ሳሞራ ወታደሩን ያዛል፤ ኪዳኔ፣ ኢሳያስ … የተባሉ ሰው የማያውቋቸው በያንዳንዱ ጀርባ ያሉ ኤርትራዊ ናቸው›› ይላሉ፡፡

ይህን ትንታኔ የሚደግፉ አስተያየት ሰጪዎች የባድመ ጦርነት ወቅት ‹‹መለስ ዜናዊ ሰላማዊ መፍትሄ›› እያሉ የነበረው የጦርነቱ መንስዔ ‹‹መለስ ካድሬውን ከፋብሪካ እንደወጣ ምርት አንድ አድርጎ በመስራቱ ከህልፈታቸው በኋላ እንኳ ለውጥ እንዳይጠበቅ ማድረጉን ይናገራሉ፡፡ ‹‹ችግሩ ከካድሬው ጀምሮ ነው›› የሚሉት ዶ/ሩ ‹‹ጠ/ሚኒስትሩ ቢያልፉም እንኳ በመንፈስ በነርሱ ላይ ሰፍረው ይኖራሉ፤ የድርጅቱ ባህሪም ያው ነው፤ ባይሆን እኮ ከዚህ በፊት እርሳቸው እያሉም ፍንጭ ይታይ ነበር፤ መለስ እንዲህ አለ፤ እከሌ ደግሞ በተቃራኒው እንደዚያ አለ ተብሎ አያውቅም›› በማለት የተለየ ነገር ከኢህአዴግ እንደማይጠበቅ ይመክራሉ፡፡ ዶ/ር ኃይሉ ‹‹ሌላ ሰው ቢመጣ አንደኛ ሌላ ሰው በመሆኑ ሁለትም ከመጣበት ባህል አንፃር ትንሽ ልዩነት ቢኖረውም ስር ነቀል ለውጥ (fundamental change) የለም›› ሲሉ ይደመድማሉ፡፡ በአዋሳው 7ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ‹‹መተካካት›› የምል ሀሳብ በአዲስ ሁኔታ ቢታይም ተግባሩ አሮጌ ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ነው›› ይላሉ፡፡

በመተካካት ዙሪያ ብዙ ቢባልም ከተመረጡት 36 ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት አዲስ ስም ሆኖ የተካተተው 6 ብቻ ነበሩ፡፡ ይህ ከመቶኛ ሲሰላ 16.6 ነው፤ በሁለት ዙር ሙሉ በሙሉ አዲስ አመራር ለመገንባት የፈለገ ፓርቲ 83.4 በመቶ ባንዴ ለመተካት ቢሞክር አደጋው የሚከፋ ይሆናል፡፡

## ቻይናኛ ፖለቲካ

ኢህአዴግ ከያንዳንዱ አባል ደርጅት የተውጣጡ 180 የም/ቤት አባላት ያሉት ሲሆን ከያንዳንዱ የግንባሩ ፓርቲ 45 ሰዎች ይወከላሉ፡፡

ከነዚህ የምክር ቤት አባላት ሌሎች አስራ አምስት ሰዎች ከያንዳንዱ ፓርቲ ተመርጠው 45 ሰዎች የማዕከላዊ ኮሚቴ ይሆናሉ፡፡ የግንባሩ አባላት 9 ሰዎችን ለስራ አስፈፃሚነት የሚመርጡ ሲሆን ፖለቲካውን የሚዘውረው ይህ ስራ አስፈፃሚ ነው፡፡ እንደ ፖለቲካ ተንታኞች አባባል የኢህአደግ ስራ አስፈፃሚ ከቻይናው ፖሊሲ ቢሮ ጋር እኩል ነው፡፡ የፍልስፍና መምህሩ ከዚህ በታች ያለውን የትኛውም አመራር ‹‹ፖለቲካዊ ውሳኔ ላይ ምንም መብት ስለሌለው ድህረ መለስ ኢህአዴግ ላይ የሚፈጥረው ለውጥ ትርጉም አልባ ነው›› ይላሉ፡፡ ስራ አስፈፃሚው የፖሊሲ ክለሳና ለውጥ ብቻ ሳይሆን የስልጣን ሽግሽግም በመምራቱ ‹‹የኢህአዴግ ፖለቲካ ቻይንኛ ነው›› ይላሉ መምህሩ፡፡ አስተያታቸውን ለፍኖተ ነጻነት የሰጡት እኚህ መምህር አቶ በረከት ስለ ጠ/ሚኒስትሩ ጤና ለህዝብ ይፋ ያለማድረጋቸውን ሲጠየቁ የመለሱት መልስ ብቻ ሳይሆን አመላለሳቸውም ‹‹ጥብቅ ማዕከላዊነትን ያመላከተ ነው›› ይላሉ፡፡

## ትልቁ ሽንቁር

ኢህአዴግ መሬት ላይ ካለው ጥንካሬው ይልቅ የሚያስተጋባው (echo) ይበልጣል፡፡ ብሔር ላይ ያለቅጥ መመስረቱን እስካልቀየረ ድረስ ህብረ ብሔር መሆን እንደሚከብደው የሚደመድሙ አልጠፉም፡፡ ፓርቲው እስከ ቀበሌ ድረስ በመውረድ ጠንካራ መዋቅር መዘርጋቱ ፓርቲውን የማይነቃነቅ አስመስሎታል፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ በህይወት ከቆዩ ስልጣን ቢለቁ እንኳ ከኋላ በመሆን ሁሉን ለመከወን መዘጋጀታቸውን (Putinism) በተለያዩ ወቅቶች ድህረ ስልጣን በምን ሁኔታ እንደሚቆዩ ለተጠየቁት ጥያቄ ከሰጧቸው መልስ መረዳት እንደሚቻል የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ፖለቲካው ባለበት በድንገት ጥለው የሚያልፉ ከሆነ የፖርቲ ውስጥ አንድነት (Harmony) ያለመገንምባት የርስ በርስ ሽኩቻ ማስከተሉ አይቀሬ መሆኑን ታዛቢዎቹ ያስቀምጣሉ፡፡ በተጨማሪም ተቃዋሚዎች፣ የራሱ የኢህአዴግ አኩራፊዎች፣ ነፍጥ አንጋቾችና መንግስት አልባነት የሚጠቀሙበት ቡድኖች የኢህአዴግ ፈተና ሊሆኑ እንደሚችሉ ይነገራል፡፡ በነዚህ ሁኔታዎች ገና ያልተፈተነውን ኢህአዴግ ‹‹ጠንካራ የሚመስል ግን ልል›› /Brittle but stable/ ስሉ ይገልፁታል፡፡

## ሽኩቻው ላይ ማን ይሳተፋል?

ዶ/ር ሙሉ አበራ ‹‹አማሮቹ የኢትዮጵያን መዳን ይፈልጋሉ›› ሲሉ ይጀምራሉ፡፡ ‹‹የበላይነት በጭራሽ አይፈልጉም፤ ይልቅ በአማራ ስም የተወከለውን የፊውዳል ስርዓት የተዋጋው ማን ነው? ኢህአፓ ውስጥ ስንት የፊውዳሉ ልጆች ስርዓቱን የሚገነድስ ‹መሬት ለአራሹ›ን አቀንቅነዋል? መኢሶን ውስጥስ? አማራ የህይወት መስዋዕትነት ከፍሏል፤ ትግሬኛ ተናጋሪዎቹ ከነቁ ከሻዕቢያ መንፈስ ተላቀው ከአማሪኛ ተናጋሪው

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

ፖለቲካ



# የሙስሊሙ ብስለት፣ የመንግስት ክስረት፣ የኢቲቪ ቅጥፈት



ነብዩ ኃይሉ

የአዲስ አበባ አየር ከጨፈገገ ሰነባብቷል፤ የክረምቱ ቅዝቃዜ የፀሀይን ወራት የሚያስናፍቅ ነው፡፡ ፖለቲካው ግን ቀድሞ የፀሀይን ወራት የናፈቀ ይመስላል፤ የፖለቲካው ነፋስ የክረምቱን ድባቴ ገለል እያደረገ ድንገቴ ክስተቶችን በማንፈስ የፖለቲካው ክረምት እየጠራረገው ይመስላል፡፡ የፖለቲካው ውጥረትና ግለትም ከጊዜ ወደ ጊዜ በመናር ላይ ይገኛል፡፡ ከክረምቱ ድንገቴዎች መካከል ለሰባት ወራት የቀጠለው የሙስሊሙ ተቃውሞ "ከመጅሊስ ወደ መለስ" እየዞረ መምጣት፣ የአቶ መለስ አልጋ ላይ መዋልና እሱንም ተከትሎ በኢህአዴግ ውስጥ የተጀመረው የስልጣን ሽሚያ (power struggle) የክረምቱ የፖለቲካ ግለቶች ሆነዋል፡፡

የአቶ መለስ መንግስት የአለቃውን ህመም ተከትሎ የገባበት ውጥረት ላይ የተጨመረው የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተቃውሞ የስልጣኑን መሰረት እንዳያሳጣው የሰጋ ይመስላል፡፡ ወራትን ባስቆጠረው የመንግስትና የሙስሊሙ ህብረተሰብ አለመግባባት፣ በሙስሊሙ አካባቢ የነበረውን የድጋፍ መሰረት ቀስበቀስ ተንዶበታል፡፡

ከታሪካዊው የታህሪር የአደባባይ ተቃውሞ ወዲህ በአፍሪካ በርካታ ሰዎችን የያዘና የተደራጀ ታላቅ ትእይንተ ህዝብ ሲደረግ የሰሞኑ የአዲስ አበባ የሙስሊሞች ተቃውሞ የመጀመሪያው ነው፡፡ በተለይም በዘንድሮው የረመዳን ፆም የመጀመሪያ አርብ ሐምሌ 13 በአንዋር መስጂድና አካባቢው በተደረገው ድምፅ አልባ የተቃውሞ ትዕይንት የተሳተፈው በግምት ከአምስት መቶ ሺ በላይ የሚሆነው ህዝብ በፍፁም ጨዋነት የተቃውሞው መልዕክቱን አስተላልፎ በሰላም መበተኑ የሙስሊሙን ህብረተሰብ የብስለት ደረጃ በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ ከአሁን አሁን ተበጠበጠ፣ ከአሁን አሁን ድንጋይ ተወረወረ ብለው ሲጠባበቁ የነበሩት የመንግስት ሃይሎች በእጅ ምልክት የታጀበውን የተቃውሞ ትእይንት እንደ ቲያትር ለመመልከት ተገደዋል፡፡

ይህ አይነቱ ሰላማዊ የተቃውሞ መንገድ ከማህተመ ጋንዲም ሆነ ከማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የሰላማዊ ትግል ስልቶች የላቀና የረቀ መሆኑ፣ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚወደስበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡ ይህ አይነቱ ተግባራዊ የተቃውሞ ስልት ሰላማዊ ትግልን መግለጫ በመስጠት ብቻ ገድበው ለተቀመጡት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ብዙ ሊያስተምር የሚችል መሆኑ አንድና ሁለት የለውም፡፡

የተቃውሞ እንቅስቃሴው መሪዎች እንደሚታሰሩ ባስ ካለም በመብት ጥያቄ ትግላቸው ሕይወታቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ አስቀድመው ተረድተዋል፡፡ ለዚህም ይመስላል የእነሱን መታሰር ብሎም ሕይወትን ማጣት ተከትሎ ህዝቡ ወደ ግብታዊ የሀይል እርምጃ እንዳገባ አስቀድመው መቀስቀሳቸው፡፡ ሌላው ብስለት የተሞላው እንቅስቃሴ የመንግስት ሚዲያዎች የተቃውሞ እንቅስቃሴው በሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ላይ ስጋት እንዲፈጥር የተሰሩትን የህዝብ ግንኙነት ስራዎች በማክሸፍና የሙስሊሙን ጥያቄ በቀና ልቦና እንዲወስደው ብሎም ከጎናቸው እንዲሰለፍ ለማድረግ ያደረጉት የተሳካ የማግባባት ስራ በሂደት ለውጥ እያመጣ መሄዱ የሚያጠራጥር አይመስልም፡፡

የሙስሊሙ ተቃውሞ ከመጅሊስ ወደ መለስ እንዲዞር እያደረጉ ካሉ አጋጣሚዎች መሀከል የኢቲቪ ቅጥፈት ትልቁን ቦታ ይይዛል፡፡ ጣቢያው የስርአቱ ዋንኛ የፕሮፓጋንዳ ማሽን እንደመሆኑ መጠን የገዢዎቹን ጥቅም ለማስከበር "ጋግሮ" የሚያሰራጫቸው መረጃዎች ህዝቡ ዘንድ መዘባበቻ አድርገውታል፡፡ እንደተለመደው የሙስሊሙን መሰረታዊ ጥያቄ በተንሸዋረረ መነፅር በማሳየትና የጥያቄውን መንፈስ ፖለቲካዊ ይዘት በማላበስ የጋገረውና እየጋገረ ያለው መረጃ መንግስት በሙስሊሙ ላይ ያለውን አቋም በአንድም ሆነ በሌላ የሚገልፅ ይመስላል፡፡

በተለይም በቅርቡ እስከ ግጭት ለደረሰው አለመግባባት ትልቁን ሚና የተጫወተው በቅርቡ "ብዙ ሃይማኖት አንዲት ሀገር" በሚል ርዕስ በኢቲቪ የቀረበው ዘጋቢ ፊልም እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች "ተቃውሞውን በመቃወም" የተደረጉ ሰልፎች ሰፊ የዜና ሽፋን በመስጠት የውግዘት መአት ማውረዱ ነው፡፡ ጣቢያው የሙስሊሙን እንቅስቃሴ ፖለቲካዊ ታፔላ በመስጠት ሙስሊሙም ሆነ ክርስቲያኑ እንቅስቃሴውን የጎሪጥ እንዲመለከተው የተለያዩ የፕሮፖጋንዳ ስራዎችን ሰርቷል፡፡

ኢቲቪ መረጃውን ጋርሮ ሳይጨርስ ህዝበ ሙስሊሙ ክስተቶችን ወዲያውኑ በፌስ ቡክና በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ለህዝብ ያዳርሳሉ፡፡ ኢቲቪ ከብዙልፋት በኋላ የሚያሰራጨው መረጃ የማደናገር አቅም የሚኖረው ለቴክኖሎጂ ቅርበት የሌለውን የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሚቀርቡትን መረጃዎች ሳይመረምሩ ለመቀበል የሚከብድ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማህበራዊ ሚዲያዎቹ እውነተኛውን መረጃ ከምስል ማስረጃ ጋር ማቅረባቸው ኢቲቪ የሚያቀርባቸው መረጃዎች ተፋልሶ ቁጣን እንዲቀሰቅስ አድርጎታል፡፡

በኢቲቪ እና ክስተቱን እየተከታተሉ በማህበራዊ ሚዲያዎች በሚዘግቡ መካከል የሚተላለፈው መረጃ ያለው ሰፊ የመረጃ ልዩነት አስገራሚ ነው፡፡ ለማሳያት ያክልም ቅዳሜ የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ ፖሊሶች ምዕመናኑን ሲያሳድዱና ሲደበድቡ የሚያሳዩት የቪዲዮና የፎቶግራፍ ምስሎች በማህበራዊ ሚዲያዎች ተሰራጭተው ምዕመናኑ ላይ የደረሰውን በደል ሲያሳዩ፤በሌላ በኩል ደግሞ ኢቲቪ ቅዳሜ ማታ ባሰራጨው ዜና "አክራሪዎች" ሙስሊሙን በአንዋር መስጂድ አግተው እንደነበር በማተት የእንቅስቃሴውን ህገ ወጥነት ተናገረ፤ በግጭቱ የወደሙ ንብረቶችንም አሳየ፡፡ ሆኖም ጣቢያው ምእመናኑ ድንጋይ ሲወረውሩ እንጂ ፖሊሶቹ ድብደባ ሲፈፅሙ አላሳየም፡፡ የግጭቱንም እውነተኛ መንስኤ ለማመላከት አልደፈረም፡፡ የተቃውሞው እንቅስቃሴ በሀገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ሚዲዎች በቂ ሽፋን አለማግኘቱ የእንቅስቃሴውን የሰብአዊ መብት ጥሰትና በሀገሪቱ ፖለቲካ ላይ የሚኖረውን በጎም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በጉልህ እንዳይታይ እንቅፋት ሆኖበታል፡፡

መንግስት ከሙስሊሞች እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ኪሳራዎችን ለማስተናገድ የተገደደ ይመስላል፡፡ ተቃውሞው ፖለቲካዊ ገፅታ እንዲይዝ ያደረገው ጥረትም ሆነ እንቅስቃሴውን ከህዝቡ ለመነጠል ያደረገው ጥረት የሰመረ አይመስልም፡፡ መንግስትን ትዝብት ላይ ከጣሉት አጋጣሚዎች መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሰው ከሳምንታት በፊት በኢቲቪ ባስተላለፈው "ብዙ ሃይማኖት አንዲት ሀገር" በሚለው ዘጋቢ ፊልም ላይ የሃይማኖት ምሁራን በሚል ያቀረባቸውን ግለሰቦች በሳምንት ጊዜ ውስጥ አሸባሪ በማለት አፋፍሶ ማሰሩ ነው፡፡

የታሰሩት ግለሰቦች የተቃውሞ እንቅስቃሴውን ለሰባት ወራት ሲመሩ ቆይተው አሁን የፖለቲካው ውጥረት ሲያይል መታሰራቸው ከኢህአዴግ የተለመደ ባህሪ አንፃር የእስሩን ፖለቲካዊ አንድምታ የሚሰጥ ነው፡፡ የተቃውሞ እንቅስቃሴው መሪዎች ህዝቡ በየትኛውም ምክንያት ወደ ስሜታዊ እንቅስቃሴ እንዳይገባ መቀስቀሳቸው፣ የመንግስትን ውንጀላ ከንቱነት ያረጋገጠ ይመስላል፡፡

መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት በሙስሊሙ ላይ ብቻ ባይሆንም የተቀሩት ሃይማኖት ተከታዮች ተቃውሟቸውን ወደ አደባባይ ለማውጣት የደፈሩ አይመስሉም፡፡

በወቅታዊው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ውጥረት ውስጥ የጎላ ድርሻ ያበረከተው የሙስሊሞች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ወዴት እንደሚያመራ ለመገመት አስቸጋሪ ቢሆንም በኢትዮጵያ ሰላማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ውስጥ ያስፈረው አሻራ ግን ለዘመናት አይረሴ ሆኖ ቀጥላል፡፡

# የሰው እጅ ጣቶች በንጉሥ ቤት "ማኔ፣ ቴቁል፣ ፋሬስ"

ቀለሙ ሁነኛው
kelemhun@yahoo.com

የናቡከደነፆር የልጅ ልጅ እና የአዲሲቱ ባቢሎን መንግስት የመጨረሻ ንጉሥ የነበረው ብልጣሶር እግዚአብሄርን ክፉኛ ማሳዘኑን ትንቢተ ዳንኤል ይነግረናል፡፡ ንጉሱ በትዕቢት ተሞልቶ የእግዚአብሔርን ቤት መቅደስ እቃዎች አረከሰ፡፡ ከእንጨትና ከድንጋይ የተሰሩ ጣዖታትን በማምለክ ፈጣሪውን አስቆጣ፡፡ የንጉሱ ጋሻጃግሬዎችም በወይንጠጅ ጠግበው ነበርና ግብዣ ላይ ሣሉ በቤቱ ግንብ ላይ የምትጽፍ የሰው እጅ ጣት ታየችው፡፡ ፅሁፉንም አነበበ፡፡ "ማኔ፣ቴቁል ፋሬስ" ይላል፡፡ "በዚህ ጊዜ ጉልበቶቹ ተብረከረኩ፣ የወገቡም ጅማቶች ተፈቱ፣ የንጉሡ ፊት ተለዋወጠ" ይለናል ቅዱሱ መጽሀፍ፡፡ ንጉሱም የጽህፈቱን ትርጉም ይረዳ ዘንድ ከለዳዊያንን፣ አስማተኞችን፣ ቃላተኞቹን አሰባስቦ ፍቺውን እንዲነግሩት አወጀ፡፡ አንዳቸውም ግን አልተቻላቸውም፤ በመጨረሻም የቃላቱ ፍቺ ከነቢዩ ዳንኤል ዘንድ ተገኘ፡፡

ማኔ፡- እግዚአብሔር መንግሥትህን ቁጠረው፣ ፈፅመውም፤ ቴቁል፡- በሚዛን ተመዝነህ ቀለህ ተገኘህ፤ ፋሬስ፡- መንግስትህ ተከፍሎ ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎች ተሰጠ

እግዚአብሔር በነቢዩ ዳንኤል በኩል የጽህፈቱን ፍቺ ባስታወቀበት በዚያው ሌሊት ንጉሥ ብልጣሶር እንደተገደለና ዳርዮስ መንግስቱን እንደወሰደ መጽሐፍ ቅዱስ ያብራራል፡፡

ንጉስ ብልጣሶር ከአያቱ ከንጉስ ናቡከደነፆር እጅግ ዘግናኝ ውርደት መማር ያልቻለ ንጉስ ነበር፡፡ አያቱ እግዚአብሔር ባስቀመጠው ዙፋን ላይ ሆኖ ፈጣሪውን በመዘንጋት እጅግ የረከሰ ተግባር በመፈፀሙ ተዋርዶ ሰባት አመት እንደበሬ ሳር መብላቱን ፍፁም ዘነጋው፡፡ እሱም እንደ አያቱ ጊዜ እንኳን ሳያገኝ ነፍሱ ከሥጋው ተለየች፡፡

እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ ለማንገስ የሚቀባቸው ነገስታት መስመራቸውን ሲስቱ በህልምም ይሁን በራዕይ ሀሳቡን ያሳውቃቸዋል፡፡ እጅግ የተመሰጠረ መልዕክቱን በነቢያቱ አማካኝነት እንዲፈቱ ያደርግና ውሳኔውን ያሳውቃቸዋል፡፡ የአምላክ ቃል ነውና ይተገበራልም፡፡

የንጉስ ብልጣሶር ግን ለየት ይላል፡፡ እሱ የተመለከተው በሰው የእጅ ጣቶች ሲፃፍ ነው፡፡ የቃላቱ ሚስጥራዊነትም ንጉሱን በብርቱ አስጨንቆታል፡፡ ፍቺውን ሳይረዳ እረፍት ማግኘት አልቻለም ነበር፡፡ እኒያ የሰው ጣቶች ግን እውነትን ነበር የፃፉት፡፡ ከላይ ከፀባኦት ከታላቁ ፈጣሪ ዘንድ የተላከን እውነተኛ መልዕክት ሳይዋሹ ፃፉ፡፡ እነዚህ ጣቶች እስከ ፃፉበት ደቂቃ ድረስ ንጉሱ ፈጣሪውን ስለመበደሉ የተፀፀተ ወይም የሚፀፀት ልብ አልነበረውም፡፡

ለዛሬው ጽሁፌ ርዕስ የመረጥኩት ከመጽሐፍ ቅዱስ የዳንኤል ትንቢት ነው፡፡ የሰው እጅ ጣቶች ዛሬም በንጉስ ቤት ታስፈልጋለችና፡፡ ምንም እንኳን የ21ኛው ክ/ዘመን መሪዎቻችን በእ/ር ስለመሾማቸው ባያምኑም እንዳለፉት ዘመናት ነገስታት ሁሉ ህዝባቸውን በመበደላቸው ፈጣሪን ጭምር የሚገዳደሩ ጥፋቶችን በመፈፀማቸው እ/ር በተለያዩ መንገዶች ይናገራቸዋል፤ ግን አይሰሙም፡፡ ይባስ ብለው በእስራኤል ላይ እንደነገሱት ጨካኝና ለቀባቸው አምላክ እንዳልታዘዙት በክብር ተሹመው የውርደት ማቅን እንደለበሱት ነገስታት እውነትን የሚነግሯቸውን ያሳድዳሉ፡፡ የንጉስ አክኣብ ሚስት ኤልዛቤል ነቢዩ ኤልያስ የበአል ነብያትን አስገድሏል በሚል ልትበቀለው ባሰበች ጊዜ ኤልያስ ወደ ኮሬብ ተራራ ተሰደደ፡፡ ነቢዩ ዳንኤል በንጉስ ዳርዮስ ዘንድ ያገኘውን ክብርና ሞገስ ለመንጠቅ ንጉሱን በፋርስና በሜዶን ህግ ቃል አስገብተው የዳንኤልን ጥፋት በማጉላት ከአንበሳ ጉድጓድ ቢወረውሩትም አምላኩ አብሮት ነበር፡፡ ነገስታቱ ግን እውነቱን የሚነግሯቸውን ነቢያትና ቅዱሳንን ቁም ስቅል ያሳይዋቸው ነበር፡፡

ዛሬም የአራት ኪሎው መንግስት፣ የቀድሞው ወታደራዊው ደርግ እውነቱን የሚያሳዩትን እንደሚሰቅልና እንደሚያሳድድ ሁሉ እሱም በተራው እያደረገው ነው፡፡ የሰው እጅ ጣቶች ብዕራቸውን ጨብጠው የኢህአዴግን አካሄድ በተቹ ቁጥር ሞትና እሥራት ይደገስላቸዋል፡፡ በእያዳንዱ እርምጃቸው ዛቻና ማስፈራሪያ ይከተላቸዋል፡፡ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የቅጥፈት ሐጢያታቸውን ለማብዛት የማይማስ ጉድጓድ የለም፡፡ የጨበጡትን ብዕር ለማስጣል የማይሸረብ ሴራ የለም፡፡ ዛሬ የፀረ ሽብር ህጉ ከሜዶንና ከፋርስ ህግ የከፋ ሆኗል፡፡ የሰለጠነው ዓለም በአሸባሪነት የፈረጃቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ከእኛ አገር መሪዎች ፍረጃ ጋር ሲተያይ "ዱባና ቅል . . ." እንዲሉ ሆኗል፡፡ የኛ መንግስት በአሸባሪነት ዘብጥያ ያወረዳቸውን ጋዜጠኞች እነ እስክንድር ነጋንና ርዕዮት ዓለሙን የሰለጠነው ዓለም ሀቅን የሚያነጥቡ ብዕረኞች መሆናቸውን በማመን ሲሸልማቸው ስናይ የመንግስታችን አካሄድ ፍፁም ግራ ያጋባናል፡፡ መሪዎቻችን ከሰለጠኑት አገራት ቁንጮ መሪዎች ጋር ስብሰባ ማዕድ እየተቋደሱ ከእነሱ መማር አለመቻላቸው እጅግ የሚያሳዝን ነው፡፡

ከንጉስ ብልጣሶር መሞት በኋላ ሜዶናዊው ዳርዮስ ሥልጣን ሲይዝ ከናቡከደነፆርና ከብልጣሶር አሳዛኝ አወዳደቅ የተማረ ይመስላል፡፡ ንጉሱ ለነቢዩ ዳንኤል ከነበረው ክብር የተነሳ ጋሻ ጃግሬዎቹ ነቢዩን ሊያጠፉ አሴሩ፡፡ የፋርስና የሜደንን ህግ ተጠቅመው አንበሳ ጉድጓድ እንዲጣል ሲያደርጉ ንጉስ ዳርዮስ አልተስማማም፡፡ አስቀድሞ ሊታደገው ቢሞክርም የሕጉ አለመሻር እንቅፋት ሆነው፡፡ ግን አንድ ብርቱ እምነት ነበረው፡፡ የዳንኤል አምላክ ከአንበሳ አፍ እንደሚያድነው አስቀድሞ አምኗል፡፡ በእርግጥም እምነቱ ሰምሮ አየው፡፡ ዳንኤልን አንበሳ ጉድጓድ ያስጣሉት የንጉሱ ጋሻጃግሬዎች ግን የአንበሶች ሲሳይ ሆኑ፡፡

የኢህአዴግ መሪዎች የመጡበትን መንገድ የዘነጉት ይመስላሉ፡፡ ለደርግ ውድቀት መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን እንደ ወራጅ ውሃ ቆጥረውታል፡፡ ደርግን ድል ባደረጉባቸው አስር አመታት ውስጥ የነበራቸው ግንዛቤ የተሻለ ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡ ቢያንስ እንደልብ መናገር ይቻል ነበር፡፡ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ የራስን ሀሳብ ለመግለጽ የከፋ ጫና አልነበረም፡፡ የሰላማዊ ትግሉ ተዋናይ የሆኑ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችም ይብዛም ይነስ በየአደባባዩ ኢህአዴግን በመኮነን የመናገር ነፃነቱ ነበራቸው፡፡ የዛሬዎቹ አኤዎቻችን ትናንት ባሳለፉት የበረሀ ህይወት የተለማመዱት ትልቁ መልካም ነገር ሀሳብን በነፃነት ማንሸራሸርና በድርጅት ስሜት በአንድ አይን መተያየት ነበር፡፡

በአገራችን የዲሞክራሲው ጭላንጭል ሙሉ በሙሉ የጨለመው ከምርጫ 97 በኂላ መሆኑ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ኢህአዴግና የዲሞክራሲ ጽንሰ ሀሳብ ጆርባና ሆድ ሆኑ፡፡ ያ መላውን የአገሪቱን ህዝብ ከዳር እስከ ዳር ያነቃቃው የቅንጅት መንፈስ ዳግም እንዳያንሰራራ የማፈኛ ህጎች እንደ አሸን እየፈሉ ፀደቁ፡፡ በምርጫ 2002 ዓ.ም 99.6% ማሸነፉን በግላጭ ያወጀው ኢህአዴግ ራሱን ፍፁም አድርጎና አይኑን በጨው አጥቦ "አውራ ፓርቲ ሆኛለሁ" ሲልም ነገርን፡፡ ዲሞክራሲ ደህና ሰንብች!

ይሁን እንጂ የተቀጣጠለው የለውጥ ቋያ የረመጡ ትኩሳት ዛሬም አልቀዘቀዘም፡፡ የሰላማዊ ትግሉን ችቦ ለኩሰው ከኢህአዴግ አፋኝ ህግጋት ጋር የሚታገሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ወድቀው አልቀሩም፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ ሰላማዊ ትግሉ ፀንሶ የሚወልዳቸውን ወጣት ፖለቲከኞችና ሀቅ አብሳሪ ጋዜጠኞች ብቅ ባሉ ቁጥር እያነቀ ቃሊቲ

ወደ ገፅ 15 ይዞራል....

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ፡ ፡ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ::

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነዉ:: ማንኛዉም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡ ፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን አለዉ የሚባለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ::

ዋና አዘጋጅ፡-
ነብዩ ኃይሉ
አድራሻ፡-
ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 10
የቤት ቁ. 320
ኢ.ሜይል፡- nebiyuhailu@gmail.com

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል
ሰለሞን ስዩም

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መስፍን


አምደኞች፡-ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ቀለሙ ሁነኛዉ
በለጠ ጎሹ
አንዷለም አራጌ
ደረጀ መላኩ

ኮምፒዩተር ጽሁፍ፡-
ብርቱካን መንገሻ
ህትመት ክትትል፡-
ወንድወሰን ክንፈ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ
አሳታሚዉ፡-አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
አድራሻ፡-አራዳ ክ/ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁ. አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ ከተማ ቀበሌ 07 የቤት ቁ.984
የዝግጅት ክፍሉ ስልክ፡- 01 11249659
09 22 11 17 62
09 23 11 93 74
09 13 05 69 42
ፖ.ሳ. ቁ. 4222
ኢ.ሜይል fnotenetsanet@yahoo.com
ujdparty@gmail.com
andinet@ andinet.org
ፋክስ ቁጥር ፡-+251-111226288

# ርእሰ አንቀፅ



# ከመንግሥት መረጃ የማግኘት መብት አለን!

ሰሞኑን ዝግጅት ክፍላችን የደረሱንን ዜናዎች ዘወትር እንደምናደርገው ሚዛናዊለማድረግ ወደ መንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊ ደውለን ነበረ:: ኃላፊው የሰጡን መልስ ‹‹እናንተን እንደ ጋዜጣ አልመለከትም፣ደም ለማፋሰስ ነው›› ብለው ስልክ ዘግተውብናል::

ባለን መረጃ ዓለማችን በርካታ እልቂቶችን አስተናግዳለች፡ ፡ በአንደኛው ዓለም ጦርነትና በሁለተኛው ዓለም ጦርነት የተፈጠረውን የዘር ማጥፋት ማስታወስ ይቻላል:: በሩዋንዳና በቡሩንዲ የተፈፀመው የዘር ማጥፋት ድርጊት ዘግናኝ ነው፡ ፡ አንድ ሃይማኖት አንድ ቋንቋ አንድ ዘር በሆነው ሶማሊያ ለግል ስማቸው፣ ክብራቸውና ጥቅማቸው የቆሙ የጐሳ መሪዎች በገነቡት መንደርተኛ አስተሳሰብ ዛሬም በሶማሊያ መቋጫ ያልተበጀለት ዕልቂት እየተፈፀመ ነው::

ደርግ ሥልጣን በያዘበት ማግስት በታወጀው ቀይ ሽብር አገራችን አንድ ትውልድ አጥታለች፤ ወንጀለኞቹ በህግ ቢጠየቁም ጠባሳው ዛሬም አልሻረም:: ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ እጅግ ዘግናኝ እልቂቶች ተፈጽመዋል:: የበደኖ፣ ወለጋ ባምባሲ፣ ጂማ፣ አርሲ፣ አርባጉጉ፣ አሰቦት ገዳም ባንዲራና ዘንባባ ይዞ መብቱን ለመጠየቅ አደባባይ በወጣው የአዋሳ ህዝብ ላይ የተፈፀመው ጭፍጨፋ፣ በጋምቤላ አኝዋክ ህዝብ የተፈፀመው የጅምላ ጭፍጨፋ፣ በድሬዳዋ ከተማ ላይ የተፈፀመው የግፍ ግድያ፣ በምርጫ 97 የአዲስ አበባ ህዝብ ቅንጅትን በመምረጡ የተፈፀመ የግፍ ጭፍጨፋና ግድያን ማስታወስ ይቻላል:: ጨፍጫፊዎቹም አስጨፍጫፊዎቹም እስከ ዛሬ ለህግ አልቀረቡም:: በአገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ደም እንዲፈስ አንፈልግም::

ደም አፍሳሾች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አምርረን እንጮሓለን:: “ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል” እንደሚባለው ኢህአዴግ የራሱን እምነት በኃይል ለመጫን የሚፈፀመውን ድርጊት ማቆም አለበት ብለን እናምናለን፡ ፡ ኢህአዴግ “በሃይማኖት ጉዳይ እጄን አላስገባም” ቢልም በተጨባጭ ግን እጁን በረጅሙ ዘርግቶ ሃይማኖትን እያመሰ ነው:: በየቤተክርስቲያኑና በየመስጊዱ ወንጌልና ቁራን ከሚሰበክ ይልቅ የካድሬዎች ሰበካ አይሎ ይገኛል፡ ፡ ኢህአዴግ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት ፈጽሞአል:: በልማት ስም በዋልድባ ገዳም እየተፈፀመ ያለውንም ማንሳት ይቻላል::

ሲኖዶስ ተሰብስቦ በሃይማኖቱ አመራሮችና በእምነቱ ቀኖና ላይ ሲመክር የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ስብሰባው ላይ እየተቀመጡ ድምጽን በድምፅ እየሻሩ የፈፀሙትንና እየፈፀሙት ያለውን ድርጊት ተገቢ ነው ብለን አናምንም::

በእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ እየደረሰ ያለው ጣልቃ ገብነት መቆም አለበት:: ኢህአዴግ የሃይማኖት ሥልጠና መስጠትም ማስተባበርም አይጠበቅበትም:: የሃይማኖቱ መሪዎች የሚመረጡት በቀበሌ መስተዳድር ውስጥ ሳይሆን በየመስጊዳቸው በራሳቸው አጀንዳ ሊሆን ይገባል:: ካድሬና ደህንነት ሙስሊሙን ህብረተሰብ እየሰበሰበ የሚያጉላላበት ሂደት መቆም አለበት ብለን እናምናለን:: በአጠቃላይ ኢህአዴግ ከደም አፋሳሽ ተግባሩ ተቆጥቦ መንግስታዊ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት:: እኛ አንድም ጠብታ ደም እንዳይፈስ እንፈልጋለን:: እኛ የደም ጥማት የለብንም:: ጥማታችን ፍትህ፤ ሠላም፣ ፍቅር፣ የህግ የበላይነት፣ የመናገርና የመጽሐፍ መብት የሆነው ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲሁም ሰብአዊ መብቶች ናቸው:: ደም አፍሳሾችም ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ጥሪያችንን እናቀርባለን:: ዛሬም እውነትን እንዘግባለን:: ለሠላም ለህግ የበላይነት እንሰራለን፡ ፡ ደም አፍሳሾች ለህግ እንዲቀርቡ እንጮሃለን::

ይህን ሀቅ በመንተራስና በህገ መንግሥቱ ላይ የተደነገጉ አንቀፆችን ዋቢ በማድረግ ህዝብ ከመንግስት መረጃ የማግኘት መብት እንዳለው ደጋግመን መግለጽ እንወዳለን::

ጋዜጣችንን “ፍኖተ ነፃነት“ ብለናታል “ፍኖት“ ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር የነፃነት መንገድ ማለት ነው::

# ከአቶ በረከት ንግግር በስተጀርባ ምን አለ?





ዳንኤል ተፈራ

ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ላለፉት 21 ዓመታት በብቸኝነት ሲዘውሩት በነበረው የስልጣን ቆይታቸው በርካታ ስሞችን አግኝተዋል፡፡ እነዚህ በርከት ያሉ ስሞቻቸው ከሁለት አቅጣጫ የሚመዘዙ ናቸው፡፡ ከደጋፊዎቻቸውና ከተቃዋሚዎቻቸው፡፡ በተለይ ብቸኛ ልዕለ ኃያል ሆነው ለመውጣት ያደረጉት ጥረት እንደ ከዚህ በፊቶቹ የኢትዮጵያ መሪዎች "ስልጣን እስከ ዕድሜ በቃኝ" መርህ ተከታዮች ጋር ማመሳሰሉ ብቻ አይደለም፡፡ በርካታ ጠላቶችንም እንዲያፈሩ አድርጓቸዋል፡፡ ስልጣን በብቸኝነት መያዝና "ፓርቲዬ ካዘዘኝ" በሚል ሰበብ ለወደፊትም ለመቀጠል ያላቸው ምኞት ይቃወሙኛል የሚሏቸውን እንዲያጠቁም ሰበብ ነበር፡፡

አቶ መለስን ደጋፊዎቻቸው ምን ይሏቸዋል? ንግግር አዋቂ፣ ብልህ፣ ቅንድባቸው የሚያምር፣ መጽሐፍቶችን ሸምጥጥ አድርገው ያነበቡና አሁን አሁን ደግሞ ከአባይ መገደብ ጋር ተያይዞ "አባይን የደፈረ ቆራጥ መሪ" እና "የልማት ጀግና" እያሉ ሙገሳ ያለስስት ሲያዥጎደጉዱላቸው እንሰማለን፡፡ ይሄ የአድናቂዎቻቸው ሙገሳ "ብቸኛ ሰው!" ሆኖ ለመውጣት የራሱን አስተዋጽኦ አድርጉላቸዋል፡፡ እንዳውም ከየዋሀኑ ሙገሳ ጀርባም እሳት የላሱ ካድሬዎች እጅ እንዳለበት ልብ ማለቱ ይጠቅማል፡፡ መለስን አግንኖ ለማውጣት አንዳንድ መፈክሮችን ያቀብሏቸዋል፡፡ ከ80 ሚሎዮን ህዝብ በላይ ባላት ኢትዮጵያ አንድ ሰው ብቻ ነው ያለው ማለት ግን ሀገርንና ትውልድን ከመስደብ እኩል ነው፡፡

ተቃዋሚዎቻቸውስ ምን ይሏቸዋል? ተቃዋሚዎቻቸው ጠ/ሚሩን የሚመለከቷቸው በጥርጣሬ ነው፡፡ "ከስራ ይልቅ ሴራ የሚያዘወትሩ፣ አምባገነን፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ቁርጠኛ ያልሆኑ፣ ጠላት የማይንቁ፣ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ሚዲያዎች ተመሳሳይ ነገር የማይናገሩ (የውስጥ ቀጋ የውጭ አልጋ)፣ ተቃዋሚዎቻቸውን የሚጠሉ፣ የዘላልማዊ ስልጣን ምኞት ያላቸው (የእግዜር እጅ ጣልቃ ገባ እንጅ!) እና ‹እኔ ከሌለሁ ሀገር ትበተናለች› እያሉ የሚናገሩ" እያሉ ትችት በቁና ያወርዱባቸዋል፡፡

እነዚህ የሁለትዮሽ ክርክሮች እንዳሉ ሆነው 21 ዓመታት ቢያልፍም ሃያ አንደኛው ዓመት ግን ገደኛ አይመስልም፡፡ ያውም ገና ግንቦት እንደተገባደደ ችግር ተፈጠረ፡፡ በርካታ ሰዎች እንደሚስማሙበት ስርዓቱ ተቀናቃኝ የሚላቸውን የሚያጠቃው ህግ እየጠቀሰ ነው፡፡ ከህጎች መካከል ደግሞ "የፀረ ሽብርተኝነት ህጉ" ይገኝበታል፡፡ በፀደቀ በጥቂት ወራት ውስጥ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች ይሄው ጦሰኛ ህግ ተጠቅሶባቸው ወደ እስር ቤት ተወረወሩ፡፡ የፀረ ሽብርተኝነት ህጉ እንደታሰበው ተቀናቃኞችን አደብ አስይዟል ብሎ ማሰብ ግን ሞኝነት ነው፡፡ እንደውም ብሔራዊ ምሬት የፈጠረ ይመስላል፡፡ "ኤጭ! አሁንስ አበዙት!" የሚለው ድምጽ ከጓዳ በመውጣት በአደባባይ መደመጥ ጀምሯል፡፡ ኢህአዴጎች የህዝቡን የብሶት ድምጽ ሰምተውት ይሆን? የሚለው እንዳለ ሆኖ ማለት ነው፡፡

ታዲያ በዚሁ ለጠ/ሚሩ ገደቢስ በሆነባቸው ዓመት አሜሪካ ያውም አንጋፋ የዓለማችን ሰዎች ባራክ ኦባማ በተገኙበት ስብሰባ ላይ አንድ የሚያስገመግም ድምጽ ድንገት እንደ ባረቀ መሳሪያ አስተጋባ "Meles is a dictator!" የብሔራዊ ብሶቱ "አሁንስ በዛ!" ወኪል ድምጽ ከጋዜጠኛ አበበ ገላው ወጣ፡፡ በትልቅ ስብሰባ ላይ ያውም "አይደፈሩም" የሚል ስም ሲገነቡ የነበሩት ሰው በድንጋጤ ዞር ሲሉ ተስተዋሉ፡፡ አቲታቸውን ነው የወሰደው፡፡

እነሆ ጥቂት ቀናትም አለፉ፡፡ እንደገና ሌላ ወሬ ተሰማ፡፡ "ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በጠና ታመሙ" የሚል በመንግስት በኩል ትንፍሽ ባይባልም የተለያዩ መላ ምቶች ቀጠሉ፡፡ "በውጭ ሀገር ህክምና እየተከታተሉ ነው" ከሚለው ጀምሮ "ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል" እስከሚለው ድረስ ተወራ፡፡ የፖለቲካ ተንታኞችም "ኢትዮጵያ ከመለስ በኋላስ?" ወደሚል ክርክር ገቡ፡፡ በእርግጥም ጠ/ሚሩ እንደታመሙ ለመገመት የሚያስችሉ በርካታ ሁነቶች ነበሩ፡፡ መሞታቸውን ለማመን የሚያስችል ግን አንዳች ምልክት አልነበረም፡፡

ከላይ በጠቀስኩት የመላምት ትንተና ወዲያ ወዲህ የሚሉ ሃሳቦች ማሰሪያ ይኖራቸው ዘንድ ጆሮን ለመንግስት መስጠት ግድ ይል ነበር፡፡ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ፈጣን መግለጫ በማውጣት የሚታወቀው የአቶ በረከት ቢሮም ድምፁን አጥፍቶ ሰነበተ፡፡ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ እንዳነበብኩት በጠ/ሚሩ ህመም ዙሪያ አስተያየት እንዲሰጡ የተጠየቁት አቶ ሽመልስ ከማል ተበሳጭተው እንደተናገሩ በሚያሳብቅ መልኩ "ይሄ የኢሳትና የእሳት ወሬ ነው" ሲሉ አጣጣሉ፡፡ የሚወሩ ወሬዎች ሁሉ የይዘታቸው ስፋትና ጥልቀታቸው ይለያይ ይሆናል እንጂ ፍንጭ ሊሰጡ እንደሚችሉ እውነት ነበር፡፡ በተለይ እንደኛ ሀገር መረጃ የሚተላለፈው በብዛት "በአፍ" በሆነበት ሀገር የአቶ ሽመልስ መልስ እውነት ነው ለማለት የማይቻል ነበር፡፡

ይሄን ጽሁፍ እስከማሰናዳ ድረስ የአቶ መለስ ጉዳይ የተንጠለጠለ ነበር፡፡ የነበረው አዲስ ነገር ቢኖር ድምፁን አጥፍቶ የሰነበተው የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ድምጽ መሰማቱ ነበር፡፡ አቶ በረከት ከጠፉበት ዋሻ ብቅ አሉ፡፡ ናዳውን ለመግታት ይሆን? ግዴለም ይሁን ከንግግራቸው ጀርባ የተደበቁ እውነቶችን እንድናሸት ምክንያት ሆነውናልና ሰማናቸው፡፡

ሐሙስ ሐምሌ 12 ቀን 2004 ዓ.ም አቶ በረከት ስሞኦን የአቶ መለስን መታመም አስመልክቶ ግልጽነት የጐለውና የተድበሰበሰ መግለጫ ሰጡ፡፡ የአቶ በረከት መግለጫ በጉጉት የተጠበቀ ቢሆንም ጥርጣሪዎችን ነፍስ እንዲዘሩ የሚያደርግ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ጥርጣሬው "ጠ/ሚሩ አርፈው ይሆን?" የሚል ነው፡፡ አቶ በረከት "አዎ አርፈዋል" ይሉናል፡፡ "ስራ በጣም ስለበዛባቸው በሐኪማቸው ትዕዛዝ መሠረት እረፍት ወስደዋል፡፡ ጊዜያዊ እረፍት ነው ወይስ ዘለዓለማዊ እረፍት የሚለው ግን ግልጽ አይደለም፡፡ (በነገራችን ላይ አቶ መለስ በህይወት ቆይተው ፓርቲያቸው ግን ቢሞት ይሻላል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሌለው ፓርቲያቸው መቀየር እንጅ የግለሰቦች መቀየር ትርጉም ላይኖራቸው ይችላል፡፡) ታዲያ አቶ በረከት ብዙ ግልጽ ሊያደርጓቸው የሚገቡ ጉዳዮች ነበሩ፡፡ በደፈናው "መለስ ህክምናቸውን አጠናቀው ወደ መደበኛ ስራቸው ይመለሳሉ" ከማለት ውጭ መቼ? እንዴት? የት ናቸው? የበሽታቸው ሁኔታ ምንድን ነው? የመሳሰሉ ዋና ጥያቄዎችን "አሁን መግለጽ አስፈላጊ አይደለም" በማለት ዘለዋቸዋል፡፡ የእነዚህ ወሳኝ ጥያቄዎች መዘለልም "ጠ/ሚሩ አልፈው ይሆን እንዴ?" ወደሚለው ጥርጣሬ ሊያደርሰን የሚሞክር ይሆናል፡፡

አቶ በረከት በመግለጫቸው የአቶ መለስን ወደ ስራቸው መመለስ የገለፁት በጥርጣሬ ነው፡፡ "በቅርቡ ወደ መደበኛ ስራቸው ይመለሳሉ ተብሎ ይጠበቃል" በማለት 30 ዓመት ሙሉ ያለ ዕረፍት በመስራታቸው ከዶክተሮቻቸው ምን ያህል ጊዜ ማረፍ እንደሚገባቸው በወራት ወይም በዓመታት ለክተው እንደሚነግሯቸው ይጠበቃል፡፡ ታዲያ አቶ በረከት ዕረፍታቸው ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ አያውቁም ለማለት አይቻልም፡

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

# የዛገው ሥርዓት ያረጁ ታክቲኮች ወደ ሙስሊሙ?

ሲራጅ ዘይኑ

ከምንም በላይ አስቀድሜ ሙስሊምና ክርስቲያን ወገኖቼን ጤናይስጥልኝ፤ ማለት ይኖርብኛል፡፡ ከሁልግዜውም በበለጠ ዛሬ ላይ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ጤንነት የምንጨነቅበት ጊዜ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አየር ላይ የሚነፍሰው ነፋስ ፍፁም ጤና ርቆታል፡፡ ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች "በሽብርተኝነት" እየተፈረጁ መታሰር፣ የነዋሪዎች መፈናቀል፣ የመምህራን ጉዳይ፣ የዋልድባው አለመግባባት፣ የአቶ መለስ ዜናዊ መታመም ወዘተ ቅርብ በሚባል ጊዜ ውስጥ ሀገሪቱን የተቆጣጠሩት ርዕሰ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አሁን ግን ከምንም በላይ አየሩን ከመቆጣጠሩም ባለፈ የተለየ አቅጣጫን እንዲይዝ እየተደረገ ያለውና የሚራገበው የሙስሊሞች ጉዳይ ነው፡፡ እኔም ዛሬ ከዚሁ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች የትኩረቴ አቅጣጫ ይሆናሉ፡፡

ወደ አብይ ነጥቦቼ ከመግባቴ በፊት ከራሴው ጋር በተያያዘ አንዲት ነገር ማለት ፈልጊያለሁ፡፡ በተለይ ከስሜ ጋር በተያያዘ፡፡ ስሜን ስታነቡት ቀድሞ ጥሩ ሙስሊም ልመስላችሁ፡፡ ግን አይደለሁም፡፡ ስሜ የከበደኝ ሰነፍ ሙስሊም ነኝ፡፡ ብዙም ጊዜ ወደ መስጅድ መሄድ የማላዘወትርና መሰረታዊ የሆነውን አምስት ወቅት ሶላት እንኳን በአግባቡ የማልሰግደው ሲራጅ ዘይኑ ነኝ፡፡ ዛሬ በምፅፍበት ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረጌም ሰው ከመሆን እንጂ ሙስሊም ከመሆን የመጣ አይደለም፡፡ ይልቅ በዙሪያዬ ካሉ ክርስቲያን ጓደኞቼ የተጋባብኝ ስሜት ነው፡፡

## ዛሬ እና መነሻዎቹ

የሙስሊሙ ማህበረሰብ ጥያቄ "እየመራን ያለው ተቋምና ሀላፊዎች ትክክለኛ ሙስሊሙን የሚወክሉና እኛ የመረጥናቸው ስላይደሉ መሪዎቻችንን እኛው እንምረጥ፤ በሙስሊሙ ስር ያሉት ተቋማትም ነፃና ሃይማኖቱን በትክክል የሚወክሉ ይሁኑ" የሚል ነበር፡፡ ከአወሊያ የተነሳው ጉዳይ በጊዜ መብረድ ባለመቻሉ ጥያቄው አድማሱን እያሰፋ መጥቶ አሁን መጅሊሱ ላይ ደርሷል፡፡ እስካሁንም ግን ጥያቄዎች ምላሽ እያገኙ አይደሉም፡፡ ጥያቄዎቹ ምላሽ አለማግኘታቸው ብቻ አይደለም አሁን ላይ አነጋጋሪ የሆነው፤ ጥያቄዎቹን ለመመለስ እየተኬደበት ያለው መንገድ እንጂ፡፡ ጥያቄውን ያነሱ ሙስሊሞች "ጥያቄያችን የሃይማኖት በመሆኑ ምላሹም ሃይማኖታዊ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ምርጫውን መስጊድ ነው የምናካሂደው" ሲሉ በተቃራኒው የቆሙ ወገኖች ደግሞ ከመንግስት ጋር በመሆን "ምርጫው መካሄድ የሚገባው በቀበሌና ወረዳዎች ነው" እያሉ ይገኛሉ፡፡ በነዚህ የሁለት ወገኖች ጥያቄ መነሻነት የሚመዘዙት ነጥቦች በርካታ ናቸው፡፡ ምርጫው ከመስጅድ ውጭ መካሄዱ አግባብነት የለውም የሚሉ ወገኖች የሚያስቀምጡት ምክንያት ሀይማኖታዊ ትውፊቱን መጠበቅ አለበት የሚልና ትክክለኛውን የሀይማኖቱን መሪ ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ ትክክለኛ መንገድ መምረጥ የሚያስችለን ቦታ መስጅድ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ ውጪ ምርጫው በየቀበሌው ከተደረገ ግን በአዲስ አቁማዳ አሮጌውን ወይን ማቅረብ ነውና አይስማማም፡፡ መጅሊሱና በመጅሊሱ ዙሪያ ያሉ ወገኖች መንግስትን ጨምሮ ምርጫውን እደማያጭበረብሩት ህዝቡ ምንም ዋስትና የለውም፡፡

በሌላኛው ወገን "ምርጫው በየቀበሌው መካሄድ አለበት" ሲሉ ለሚያነሱት ጥያቄ እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት "ሴቶች በምርጫው መሳተፍ አለባቸው፡፡ በምርጫው ወቅትም የተሻለ ጥንቃቄ ለማድረግ አመቺው ቦታ ቀበሌ ነው" ይላሉ፡፡ አክለውም ከዘገዩ በኋላ ያመጡት ምክንያት በቀደመው የሀይማኖቱ ተከታዮች ዘመን ምርጫ ይካሄድ የነበረው መስጅድ አልነበረም የሚል ነው፡፡ ይህንን ምክንያት ደግሞ ሌሎች "እና ቀበሌ ነበር የሚካሄደው?" ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ በተጨማሪም "በሌሎች ሀይማኖቶች ውስጥ የሚካሄደው ምርጫስ በቀበሌ ነው እንዴ?" ይላሉ፡፡ በሁለቱ ወገኖች የሚነሱ ተያያዥ ጥያቄዎች እንዳሉ ሆነው ይህንን ውዝግብ ተከትለው የመጡት ነገሮች ናቸው ትኩረት የሳቡት፡፡

## ተንኳሹ ማነው?

ለወራት የዘለቀው የቃላት ውዝግብ ወደ መጠነኛ ጉሸሚያና አደባባይ ያመራው ባለፈው አርብ (ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም) ነው፡፡ በእለቱ ለተነሳው ግጭት መነሻ የሆነውም ሙስሊሙ ማህበረሰብ በአወሊያ ተገኝቶ በቀጣይ እሁድ ላሰበው የ "አንድነት ሰደቃ" ዝግጅት በሚደርግበት ወቅት የፀጥታ ሀይሎች ወደ ቅጽር ግቢው ዘልቀው ገብተው የተሰናዳውን ምግብና ከብት ለመውሰድ መሞከራቸው ነው፡፡ ይህ ሁኔታም እሁድ ተገናኝቶ ፀሎቱን ሊያደርስ የነበረውን ህዝብ አበሳጭቶ ያለ ወቅቱ አስነሳው፡፡ በወቅቱም በርካቶች ጉዳት ደረሰባቸው፤ የተቀሩትም ታሰሩ፡፡ እና አሁን ማነው ተተናኮሰ ሊባል የሚችለው? ደግሞ በማምለኪያ ቦታዎች ላይ የእምነቱ ተከታዮች የፈለጉትን ማድረግ እንዳይችሉ፣ ያለ ማንም ፈቃድ ስብሰባዎች እንዳያደርጉ የሚከለክል ህግ አለ? አደባባይ መውጣትና በየመስጅዱ በመሰብሰብ መካከል ያለው ልዩነትስ በውል ይታወቅ ይሆን? ምላሾቹን እናንተው አሰላስሏቸው፡፡

እኔን ይበልጥ ያስገረመኝ ሌላ ትንኮሳዎች ላንሳላችሁ፡፡ የመንግስትና የሚዲያዎች ትንኮሳ፡፡ መንግስት (ኢህአዴግ ብለው ይቀለኛል፡፡ መንግስትና ፓርቲ ተምታቷል፡፡) የመሰለውን ስትራቴጂ ያወርዳል፡፡ ሚዲያዎቹ ደግሞ ተቀብለው ያለምንም ጥያቄና ምክንያታዊነት ያቀነቅኑታል፡፡ በተለይ ሬድዮ ፋና እና ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፡፡ ውሸት በማምረት ከእግር ጥፍሩ እስከ አናቱ የተዘፈቀው አንድ ለእናቱ ዝነኛው የኢትጵያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኞችንና ፖለቲከኞችን በሽብርተኝነት ለማስፈረጅ ላይ ታች ሲል ከርሞ ሰሞኑን ፊቱን ወደ ሙስሊሙ መልሷል፡፡ በርትቶ እየገፋበትም ነው፡፡ በየእለቱ የሚያቀርባቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች ይዘት ሀገሪቱ ኢትዮጵያ መሆኗን እንድንጠራጠር የሚጋብዝ ነው፡፡ በቅርቡም ኢቴቪ ሰራሽ "ዘጋቢ ፊልሞችም" ለእይታ እንደሚበቁ ይጠበቃል፡፡ መገለጫው ነውና፡፡ ሬዲዮ ፋናም ቢሆን ከኢቴቪ ብዙ አይለይም፡፡ ጥሩ የማስመሰል ችሎታ ያለው አክሮባቲስት ጣቢያም እንደሆነ ይነገርለታል፤ ይዘፈንለታል፡፡ "ሚዛናዊ" ለመምሰል በእጅጉ ይጣጣራል፡፡ ሆኖም ግን እራሳቸው ያማረሩትን ህዝብ ከችግር ብዛት ነቂ አድርገው ቁጭ አደረጉት፡፡ እናም ፋና ወይም ኢቴቪ አንድ ነገር ሲጀምሩ እቺን ቁጨማ በሚል ቀድሞ ይጨርሰዋል፡፡ "ደግሞ ነገ ማንን ሲያስሩ ነው ይህን ፕሮግራም የሰሩት?" እያለም የጀመሩትን ድርሰት በብርሃን ፍጥነት ቀድሞ ይጨርሰዋል፡፡ እነዚህ የመገናኛ ብዙሃን ከሰሞኑ በሚያስተላልፏቸው ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ መልዕክቶች ቢጨመቁ ለምንድነው ተግባብታችሁ የምትኖሩት? ተጨራረሱ፤ ተራረዱ የሚሉ የተቀረው ህብረተሰብ ሽብርተኝነትን ቦምብን፣ ገጀራን፣ ወዘተ ከእስልምና ጋር እንዲያያዙ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ርዋንዳን የሚያስታውሱ ተንኳሽና ተናካሽ መልዕክቶች ስፍር ቁጥር የላቸውም፡፡

## የክርስቲያኑን ጥገኝነት ፍለጋ

የኢህአዴግ መንግስትን ባህሪ ጠንቅቆ ለተከታተለው ሲሰነጥቅና ሲከፋፍል የኖረ መንግስት መሆኑን አያጣውም፡፡ ብሔር

ወደ ገፅ 9 ይዞራል....

ቆይታ



የዛሬ እንግዳችን አቶ ጥላሁን እንደሻው ይባላሉ፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጂኦግራፊ የተመረቁ እና በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት በጋዜጠኝነትና በተለያየ ዘርፍ በኃላፊነት አገልግለዋል፡፡ በፖለቲካ ህይወት ደግሞ የደቡብ ህብረት ሊቀመንበር እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ዋና ፀሐፊ በመሆን አገልግለዋል፡፡ በአሁን ወቅት ደግሞ የግንባሩ ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠዋል፡፡ በመድረክ ዙሪያ ከባልደረባችን ብስራት ወ/ሚካኤል ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል፡፡

# እኛ የምንታገለው ለሥርዓት ለውጥ እንጂ ለግለሰብ አይደለም

➢ **በአሁን ወቅት መድረክ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ነው ያለው?**

በጥሩ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የተለያዩ ስድስት ፓርቲዎች በቅንጅት ነበር የምንሰራው፤ አሁን ግን በየፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ውሳኔ በኂላ ወደ ግንባር በመሸጋገር ሙሉ በሙሉ ወደ ትግበራው እየገባን ነው፡፡

➢ **መድረክን ወደ ግንባር ማሸጋገሩ ለምን አስፈለገ?**

የመጀመሪያው ቅንጅት ሲሆን ይሄ ጊዜያዊ ህብረት ነው፡፡ ለዚህም ከግንባር በፊት የነበረን የአብሮነት ስራ በቅንጅት ደረጃ ነው፡፡ ሄ ደግሞ ለፓርቲዎቹም ለሀገራችን ህዝብም መተማመንን አይፈጥርም፡፡ በቅንጅት የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ ባለፈው ከነበሩ ተሞክሮዎች አይተናል፤ ወዲያው ሲፈርሱም ታዝበናል፡፡ መድረክን ግን ከዛ በተሻለ መልኩ በሀገራዊ ጉዳይ የሚስማሙ ፓርቲዎች ለረጅም ጊዜ ተመካክረው ዳግም መፍረስ እንዳይኖር ዘለቄታዊ ጥቅም ባለው ሁኔታ ለመስራትና በህዝቡም እምነት የተጣለበት መስራት የሚችል ጠንካራ ድርጅት ስላስፈለገ ነው ወደ ግንባር የተሸጋገርነው፡፡ በዚህም ጠንካራ መተማመን ላይ የተመሠረተና ህዝቡን የሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ ትልቅ ራዕይ አንግቦ የተነሳ ነው፡፡ ቅንጅት ህጋዊ የምስክር ወረቀት የሌለው ሲሆን ግንባር ግን ዘለቄታዊ የምስክር ወረቀት ያስፈልገዋል፤ ስለዚህ በአብሮነት ቀጣይነት ያለው ስራ ለመስራት ግንባር አስፈላጊ ነው፡፡

➢ **ታዲያ ወደ ግንባር የሚደረገው ሂደት ለምን ዘገየ?**

ከጠቀሜታው አንፃር ዘገየ ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ለዘለቄታዊ ጥቅም ስንል አንድ ዓመት ሙሉ በደንቡና በፕሮግራሙ ዙሪያ ስንመካከር ቆይተናል፡፡ ፕሮግራምና ደንብ የእያንዳንዱ የመድረክ አባል ፓርቲ ፕሮግራምና ደንብ ታይቶና ታሽቶ ለሀገራችን ይጠቅማል ያልነውን ተስማምተንና ተማምነን ስለሰራን የዘገየን ይመስላል እንጂ ከዓላማው አንፃር አልዘገየንም፡፡ ሌላው የአባል ፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባኤ የግንባሩን ሂደት ማጽደቅ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም አመራሮች ተስማሙ ማለት አባላት ተስማሙ ማለት አይደለም፡፡ እርስ በርስ የተደደረገው ውይይትም ሰፊ ነው፡፡ በአጠቃላይ ጊዜ የወሰደ የመሰለው በአዲስ መልክ የተሰራው የመድረኩ ደንብና ፕሮግራም ማዘጋጀት ነው፡፡

➢ **አሁን የመሰረታችሁት ግንባር አስተማማኝ ነው እያሉኝ ነው?**

አዎ፡፡ ምክንያቱም የበሰለ ውይይት የተደረገበትና በጋራ መተማመን ላይ የተመሠረተ ነውና፡፡

➢ **የመድረክ ግንባር መሆን ከኢህአዴግ ግንባር በምን ይለያል?**

በአደረጃጀት ራሱ ይለያል፡፡ የመድረክ ግንባር አባል ፓርቲዎች የራሳቸው ህልውና ኖሯቸው በነፃነት ይንቀሳቀሱ የነበሩና ራሳቸው ተፈላልገው ለሀገራችን በመቆርቆር የፈጠሩት ግንባር በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡ ያኔ የነበራቸው ህልውና ዛሬም ቢሆን ይቀጥላል፡፡

የኢህአዴግ ግንባር ግን በህወሓት አደራጅነትና የበላይነት የተፈጠረ ስለሆነ ከህወሓት ውጭ ያሉ አባል ፓርቲዎች የራሳቸው ህልውና እና ነፃነት የላቸውም፡፡ መድረክ ጋር ግን ከዚህ የተለየ እንደሆነ ከላይ ጠቅሼልሃለሁ፡፡

➢ **ለህዝቡ የሚሰጠው የተለየ ጥቅም ምንድነው?**

ጠንካራ፣ የተሻለና አማራጭ ሆኖ መቅረብ፡፡ በዚህም ህዝቡን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ አመኔታን ያገኘ መሆኑን ማረጋገጥና የህዝብ ይሁንታና ድጋፍ ያለው ፓርቲ መፍጠር፡፡ ምክንያቱም ከተናጥል ትግል ይልቅ እንደ መድረክ ጥንቃቄ የተሞላበትና በመተማመን ላይ የተመሠረተ የፓርቲዎች ስብስብ ግንባር በመሆኑ ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡

➢ **መድረክ ካለው ስብስባና አቅም አንፃር የሚጠብቅበትን እንዳልሰራ ይነገራልና እዚህ ላይ እርስዎ ምን አስተያየት አልዎት?**

እሱ ላይ እኔም እስማማለሁ፡፡ የሚጠበቀውን ያህል ያልሰራነው አንዱ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በመተዳደሪያ ደንቡና ፕሮግራም ላይ እንዲሁም ተጨባጭ የሀገራችንን ሁኔታ በማጥናት ዘለቄታ ያለው ስራ ለመስራት ሰነዶችን ስናዘጋጅ ቆይተናል፡፡ ሌላው ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የሚፈጥረው ችግርም አንዱ ተጠቃሽ ነው፡፡

➢ **ወደፊትስ ምን ለመስራት አስባችኂል?**

ሊያስሩን የሚችሉ አስተማማኝ ሰነዶችን አዘጋጅተን ስላልጨረስን ባወጣናቸው ዕቅዶች መሠረት አሁን ወደተግባር እየገባን ነው፡፡ ይህ ማለት እስካሁን አልሰራንም ማለት ሳይሆን ወጥ በሆነ አደረጃጀት በመላ ሀገሪቱ ተገቢውን እንቅስቃሴ አላደረግንም ለማለት ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በኂላ በዕቅድና በሰነዶች ዝግጅት ላይ የምናጠፋው ጊዜ አይኖርም፡፡

➢ **በተለይ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መግለጫ ከመስጠት ባለፈ ወደ ህዝቡ ሰርፃችሁ አልገባችሁም ይባላል፤ እዚህ ላይ ምን ሐሳብ አልዎት?**

ይሄ ስህተት ነው፡፡ እኛ ከህዝብ ተነጥለን አናውቅም፤ እንደውም በገዥው ፓርቲ በአብዛኛው የሚፈፀሙ በደሎች በአባሎቻችን ላይ ነው፡፡ መግለጫውንም ቢሆን የምናወጣው አዲስ አበባ ያለነው አመራሮች በስማ በለው ሰምተን ሳይሆን በተጨባጭ በክልል እስከቀበሌ ባሉ አባሎቻችንና አመራሮች በሚሰጠን መረጃ ነው፡፡

እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት የመድረክ አባል ፓርቲዎች በመላው ኢትዮጵያ አሉ፡፡ ምናልባት አንዳንድ ቦታ በተለያየ ተጽዕኖ ቢሮ ባይኖር እንኳ አባሎቻችን ተደራጅተው ይመክራሉ፣ ይንቀሳቀሳሉ በአካባቢያቸው ያሉትን መረጃዎችን አጣርተው ወዲያው ይሰጡናል፣ በተጨማሪ እኛም አረጋግጠን ነው መግለጫ የምንሰጠው፡፡

➢ **ዓላማችሁና የመጨረሻ ግባችሁ ምንድነው?**

ህዝቡን የስልጣኑ ባለቤት አድርገን፣ በነፃነት እንዲደራጅ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ባለቤት ስለሆነ ሙሉ የመወሰን መብቱና ከሀገሪቷ የተገኘውንም ሀብት በአግባቡና በፍትሐዊነት እንዲጠቀም ማመቻቸት፡፡ ህዝቡም የፈለገውን መሪ በነፃነት እንዲመርጥ ፍላጐት ያለውም እንዲወዳደር የፖለቲካ መድረኩን ነፃ ማድረግ፡፡

በኢኮኖሚ ረገድም ህብረተሰቡ አቅሙ በፈቀደ ሁሉ ከየትኛውም የፖለቲካ ተፅዕኖ ተላቆ ሰርቶ ራሱን፣ ቤተሰቡንና ሀገሩን እንዲጠቅም ዕድሉን ከራሱ ከህዝቡ ጋር በመሆን መፍጠር፡፡

➢ **በአሁን ወቅት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተመርቀው ወደ "ኮብልስቶን" ስራ እንዲሰማሩ በተደረጉና በመንግስት ላይ ያላችሁ አቋም ምንድነው?**

በመጀመሪያ ደረጃ እኛ ዜጐችን ለሚጠቅም ማንኛውም ስራ ትልቅ ከበሬታ አለን፡፡ ነገር ግን ገዥው ኢህአዴግ በሚከተለው የተሳሳተ የትምህርት ፖሊሲ ይህ ዓይነት ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ሰሚ ብናጣም ቀድመን ተናግረናል፡፡ በአንድ በኩል በቂ የተማረ የሰው ኃይል የለንም እያልን በሌላ በኩል ደግሞ ከ15 ዓመት በላይ በትምህርት ያሳለፉ ዜጐችን በ15 ቀን አጭር ስልጠና ማንኛውም አነስተኛ የትምህርት ደረጃ ያለው ዜጋ የሚሰራውን እንዲሰራ ማድረግ ትልቅ የሀገር ሀብት ብክነት ነው፡፡ ምክንያቱም ዜጐች በትምህርት ቆይታ ከወላጆቻቸው ያውም ከድሃው ወገናችን የወጣው ገንዘብ የሀገር ሀብት ነውና፡፡ ተመራቂዎቹ ራሳቸው ሲማሩ ለኮብልስቶን ስራ ብለው ሳይሆን ያገኙትን ዕውቀት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በስራ ላይ ለማዋል ነው፡፡ አሁን ግን የተማሩትን በሙሉ ባዶ አድርጐ ወደሌላ ስራ ማሰማራት የሰው ኃይል፣ የዕውቀትና የገንዘብ ብክነት ነው፡፡

ሌላው አነስተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸውንስ የት ለማድረግ ነው? እነሱም ዜጐች እኮ ናቸው፡፡ የኮብልስቶን ስራ እራሱ ዘለቄታ ያለው ሳይሆን የአጭር ጊዜ ስራ ነው፤ ከዛስ አሁን ወደዛ የሚያሰማራቸውን ተመራቂዎች የት ለማድረግ ነው? እኚህ ወጣቶች የሀገር ሀብቶች ናቸው፤ ለሀገሪቱም ሆነ ለህዝባችን በተማሩበት ሙያ ቢመራመሩና ቢሰሩ ነው ጠቀሜታ ያለው፡፡ ይህን ለማድረግ የተሻለ የትምህርትና የማኀበራዊ ፖሊሲ ያስፈልጋል፤ ይሄ ደግሞ እኛ በጥናት የተደገፉ ፖሊሲዎች አሉን፡፡ በአጠቃላይ መንግስት በዚህ ላይ ትልቅ ስህተት ፈፅሟልና ፈቃደኝነቱ ካለ ሊታረም ይገባዋል፡፡

➢ **የሙስሊሙ ማኀበረሰብ ከመንግስት ጋር ያለውን ጉዳይ እንዴት አያችሁት? እዚህ ላይ ያላችሁ አቋም ምንድነው?**

ጉዳዩን እየተከታተልን ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታዎችን ግን አጣርተን ስላልጨረስን አቋም አልያዝንም፤ እያጠናን እና እየተከታተልን ነውና፡፡

በአጠቃላይ መድረክ በኃይማኖት ጉዳይ መንግስት ጣልቃ መግባት የለበትም የኃይማኖት ጉዳይ ለኃይማኖቱ ተከታዮችና ለሃይማኖት አባቶች መተው አለበት ብሎ ያምናል፡፡ የኃይማኖቱ ተከታዮች የሚመራቸውንም ቢሆን የኃይማኖታቸው ሥርዓት በሚፈቅደው ዶክተሪን መሠረት መሆን አለበት የሚል አቋም ነው ያለን፡፡ ነገር ግን የሃይማኖ አክራሪነት አለ ብሎ በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ እጅን ማስገባት አክራሪነት ይፈጥራል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም እኔ እስከሚገባኝ አክራሪነት ማለት "የእኔ ሃይማኖት ብቻ ነው ትክክል የሌላው ስህተት ነው" ብሎ የሌሎችን መብት መጨፍለቅ ነው፡፡ የሌሎችን መብት ሳይነኩ የራሳቸውን የኃይማኖት ሥርዓት አጥብቆ መያዝና ማወቅ አክራሪነት አይደለም፡፡

ስለዚህ በሃይማኖት ጉዳይ በህገመንግስቱ የተቀመጠው ህግ መከበር አለበት፣ እኔ በመረጥኩልህ ተመራ ማለት ህግን መጣስ ስለሆነም መቆም አለበት፡፡ በአጠቃላይ አንድ የሃይማኖት ተከታይ የሌላውን መብት እስካልነካ ድረስ በሃይማኖቱ ጉዳይ መንግስት መግባት የለበትም፡፡

➢ **መቼ ነው ወደ ህዝቡ ወርዳችሁ የምትሰሩት?**

እስከ አሁንም እየሰራን ነው፡፡ ነገር ግን በተጠናከረ መልኩ በመላው ሀገራችን ከአሁን ጀምሮ እንሰራለን፡፡ እዚህ ላይ ህዝቡም ተጨማሪ የራሱን ግብዓት እየሰጠ አብሮን በመሆን ሰብዓዊና ቁሳዊ ድጋፍ ሊያደርግልን ይገባል፡፡ ከዚህ በኂላ ህዝቡ በተጠናከረ መልኩ አብሮን እየታገለ ስንደክም ሊወቅሰንና ሊያርመን እንዲሁም ጥሩ ስንሰራ ሊያበረታታን ይገባል፤ ለውጡም ሆነ ውጤቱ የሁላችንም ነውና፡፡ ስለዚህ የበለጠ በተጠናከረ መልኩ እንድንቀሳቀስ ህዝቡ ደንባችንና ፕሮግራማችንን አይቶ አብሮን ሊታገልና የገንዘብም ድጋፍ ቢያደርግልን በአጭር ጊዜ ውጤታማ እንሆናለን ብለን እናስባለን፡፡

➢ **እየተሰደዱ ስላሉ ዜጐችና በውጭ ስለሚኖሩ ዜጐችን ምን ትላላችሁ?**

የዜጐቻችን በአሰቃቂ ሁኔታ በኮንቴይነር ሳይቀር እንደ ዕቃ እየታሸጉ መሰደድ የስርዓቱ ውጤት ነው፡፡ እዚህ ላይ የሚሰደዱ ወገኖቻችን ስደትን ምርጫቸው አድርገው በመንገድ ላይ ከመሞትና ከመሰቃየት ለዛ የዳረጋቸውን ስርዓት መቀየር ከሚሰሩት ጋር አብረው በመታገል በሀገራቸው ላይ በዜግነታቸው ኮርተው የፈለጉትን ስራ ለመስራት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ የራስንም ሆነ የቤተሰብን ህይወት ለመለወጥ ስደት ብቸኛው አማራጭ አይደለም፡፡

በውጭ የሚኖሩ ዜጐቻችንም የሀገራችን ጉዳይ እነሱንም ስለሚመለከት እዚህ ሀገር ቤት በችግር ውስጥም ሆነን አስከፊውን ስርዓት ለመቀየር ለምንታገለው የሚችሉትን የገንዘብ እና የእውቀት እንዲሁም የቁሳቁስ ድጋፍ ሊያደርጉልን ይገባል፡፡ አለበለዚያ የህዝባችን ስቃይ እየበረታ ሀገራችን ከአሁን በባሰ መጥፎ ሁኔታ ውስጥ ልትገባ ትችላለችና ሊያግዙን ይገባል፡፡

➢ **በመከላከያ ሰራዊትና በገበሬው ህይወት ዙሪያ ያላችሁ አቋምስ ምንድነው?**

እኛ ለመከላከያ ሰራዊታችንም ሆነ ለሌሎች የፀጥታ ኃይሎች ትልቅ ክበር አለን፣ የእኛው አብራክና ሀገራችንንና ህዝባችንን ከጠላት የሚጠብቁ እንቁ ልጆቻችን ናቸውና፡፡ ህዝቡ የተሻለ ኑሮ እየኖረ ከሀገሩ ሀብት በእኩልነትና ፍትሐዊነት እንዲጠቀም፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከሩ

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

# ኢህአዴግ ከፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ ኢትዮጵያን እንዴት እናውጣት?

በለጠ ጉሹ ወ/ሚካኤል

በኢህአዴግ ውስጥ እውነተኛ ሥልጣን ያለው ህወሓት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በሌላ በኩል ሻዕቢያ በህወሓት መሣሪያነት (አሽከርነት) ኢትዮጵያን ለመበዝበዝ እስካሁንም ድረስ ጥረቱ እንደቀጠለ ነው፡፡ ሻዕቢያ በአሥመራ፣ ኢህአዴግ በአዲስ አበባ ሥልጣን ከያዙ በኋላ፣ ለሰባት ዓመታት ያህል ሻዕቢያ በኢህአዴግ አጋፋሪነት የኢትዮጵያን ገንዘብና ሀብት ዘርፎአል፡፡ የአቶ መለስ መንግሥት ከኢትዮጵያ በጀት እየቀነሰ ለኤርትራ መንግሥት በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ሰጥቶአል፡፡ ኤርትራ ከተገነጠለች በኋላ የአሰብ ነዳጅ ማጣሪያ የሻዕቢያ ንብረት መሆኑ እየታወቀ ለማጣሪያው ጥገናና ማሻሻያ እየተባለ ከኢትዮጵያ በጀት በውጭ ምንዛሪ ጭምር ወጪ ተደርጐአል፡፡ የማጣሪያ አገልግሎት ክፍያም ተከፍሏል፡፡

የሻዕቢያ ወኪሎች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ብድር ተፈቅዶላቸው፣ ጤፍ፣ በርበሬ፣ ቡና ቆዳ፣ አጠና፣ ስኳር ወዘተ ከኢትዮጵያ ገበያ እየገዙ ወደ ኤርትራ አሻግረዋል፡፡ በተለይ ቡናውን መልሰው ወደ ውጭ ሀገር እየላኩ፣ የውጭ ምንዛሪ አግኝተዋል፡፡ ቡና የማታመርተው ኤርትራ በዓለም ገበያ በቡና ላኪነት እስከመታወቅ ደርሳ ነበር፡፡ በአዲስ አበባ በነበረው የኤርትራ ኤምባሲ ውስጥ የኢትዮጵያን ብር በውጭ ምንዛሪ እየቀየሩ የውጭ ምንዛሪውን ወደ አስመራ ይልኩ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የሻዕቢያው ኤምባሲ በኢትዮጵያ ትልቁ ጥቁር ገበያ ሆኖ ነበር፡፡ ለአሰብ ወደብ አገልግሎት ክፍያ እየተባለ፣ በብርና በውጭ ምንዛሪ አያሌ ገንዘብ ለሻዕቢያ ተሰጥቶአል፡፡

ኤርትራን እና ትግራይን አቀላቅለው አንድ ጠንከር ያለ መለስተኛ ትግረኛ ተናጋሪ ሀገር ለመመስረት ጫካ በነበሩበት ጊዜ በተዋዋሉት መሠረት ወያኔዎቹም/ኢህአዴጎቹ በበኩላቸው ከቀሩት የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ገንዘብና ሀብት ወደ ትግራይ ያሻጋግሩ ነበር፡፡ በአንፃራዊ መልኩ የተሻለ ለምነት ያላቸውን መሬቶች በኃይል ከጐንደር እና ከወሎ ክፍላተ ሀገር ወስደዋል፡፡ ከመሀል ሀገር ፋብሪካዎች እየተነቃቀሉ ወደ ክፍለ ሀገራቸው አጉዘዋል፤ ሌላም ሌላም ብዙ የሚያስተዛዝብ ነገር ሰርተዋል፡፡ ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለመቆጣጠር የሚያስችሏቸው ግዙፍ ኩባንያዎች (እነሱ ኤንዳውመንት ይሏቸዋል) አቋቁመው የብዝበዛ መረባቸውን በመላ ኢትዮጵያ ዘርግተዋል፡፡ ይህ ድርጊት በአንድ በኩል ከቀሩት የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ጋር ያላቸውን ትስስር በማጠናከሩ፣ የመገንጠል ስሜታቸውን ያቀዘቀዘው ይመስላል፡፡

በግማሽ ኤርታራዊው አቶ መለስ የትግሬኛ ተናጋሪውን ድጋፍ ስለሚፈልጉ ከኢትዮጵያ መንግሥት ዓመታዊ በጀት በፌደራል ደረጃ ከሚመደበው ገንዘብ ከፍተኛ መጠን በትግራይ ለሚገነቡ ትላልቅ መሠረተ ልማቶች በመመደብ፣ በአጠቃለይ "ለትግራይ ክልል" የሚደለደለውን በጀት (ከፌደራል እና ከክልል ድጐማ) ከፍተኛ ለማድረግ ጥረዋል፡፡ "በጦርነት ለተጐዱ" በሚል ሰበብም ለትግራይ ክልል አድሎአዊ የሆነ የበጀት አመዳደብ ስልት ተጠቅመዋል፡፡

ይህም ሆኖ፣ በህወሓት ውስጥ ሻዕቢያ ያለውን የበላይነት የሚቃወሙ የህወሓት ባለሥልጣኖች አንገታቸውን ቀና ቀና ማድረግ ጀመሩ፡፡ እነ አቶ ገብሩ አስራት ከኢትዮጵያ በትግራይ በኩል ወደ ኤርትራ የሚሻገረውን ሀብት ለማስቆም እርምጃ መውሰድ ጀመሩ፡፡ "ሻዕቢያ በኢትዮጵያ ላይ ላካሄደው ወረራ ዋናው መንስኤ ኢኮኖሚያዊ ነው" የሚባለው ከዚህ ክስተት በመነሳት ነው፡፡ በሁለቱ ሀገሮች መካከል የተፈጠረው ውጥረት እየጨመረ በመሄዱ የኤርትራ መንግሥት በኢትዮጵያ ብር መጠቀሙን አቁሞ፣ ናቅፋ የሚባል የራሱን ገንዘብ አሳተመ፡፡ ይህ እርምጃ እስከ ተወሰደበት ጊዜ ድረስ በኤርትራ ኢኮኖሚ ውስጥ የተከማቸውንና የሚዘዋወረውን የኢትዮጵያ ብር ተፅዕኖ ለማምከን የኢህአዴግ መንግሥት በነባሮቹ የብር ኖቶች ላይ መጠነኛ ለውጥ በማድረግ አዲስ ገንዘብ አሳትሞ አወጣ፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ፣ ሻዕቢያ ኤርትራ ውስጥ በነበረው የኢትዮጵ ብር ተጠቅሞ ከፍተኛ ሀብት ከኢትዮጵያ መዝረፍ በቻለ ነበር፡፡

ይሁንና በህወሓት ውስጥ የተደበቁ ኤርትራውያንና ከፊል ኤርትራውያን በኤርትራ ኢኮኖሚ ውስጥ የነበረው የኢትዮጵያ ብር ወደ አሜሪካ ዶላር እንዲቀየርና ለሻዕቢያ እንዲሰጥ ሞክረው ነበር፤ ግን ይህም ሴራ ኢትዮጵን በሚወዱ ህወሓቶች ከሽፎአል፡፡ ሻዕቢያ በዚህ ሁሉ ተናዶ፣ ባድሜን ወረረ፡፡ ወረራውን በመቀልበስ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን እንዳታስከብር የእነ አቶ መለስ ቡድን "ሰላማዊ ድርድር" በሚል ሽፋን ከፍተኛ ጥረት አድርገው ነበር፡፡ ሆኖም "ለውጭ ተፅዕኖ አንበረከክም፤ በመልሶ ማጥቃት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እናስከብራለን" በሚል መርህና መፈክር እና አቶ ስዩ አብርሃ ወረራውን ለመቀልበስ ጦርነት አካሂደው አንፀባራቂ ድል አስገኝተዋል፡፡ ይሁንና እነ አቶ መለስ ከውጭ ኃይሎች ጋር በመተባበር በብዙ ህይወትና ሀብት መስዋዕትነት የተገኘውን ወታደራዊ ድል "በሕግ የበላይነት" ስም ወደ ሽንፈት ቀይረውታል፡፡ የእነ አቶ ስየ "አሰብን ይዘን እንደራደር" መፈክር ወደ የአልጀርሱ ስምምነት ቅሌት ተለወጠ፡፡ አቶ መለስ በዚህም አላቆሙም፤ እነ አቶ ስየን ከህወሓት እና ከሥልጣን አባረሯቸው፡፡ አቶ መለስ "በሕግ የበላይነት" ሽፋን ባድሜን ለሻዕቢያ አስፈረዱለት፡፡ ከዚህ በላይ ሻዕቢያነት (ኤርትራዊነት) ከወዴት ይገኛል?

አቶ መለስ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ በማድረጋቸው ኢኮኖሚያችን ከፍተኛ ችግር ገጥሞታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ በዓመት ከሁለት ቢሊዮን ዶላር ወይም ሰላሳ ስድስት ቢሊዮን ብር ያላነሰ ገንዘብ ለወደብ አገልግሎት በውጭ ምንዛሪ ለባዕዳን ትከፍላለች ይህ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደሀ ሆኖ መቀጠል ከፍተኛ አሉታዊ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ፣ በሀገሪቱ የውጭ ክፍያ ሚዛን ላይ (balance of phyments) ጉጂ ተፅዕኖ አሳድሮአል፡፡ ከኤርትራ ጋር ያለው ውዝግብ ባለመቋጨቱና እንዲሁም የኢህአዴግ የጉሣ ፖለቲካ ባስከተላቸው የእርስ በእርስ ግጭቶች ምክንያት ሀገሪቱ ለመከላከያ፣ ለደህንነት እና ለፖሊስ የምታወጣው ወጪ ከምንጊዜውም በላይ ንሮአል፡፡ እዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ፤ ኢህአዴግ በዓመታዊ በጀቱ ላይ የሚያወጣቸው አሓዞች በአብዛኛው በተጨባጭ ከሚወጡት ወጪዎች ጋር አይጣጣሙም፡፡ ለምሳሌ ኢህአዴግ በ2005 በጀት ውስጥ ለመከላከያ የያዘው ወጪ 6.5 ቢሊዮን ብር ነው፤ ግን በተጨባጭ ወጪ የሚደረገው የዚህ እጥፍ ሊሆን ይችላል፤ እንደሚታወቀው አቶ

ወደ ገፅ 12 ይዞራል....

# ክቡር ሚኒስትር እባክዎትን በአይ.ሲ.ሲ ንስሀ ሣይገቡ እንዳያርፉ

ግሩም አስፋው

በመሠረቱ ንስሀ ማለት ከሃይማኖት ጋር ተያያዞ የሚነሳ ቃል ሲሆን ለሰሩት ኃጢያት ቀኖና ወስዶ ንስሀ መግባት እና ለሠረጉ ኃጢያት ከፈጣሪ ዘንድ ይቅርታ ማግኘት ማለት ነው፡፡ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ማንኛውም ከ18 አመት በላይ የሆነ ሰው የንስሀ አባት (ቄስ) እንዲኖረው ግድ ይላል፡፡ ቀኖናውን የሚሰጡ እነሱ ናቸው፡፡ እንደ እ.ኤ.አ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ አይሲሲ (International Criminal Court) የተባለ የአምባገነኖች ንስሀ አባት ተመስርቷል፡፡ በዚህ ተቋም ውስጥ ብዙ ግፍ እና በደል ያደረሱ የተለያዩ ሀገር መሪዎች እና ሌሎችም በሰው ልጆች ላይ ሰቆቃ የሚፈፅሙ ግለሰቦች ንስሀ እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡ በተለይ አህጉራችን አፍሪካ በዚህ በኩል ተወዳዳሪ አልተገኘላትም፡፡ እንዲያውም የአይሲሲው ቄስ (ዳኛ) የንስሀ ቡራኬያቸው በአፍሪካ መሪዎች ላይ የጀመሩት ይመስለኛል፡፡ የቀድሞው የላይቤሪያው አምባገነን መሪ ቻርለስ ቴሌር ለሺህ ፐሩ መሣሪያ ነው፡፡ እና አልበሽር ዮሴፍ ኮኒ፣ እና ሌሎች ጨፍጫፊዎች ደግሞ አይሲሲ "ንስሀ ያስፈልጋቸዋል እና አቅርቡልኝ" እያለ ይገኛል፡፡ እስካሁን ቀርበው ንስሀ አልወሰዱም፡፡ አንዴ ተጠቃለን መውሰዱ ይሻላል ብለው ነው መሠለኝ፡፡ አንድ ቀን ቀርበው ንስሀ ሲወስዱ እናይ ይሆናል፡፡ ብዙዎች አይሲሲን በአፍሪካ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ሆን ተብሎ አፍሪካን ለመጉዳት የተቋቋመ የንስሀ መስጫ ድርጅት ነው በማለት ይወቅሱታል፡፡ በተለይም የአፍሪካ መሪዎች፡፡ ታዲያ አይሲሲ ለዚህ ወቀሳም ለመስጠት አልተቀጠበም፡፡ "በአፍሪካ ያሉ ቀሳውስቶች መሪዎቻቸውን ንስሀ ለመስጠት ብቃቱ የላቸውም፡፡ የሚሰሩት ሐጢያትም ቀሳውስቱ ከሚያውቁበት በላይ ነው፡፡ በዚህ ላይ የአፍሪካ ቀሳውስቶች በትምህርት ደረጃቸው ሳይሆን ቄስ (ዳኛ) የሚሆኑት ለመሪዎች ባላቸው ታማኝነት ንስሀ ስለሆነ ተገቢውን ንስሀ በተገቢው መንገድ እና ሰዓት ለአለቆቻቸው አይሰጡም" በማለት ነበር፡፡ አይሲሲ ምላሽ የሰጠው፡፡ እኔ በበኩሌ የአይሲሲ ምላሽ ትክክል ይመስለኛል፡፡ የኛ ሀገር ጳጳሳት ሼኮች እና ፓስተሮች የሚያደርጉት ለዚህ አባባሉ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡ ይቅርታ አድርጉልኝ እና የሃይማኖት መሪዎቻችን በቤተ ክርስቲያን እና መስኪድ ውስጥ ሳይሆን በብዛት የምናያቸው በኢቴቪ ነው፡፡ ጥቅሳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከቁራን ሳይሆን ከህገ መንግስቱ እና በየጊዜው ከሚወጡ አሳሪ አዋጆች ሆኗል፡፡

የድሮ የሀይማኖት አባቶች ለሀገራቸው ሲሉ ህይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ የአሁኖቹ ሀገር በመሸጥ፣ ከትርፍ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የቀድሞዎቹ ገዳማትን መሥርተዋል፣ ቤተክርስቲያናትንና መስጊዶችን አንፀዋል፡፡ የአሁኖቹ ገዳማትንና መድረሳዎችን በማፍረስ ፊት አውራሪ ሆነዋል፡፡ የቀድሞዎቹ በእግዚአብሔር መላዕክት ይጠበቁ ነበር፡፡ የአሁኖቹ በመንግስት ሠራዊት ይጠበቃሉ፡፡ ልዩነታቸው በጣም ብዙ ነው፡፡ ሁሉንም መዘርዘር አይቻልም፡፡ በአጠቃላይ ልዩነታቸው የመላዕክት እና የሰይጣን ያክል ነው፡፡

ከመስቀል ይልቅ ሽጉጥ መያዝ የሚያዘወትሩ የሃይማኖት መሪዎችም አሉ፡፡ በእርግጥ ሰውን እንደየ አመጣጡ እና እንደየ ምርጫው ለማስተናገድ ሊሆን ይቻለዋል፡፡ በእርግጥ ይህ ምዕመናን ግራ ሊያጋባው ይችላል፡፡ ጳጳስ እገሌ በማለት ፋንታ ሽጉጥ ይዞ ሲያየው ጀነራል እገሌ ማለቱ አይቀርም፡፡ ከህገ መንግስቱ አንፃር ሽጉጥ ቀርቶ መትረዬስ መያዝ መብታቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር ትክክል ሳይሆን ብችልም፡፡ ቢበዛ እንደ አለቆቻቸው አንድ ቀን ንስሀ መውሰድ ነው፡፡ እ/ርም የኢትዮጵያ ህዝብም ይቅር ባይና መሐሪ ናቸው፡፡

ወደ ዋናው ነገር ስንመለስ በእርግጥ የኛው መሪ አይሲሲ ዘንድ ለመቅረብ የሚያበቃ ወንጀል ፈጽመዋል? ወደዚያ ከማለፋችን በፊት ወደ አይሲሲ ፊት ሊያቀርቡ የሚችሉ ወንጀሎችን International & law politics (p.250-252) ከተባለው መጽሐፍ ጥቂቶቹን እንመልከት፡፡

የዘርማጥፋት ወንጀል፣ ግድያ፣ የሰውን ዘር እንዲጠፋ ማድረግ፣ ባርነት፣ ሰዎችን አስገድዶ ከቀያቸው ወደ ሌላ ቦታ መውሰድ፣ ያለ ምክንያት ማሰር፣ ግርፋት፣ አስገድዶ መድፈር ወዘተ ናቸው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ወንጀሎች ሁሉ የኛ ጠቅላይ ሚኒስትር ያልፈፀሙት የለም፤ እንዲያውም ከዚህ በበለጠ ፈጽመዋል፡፡ እንዲያውም አይሲሲ ስለ እሳቸው ወንጀል ምርመራ ቢጀምር አሁን የሰጠው ዝርዝር ከፍ በማድረግ ሌሎች የወንጀል ዝርዝሮችን ይጨምር ነበር፡፡ ለምሳሌ ብንወስድ የዘር ማጥፋት ወንጀል ገና የገቡበትን ቤተ መንግስት በደንብ ሳያውቁት እና ሳይለምዱት ነው መፈፀም የጀመሩት፡፡ ከሩዋንዳ ባልተናነሰ መልኩ በተለያዩ ክልሎች በሚኖሩ አማራጮች ላይ (በተለይ በሐረር እና በአርሲ አካባቢ) ጅምላ ጭፍጨፋ አካሄደዋል፡፡

በጋምቤላ እና በሌሎች ማህበረሰቦች ላይ አሰቃቂ ጭፍጨፋ ተካሂዷል፡፡ ቀኑን ባላስታውሰውም በአሜሪካ ድምጽ የአማርኛው ፕሮግራም ላይ የጋምቤላ ክልል ፕሬዝዳንት ጭፍጨፋ እንዲካሄድ ያዘዙት ጠ/ሚሩ ናቸው ብለው መናገራቸውን የሚገልፅ ዜና ሰምቻለሁ፡፡ ግድያን በተመለከተ ብዙ ኦሮሞዎች ኦነግ፣ ሱማሌዎች ኦብነግ፣ አማራዎች ቅንጅት እና ግንቦት ሰባት እየተባሉ ተገድለዋል፡፡ አሁንም እየተገደሉ ይገኛሉ፡፡ ኢህአዴግን የጥይት ማለቅ እንጂ የሰው ማለቅ አያሳስበውም፡፡ ለዚህ ነው ምርጫ 97ትን ተከትሎ በተፈጠረው ብጥብጥ የተገደሉትን ሰዎች ኢህአዴግ "የጥይት ዋጋ ክፍላችሁ ነው አስከሬኑን የምትወስዱት" ያለው፡፡ ባርነት በኢህአዴግ ዘመን የኢትዮጵያውያን መጋለጫ ሆኗል፡፡ ሴት እህቶቻችን ወደ አረብ አገሮች ለባርነት እየሸጠ ይገኛል፡፡ አገር ውስጥ ያሉትም ቢሆኑ በቀጥታም ተገደውም ባይሆን በተዘዋዋሪ ኑሮ እያስገደዷቸው የጉልበት ብቻ ሳይሆን የወሲብም ባሪያ ሆነው ይገኛሉ፡፡ አስገድዶ መድፈር ድሮ በጫካ ውስጥ ነበር በአብዛኛው የሚካሄደው፡፡ አሁን ደግሞ በአለቆች ቢሮ ውስጥ ከድሮው በባሰ መልኩ ሴቶች ይደፈራሉ፡፡ እምቢ ካለች ከሥራ ልትባረር፣ ደሞዝ ሊቆረጥባት፣ እድገት እና የትምህርት እድል ላታገኝ ትችላለች፡፡ ኢህአዴግ ይህንን ለአለቆች ሆን ብሎ ያመቻቸላቸው ይመስል ብዙ አለቆች የሚሰሩት ቢሮ ሳይሆን በመኗሪያ ቤት ነው የሚመስለው፡፡ ከቁም ሣጥን ጀምሮ እስከ ዲኤስ ቲቪ ተሟልቷል፡፡ የሶፋዎች ስፋት ለመቀመጫ ብቻ አይመስልም፡፡

የአለአግባብ እስራት እና በሴቶች ላይ ስቃይ መፈፀም አይሲሲ ከዘረዘራቸው ወንጀሎች ውስጥ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በአግባቡ ከታሰረው ይልቅ ያለ አግባቡ እና በአጋጣሚ የታሰረው ሕዝብ ቁጥር ይበዛል፡፡ በአሸባሪነት ሰበብ እና በጉዳና ነውጠኝነት የሚታሰረው ሕዝብ የሀገሪቱ የቀን ተቀን ውሎ ሆኗል፡፡

ምን ይህ ብቻ፣ ከአገራቸው ተሰደው በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም ካያሉበት እየለቀመ ለማሰር ኢህአዴግ በየጊዜው ይዝታል፡፡ የዘመነ ኢህአዴግ ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም መኖር አይቻልም እንጅ ለእሥርስ ለአለም ህዝብ ትበቃለች፡፡ እሱ ተላልፎ ወደ አይሲሲ ቢ በሚሰጥበት ሰዓት ‹‹አሳልፋችሁ

ወደ ገፅ 15 ይዞራል....

# ‹‹የሚገርመው ባይፈርድባቸው ነበር›› !!!



ብዙአየሁ ወንድሙ

ባለፈው ሳምንት በእነ አንዱዓለም የክስ መዝገብ የተከሰሱ 24 ፍርደኞች አንድ አነስተኛ ጽሁፍ አቅርቤ ነበር:: በዚህ ጽሁፍ ለማሳየት የሞከርኩት የተወሰኑትን እስረኞች ሲያዙ የነበረውን ሁኔታ፣ ተይዘው ገና ምርመራው ሳይጠናቀቅ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍርድ፣ ፍ/ቤት ሳይወሰን የተሰራባቸውን ዶክመንተሪ ፊልም ለማየት ሞክረናል:: አንድ ሰው ፍ/ቤት እስኪፈረድበት ድረስ እንደ ንፁህ ሰው የመታየት መብት አለው፤ የሚለው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ተጥሷል:: ከተያዙበት ቀን ጀምሮ ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ተደርጓል:: በሌላ በኩል የቤተሰባቸውን የትግል አጋሮቻቸውንና የተለያዩ ሰዎችን ሐሳብ አካተው ጥፋተኛ አይደሉም በማለት የተስተናገዱበትን ሚዲያ እንደጥፋት ተቆጥሮ ተብጠልጥሏል:: በዛሬው ጽሁፌ በምርመራ ወቅት የነበረውን የፍርድቤት የጊዜ ቀጠሮ ድባብ በአጭር በአጭሩ እናስታውሰው::

መስከረም 3/2004 ዓ.ም አንዱዓለም፣ እስክንድር፣ ናትናኤል፣ "ለሽብር ተግባር ሲንቀሳቀስ ተያዙ" ተባለና በምሽት የዜና እወጃ ተነገረ:: በማግስቱ ከቤተሰብ ዛሬ በ8 ሰዓት አራዳ በሚገኘው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት እንደሚቀርቡ ተነገረን:: ዕለቱ መስከረም 4/2002 ዓ.ም መሆኑ ነው:: ሰሞኑን በድንገተኛ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው የጀርመን ሬዲዮ ጋዜጠኛ ታደሰ እንግዳው የሪፖርተር ጋዜጣ ጋዜጠኛ ታምሩ ጽጌና ከፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ቀድመን በሥፍራው ደረስን:: በርካታ የእስረ ቤተሰብና ጉዳዩን ለመከታተል የፈለጉ በርካታ ሰዎች በሥፍራው ተገኝተዋል::

እያንዳንዱ እስረኛ የሚቀርበው ለየብቻው ነበር:: በቅድሚያ የቀረበው ከሁለት ወር በፊት በጋዜጠኝነት ሞያው ዓለም አቀፍ ተሸላሚ የሆነው ጋዜጠኛና የፖለቲካ ተንታኙ እስክንድር ነጋ ነበር:: እስክንድር በአንድ ፒካፕ መኪና ውስጥ ብቻውን ተቀምጦ በቅርብ ርቀት አይን ለአይን ተጋጨን፤ የአንገት ሠላምታ ተለዋወጥን:: በዙሪያው ያለው ጥበቃ ከፍተኛ ነው:: እስክንድር በዚህ ዓይነት የመሣሪያ ብዛት ተከቦ ስመለከተው አስገረመኝ:: ምክንያቱ አንድ የማውቀው ጉዳይ ስለነበረ ነው:: ላካፍላችሁ፤ ጳጉሜ 3 ቀን 2003 ዓ.ም አንድ ሰው ይጠራኝና ‹‹ሚስጥር ልንገርህ›› ይለኛል:: ‹‹ምንድነው? ብዬ›› ስጠይቀው ‹‹ሰሞኑን ጋዜጠኞች ሊታሰሩ መሆኑን ሰምቼአለሁ፤ የነገረኝ አንድ የኢህአዴ ባለሥልጣን ነው›› በማለት እርግጠኛ ሆኖ ይነግረኛል:: ‹‹እነማናቸው ስማቸውን ነግሮሐል?›› ብዬ ስለው፤ ‹‹አዎ፤ እስክንድር ነጋ፣ ዳዊት ከበደ...›› በማለት የአንድ አራት ሰዎችን ስም ይነግረኛል:: ጉዳዩን አጣጣልኩትና ተለያየን::

ማታ ጋደም ካልኩ በኋላ ታወሰኝና አብሰለሰለኝ:: እነዚህ ሰዎች ከታሰሩ በኋላ ሰምቼ ነበር፤ ንቄ ትቼው ነው ብዬ ብል ጥሩ አይደለም ብዬ አሰብኩኝ:: የመረጃ ምንጬንም በማግስቱ ለእስክንድር ስልክ ደውዬ እፈልግሃለሁ አልኩትና ተገናኘን:: የሰማሁትን ሁሉ ነገርኩት፤ እስክንድር ምንም አልገረመውም:: የድንጋጤ ስሜትም አልፈጠረበትም:: በድረ ገፅ የምፅፈው ላያስደስታቸው ይችላል:: ከዚያ ውጭ "እኔ አንድም የፈጠርኩት ወንጀል የለም:: የምሸሽበት ምክንያትም የለኝም:: በስደት ፈረንጅ አገር መኖርም አልፈልግም:: እስከዛሬ 7 ጊዜ አስረውኛል:: አሁን ካሰሩኝ እንደማይለቁኝ አውቃለሁ:: በአገሬ ላይ ተቀምጬ የመጣውን ሁሉ እቀበላለሁ" ብሎ አለኝ:: እኔም አንድ ሸክም እንደወረደልኝ ቀለለኝ:: "እሱን እርሳው የዓመት በዓል ዋዜማ ልጋብዝህ" ብሎ ጋበዘኝና ተለያየን፤ ከዚያ በኋላ አልተገናኘንም፤ ከአምስት ቀን በኋላ መስከረም 3/2004 ዓ.ም ‹‹ታሰረ›› የሚል ዜና ሰማሁ:: አልገረመኝም:: በማግስቱ እንደ አንድ ከፍተኛ ወንጀለኛ በመሣሪያ ተከቦ ሳየው ከአንገት ሠላምታ በኋላ ተሳሳቅን:: ቀደም ሲል መረጃውን የነገረኝ ወዳጄ እንዳለኝ "ሆን ተብሎ ለአንተ እንዲነግርህ ተደርጐ እንደተነገረኝ የገባኝ እስክንድር ከታሰረ በኋላ ነው::" በማለት በመደነቅ በድጋሚ አጫውቶኛል::

በዚህ ዓይነት እጀባ የመጣው እስክንድር ከመኪና አውርደው ችሎት አቀረቡት:: ችሎቱን እንድንከታተል ብንጠይቅ ፖሊስ ከለከለን፤ እስክንድር ከችሎት ሲወጣ ሦስታችንም ጋዜጠኞች ዳኛው ፊት ቀርበን አቤቱታ አቀረብን:: ጋዜጠኞች መሆናችንን ገለፅን፤ ችሎቱ ውስጥ ገብተን ለመዘገብ ፖሊስ እንደከለከለን አስረዳን:: ዳኛው የጋዜጠኝነት መታወቂያችንን ተቀብለው ከረጋገጡ በኋላ "ፖሊስ ችሎት ገብታችሁ እንዳትዘግቡ የመከልከል ሥልጣን የለውም:: ፖሊስ ምን አገባው? መዘገብ የምትፈልጉትን ገብታችሁ መከታተል ትችላላችሁ" በማለት ብይን ሰጡን:: ቀደም ብሎ ቀርቦ ወደ ማዕከላዊ እስር ቤት ስለተመለሰው እስክንድር ጠየቅን:: "በሽብርተኝነት ተጠርጥሮ መያዙን፤ ፖሊስ ‹የምርመራ ጊዜዬን አላጠናቀኩም› በማለቱ የ28 ቀን ጊዜ ቀጠሮ መስጠቱን" ዳኛው ገለፁልን:: እጅ ነስተን ወጣን::

በሁለተኛ ደረጃ የአንድነት ፓርቲ ብሔራዊ ም/ቤት አባል የሆነው መምህር ናትናኤል መኮንን ቀረበ:: እኛም ተከትለን ገባን:: ፖሊስ "የሽብር ተግባር ለመስራት በማቀድ ላይ እንዳለ በቂ ማስረጃ እንዳለው እና በዚሁ ምክንያት መያዙን ለፍ/ቤቱ አስረዳ:: በመቀጠልም 28 ቀን ጊዜ ቀጠሮ እንዲሰጠው ጠየቀ:: ዳኛውም ናትናኤልን "ምን አስተያየት አለህ?" በማለት ጠየቀው፤ መምህር ናትናኤልም "በቂ ማስረጃ አለኝ ብለዋል:: ባላቸው ማስረጃ ለምን ክስ ከፍተው ፍ/ቤት አያቀርቡኝም:: 28 ቀን ጊዜ ቀጠሮ መጠየቅ ለምን አስፈለገ?" በማለት ጠየቀ:: ፖሊስ "ያላጠናቀኩት ምርመራ ስለአለ ያስፈልገኛል" በማለት ገለፀ:: ፍ/ቤቱም የፖሊስን ጥያቄ ስለአመነበት ለጥቅምት 2/2004 ዓ.ም ተቀጠረ:: በመቀጠልም ከምርመራ በኋላ ተፈተው የዐቃቢ ህግ ምስክር ሆኖ የቀረበው አሳምነው ብርሃኑ ቀረበ:: የ28 ቀን ቀጠሮ ተሰጠበትና ወጣ:: ሌላው ከምርመራ በኋላ የዐቃቢ ህግና ምስክር እንዲሁም የተከሳሽ መከላከያ ምስክር በመሆን የቀረበው ዘመኑ ሞላ ቀረበ:: እሱም በተመሳሳይ ሁኔታ የ28 ቀን ጊዜ እንዲያውም ቀጠሮ ተሰጥቶ ሄደ:: በመጨረሻ ሲጠበቅ የነበረው አንዱዓለም አራጌ ነበር:: የፍ/ቤቱ ግቢ በታሳሪ ዘመድ አዝማድና ቤተሰብ እንዲሁም በትግል እና በሞያ አጋሮቻቸው ተሞልቷል:: ወደ እስረኞቹ ማንም እንዳይቀርብ መሣሪያ ተደግኖአል:: በጥበቃ ላይ የነበሩት ፖሊሶች ሁሉንም በግቢው ውስጥ ያለውን በጥርጣሬና በጥላቻ እያመናጨቁ ከሥፍራው ያርቁ ነበር:: በዚህ ወቅት ሳይጠቀስ የማያልፍ ነገር ነበር:: በተለይ እስረኞችን የሚያመላልስ አንድ የሰቪል ልብስ የለበሰ የፖሊስ ባልደረባ በእስረኛ ቤተሰብ ላይ ሲፈጽም የነበረው ድርጊት ነው:: ‹ወደ እስረኞች አትቅረቡ፤ እስረኞቹን ሠላም አትበሉ፤ እነሱን አትመልከቱ›› ከሚለው ቁጣና ማመናጨቅ በተጨማሪ ጠጠር መወርወር፣ ምራቅ መትፋትና ከአንድ ህዝብ አብራክ የወጣ ሰው በተለይ የፖሊስን ሞያ የሰለጠነ በፖሊስ ሥነ ምግባር ታንፆ የወጣ የማይጠበቅ ነውረኛ ድርጊት ሲፈጽም ታይቷል:: ጉዳዩን በትግስት ይከታተሉ የነበሩ ሁሉ እንዳለ ሆኖ አንዱዓለም ዘግይቶ ታጅቦ ፍ/ቤት ደረሰ:: አሁን ከአሁን ከመኪና አውርደው ችሎት ያቀርቡታል ተብሎ ሲጠበቅ ተመልሰው ይዘውት ከግቢ ወጡ:: ሁሉም አዘነ፤ ‹‹ሌሎቹን አቅርበው እሱን ብቻ እንዴት ግቢ አድርሰውት ፍ/ቤት ሳያቀርቡት ይመልሱታል?›› በማለት መነጋገሪያ ሆነ:: ሁሉም የየራሱን ግምት ሰጠ:: "ምናልባት ደብድበውት ቤተሰብና ፍ/ቤት እንዳያውቅ ሊሆን ይችላል" በማለት አንዱ ሲናገር ሌላው ደግሞ "አትደናገጡ፤ አትናደዱ፤ ተረጋጉ:: እነሱ የፈለጉት እዚህ ከተሰበሰብነው ውስጥ ለምን እንዲህ ታደርጋላችሁ? እንዴት እንዲህ ይሆናል? ብለን እንድንልና ረብሻ እንዲፈጠር ከመሐላችን ሰው ለማሰር እየሰሩ ላለው ድራማ ማስመሰያና ማድመቂያ ፈልገው ነው:: ዝም ብለን ድርጊቱን እንከታተል" በማለት ሁሉንም አረጋጋው:: ግቢ የመጣው ሁሉም ስለሚተዋወቅ በጥቂት ደቂቃ መስማት የሚገባው በአጭር ደቂቃዎች ይደረሳል::

የአንዱዓለምን መምጣት ሲጠባበቁ የነበረው ዳኛ ስለዘገየባቸው መርማሪ ፖሊሱን አስጠርተው "የሚቀርብ እስረኛ አለ ብላችሁ አልነበረም እንዴ? የታለ? ለምን አታቀርቡትም? መሽ አይደለም እንዴ?" በማለት በቁጣ ይጠይቃሉ:: "እየመጣ ነው:: ተሽከርካሪ ተበላሽብን ነው አሁን ደርሷል::" የሚል ምላሽ ይሰጣል:: ወዲያዉኑ አንዱዓለም አራጌን መልሰው ይዘውት ይመለሳሉ:: ከመኪና አውርደው ችሎት አቀረቡት:: እንደሌሎቹ ሁሉ አሁንም ጋዜጠኞች ተከትለን ገባን:: "በምን እንደታሰሩ ያውቃሉ?" በማለት ዳኛው አንዱዓለምን ጠየቁት "በሽብርተኝነት ተጠርጥረህ ነው በማለት ፖሊስ ነግሮኛል" በማለት መለሰ:: "ፖሊስ የምትለው አለ" ዳኛው ጠየቁ:: "ምርመራዬን ስለአላጠናቀኩ የ28 ቀን ጊዜ ቀጠሮ ይስጠኝ" በማለት ጠየቀ:: ዳኛው አንዱዓለምን የሚናገሩት ነገር አለ?" ሲሉ ጠየቁ አንዱዓለምም "ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ የምናገረው ነገር አለኝ:: እየተወሰደ ያለው በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለማፈን የሚወሰድ ርምጃ ነው:: እኔም ለዚሁ ሰለባ ሆኜአለሁ:: ከእንግዲህ ወዲያ ፍ/ቤቱ የፈለገውን ሊወስድ ይችላል:: ሞትንም ጨምሮ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ" በመቀጠልም "ዳኛው በሚናገሩት እርምጃ መውሰድ ይቻላሉ:: ሆኖም ግን ፍ/ቤቱ የሚጠይቅዎት የእርስዎን መብት ለማስከር ነው:: ፍ/ቤቱን ሊያከብሩ ይገባል:: ፍ/ቤቱ በነፃ የዳኝነት ሥርዓት የሚያከናውን ነው::" በማለት ሲናገሩ በመጨረሻ አቶ አንዱዓለም "እንደዚያ ነው ብዬ አላስብም" በማለት ለፍ/ቤቱ መልሰዋል:: ዳኛውም የተጠየቀውን የ28 ቀነ ቀጠሮ ተፈቅዶ ለጥቅምት 2/2004 ዓ.ም በ8 ሰዓት ተቀጥሮ የመጀመሪያው ዕለት የፍ/ቤት ውሎ ተጠናቀቀ:: አንዱዓለም እንደአመጣጡ ታጅቦ ተመለሰ:: ታዳሚውም እንደየአመጣጡ ተበተነ::

ጥቅምት 2/2004 ዓ.ም በ8 ሰዓት የሚለውን የቀጠሮ ጊዜ ሁሉም በፕሮግራሙ አስቀምጦ ሲጠብቅ ቆየ:: አንዳንድ ቤተሰብ እኔ እነዚህን ሰዎች አላምናቸውም:: ሥራቸው እንደመንግስት ሳይሆን እንደ...ነው:: 8 ሰዓት ብለው 2፡30 ሊያቀርቧቸው ይችላሉ::" በማለት ተጠራጥረው ጥዋት 2፡30 ላይ ፍ/ቤት የሄዱ አሉ:: እኛ በፕሮግራማችን መሠረት ጥዋት ወደ የሥራችን ተሰማራን:: 2፡30 ላይ ከየአቅጣጫው ስልክ ጥሪ ደረሰኝ:: እስረኞቹ ፍ/ቤት ቀርበው እየተመለሱ ነው:: ሌላው ሰው ስለማይቀርብ ጋዜጠኞች ኑኑ ግቡ የሚል ነበር:: ለሦስት ሰዓት አስር ደቂቃ 12፡50 ጉዳይ ሲደርስ የዕለቱ ችሎት ተጠናቋል:: አንዳንድ ቤተሰብ እንዳሉት "የፍ/ቤቱ አጥር ሳይከፈት ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ ከጥዋቱ 1፡30 ጀምሮ ዳኛው ተሰይሞ እንድአለፈው አንድ በአንድ እያመላለሷቸው 2ከ30 ላይ ተጠናቀቀ" በማለት ነገሩን:: ጋዜጠኞች ተሰባስበን ዳኛው ዘንድ ቀርበን "ቀጠሮው በ8 ሰዓት ሆኖ ሳለ በምን ምክንያት ወደ ጥዋት ተዛወረ:: እንዴት ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ ችሎት ተሰይሞ ጉዳዩን ሊመለከት ቻለ? ምን ተወሰነ?" የሚሉ ጥያቄዎችን አቀረብን:: ዳኛውም ወቅቱ ዳኞች እረፍት ላይ ያሉበት ጊዜ ስለሆነ የሥራ መደራረብ አለ:: በዚሁ ሥራ መደራረብ ምክንያት ፖሊስ በጥዋቱ ፕሮግራም እንዲታይለት በመጠየቁ ሰዓቱን አሻሽለን ተመልክተናል:: ችሎቱ የተሰየመው መደበኛውን የሥራ ሰዓት ጠብቆ ከ2፡30 ጀምሮ ነው:: ፖሊስ የምርመራ ጊዜዬን አላጠናከኩም በማለቱ ተጨማሪ 28 ቀን ተሰቶታል:: የሚል መንፈስ የነበረው ነበር::

በዚህ መልክ ሲደረግ የነበረው የጊዜ ቀጠሮ ለ3 ጊዜ ተሰጥቶ በአራተኛ ዐቃቢ ህግ ክስ በመክፈቱ የክስ ሂደቱ ልደታ በሚገኘው ፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት መታየት ጀመረ:: በሚቀጥለው ሳምንት የክርክሩንና የፍርድ ሂደቱን ድባብ ለማሳየት እሞክራለሁ::

## የአደባባይ ምስጢሮች

### ‹‹ይሉሽን ብትሰሚ ገበያ ባልወጣሽ››

በቅርቡ የወጣ የፍትህ ጋዜጣን ሳነብ አንድ አስገራሚ ነገር አነበብኩ:: ፖሊስ ለፍትህ ጋዜጣ የጻፈው መሆኑ ነው:: የጽሑፍ ዓላማ ፍትህ ጋዜጣ ላይ የተሰራው ዜና እንዲስተባበልለት የሚጠይቅ ነው:: የማስተባበያው ይዘት በመገናኛ አካባቢ ፖሊስ በጎዳና ላይ ከነጋዴዎች ጋር ባደረገው ግጭት አንድ ሰው ተገደለ ተብሎ የተሰራው ዜና ሐሰት በመሆኑ የሞተ ሰው የለም፤ ‹‹የፖሊስን መልካም ዝና የሚያጎድፍ ስለሆነ እንዲስተባበልልን›› የሚል ይዘት ያለው ነው:: ዜናው በተሳሳተ መረጃ የተሠራ ከሆነ ቢስተባበል ተቃውሞ የለኝም::

እኔን ያስገረመኝ ‹‹የፖሊስን መልካም ዝና የሚያጎድፍ በመሆኑ›› የሚለው ቃል ነው:: የትኛው ፖሊስ ነው መልካም ዝና ያለው? ልዩ ኃይል የሚባለው? ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራን የሚመራው ፖሊስ? አዲስ አበባ ፖሊስ ወንጀል ምርመራን የሚያዘው ፖሊስ? በካድሬ፣ በደህንነት እና በዐቃቢ ህግ ትዕዛዝ የፈጠራ ክስ እየፈበረከ ተቃዋሚዎችንና ጋዜጠኞችን የሚያስረው ፓሊስ? ይኸ በየሠፈራችን የምናየው ፖሊስ ጣቢያን የሚያዘው ፖሊስ? በየቤተክርስቲኑ፣ በየመስጊዱ እንደማፍያ የእምነት ቦታዎችን የሚደፍረውንና፣ ወንጀል የሚፈጽመው ፖሊስ? ይኸ ንፁሐን ዜጎችን የሚደበድብ፣ እሰር ሲሉት የሚያስረው፣ በጥይት ምታ ሲሉት የሚመታ ፣ ግደል ሲሉት የሚገለው ፖሊስ? ነው ወይስ እኛ የማናውቀው ፖሊስ ነው መልካም ዝናው የሚጎድፈው? ለኢህአዴግ ሥልጣን በማገልገሉ በመንግስትና በኢህአዴግ ባለሥልጣናት የሚሞገሰው ፣የሚሞካሸውና የሚሻለው ህዝብ ላይ በሚፈጸመው ግፍና ሰቆቃ ደግሞ የሚፈራውና የሚጠላው ፖሊስ ነው? ወይስ ሌላ? ‹‹ይሉሽን ብትሰሚ ገበያ ባልወጣሽ !!›› የኪሊማንጃሮ ኢንተርናሽናል ድርጅት ሪፖርትን አልሰሙ ይሆን?

### እሱንም መዋሸት ጀመሩ!!

ሁለት ጓደኛሞች ቀን፣ ሰዓት፣ ቦታ ወስነው ለመገናኘት ይቀጣጠራሉ:: አንደኛው የራሱን ሰዓት ተመልክቶ በቀጠሮ ቦታ ይደርሳል:: ሌላው ደግሞ የራሱን ሰዓት እየተመለከተ ወደ ቀጠሮ ሰዓት የሚሄድበትን ጊዜ ያሰላል:: ቀድሞ የደረሰው በዘገየው ጓደኛው እየተበሳጨ ይቆያል:: ረጂም ደቂቃ በመቀመጡ ‹‹የተበሳጨው ከዚህ በላይ አልጠብቀውም፤ ይህን ያህል ያስቀመጠኝ ንቀት ነው!!›› በማለት ከመቀመጫው ተነስቶ ለመሄድ ሲል ሉላኛው በራሱ ሰዓት ጊዜውን ጠብቆ ሲመጣ በራፍ ላይ ይገኛሉ::

ሰልችቶት የተነሳው በጣም ይናደድና ‹‹እንዴት ብትንቀኝ ነው ይህንን ያህል የምታስቀምጠኝ›› በማለት ይቆጣል፤ ዘግይቶ የመጣው ሰዓቱን እያሳየው ‹‹ይኸው የመጣሁት ልክ በሰዓቱ ነው›› ብሎ ያሳየዋል:: እንዴት ተባብለው ሰዓታቸውን ሲያስተያዩ በመካከለቸው የሰዓት ልዩነት አለ:: በሰዓቱ የደረሰው ሰዓቱን የሞላው በቪ.ኦ.ኤ ሲሆን የዘገየው በኢቴቪ ነው:: በሰዓቱ የደረሰው ‹‹ሰዓትህን በምንድ ነው የሞላኸው?›› ብሎ ቢጠይቀው የዘገየው ‹‹በኢቴቪ ነው›› ይለዋል:: ‹‹እነሱ እንደሚዋሹ እያወክ እንዴት በእነሱ ትሞላለህ›› ብሎ ቢጮህበት ‹‹ዜናውንና ሌላ ሌላውን እንጂ ሰዓት አይዋሹም ነበር እሱንም መዋሸት ጀመሩ›› ብሎ አለ::

ምልከታ

# አቶ መለስ ሃኪም ይረፉ አላቸው፤ ህዝቡ ግን “ይረፉ” ካለ ቆይቷል!



አቤ ቶክቻው

ባለፈው ሳምንት አቶ በረከት ስምኦን መግለጫ ሰጥተው ነበር። በመግለጫቸውም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ህመመም በይፋ አምነዋል።

በነገራችን ላይ ጋዜጣዊ መግለጫው እየተሰጠ ድንገት ወደ አዳራሹ የመግባት እድል ቢያገኙ አቶ በረከት ስምኦን መሀል ላይ ቁጭ ብለው በግራ እና በቀኝ ጋዜጠኞች ከበዋቸው፤ ከጀርባቸው የአቶ መለስ እና የአቶ ግርማ ፎቶ ተሰቅሎ ሲመለከቱ ሃዘን ቤት የመጡ ነው የሚመስልዎ! ከሁለቱም ፎቶ ስር የሆነች ብልጭልጭ ነገር ቢሰቀልማ ፎቶግራፋቸውን እያዩ እንባዎ እርግፍ እርግፍ ሊል ይችል ነበር። የምር ግን ይሄ ፎቶ ሰቀላ ለማሟረት እንጂ ለወዳጅነት አይመስልም! እኔ የምለው አቶ ግርማንስ በቃ ረሳናቸው ማለት ነው!?

በነገራችን ላይ አቶ ሽመልስ ከማል ባለፈው ጊዜ ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መታመም ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ “ይሄ የኢሳት ወሬ ነው!” ብለው ነበር። ያን ግዜ ብዙ ሰው አልገባውም ነበር። ይሄ የኢሳት ወሬ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ የአቶ ሽመለስ አለቆች አቦይ ስብሐት እና አቶ በረከት ስሞንን መጠየቅ በቂ ነው። እነርሱ እንዳረጋገጡት ታድያ “የኢሳት ወሬ” ማለት ታማኝ ምንጭ ማለት ሆኖ እናገኘዋለን።

እኔ የምለው አቶ ሽመልስን ግን መንግስታችን እንዲህ መጫወቻ ያደረጋቸው በምን ጥፋታቸው ይሆን!? የሆነ ጊዜ “የአሜሪካን ድምፅን እኛ አላፈንም ኢህአዴግ እንዲህ አይነት አፈና ማድረግ ባህሪው አይደለም።” ብለው መግለጫ በሰጡ በስንተኛው ቀን አቶ መለስ “እሱን ዝም በሉት የአሜሪካን ድምፅን አፍነናል!” ሲሉ ተናገሩ። አሁን በቅርቡም “ስካይፒ ይከለከላል የተባለው ውሸት ነው።” አሉ አቶ በረከት ደግሞ ተነስተው “እሱ ምን ያውቃል ስካይፒንም ሆነ ሌሎች የኢንተርኔት ቴክኖሎጂዎችን እንቆጣጠራለን!” ሲሉ መግለጫቸውን ውድቅ አደረጉባቸው። ደግመው፤ “ጠቅላይ ሚኒስትሩ አልታመሙም!” አሉን ነገሩ ግን ወዲህ ሆነ... በጥቅሉ እርሳቸው የሚሰጡት መግለጫ ማላገጫ እንዲሆን ስለምን እንደተፈረደባቸው ግራ ያጋባል!

የሆነ ሆኖ መለስ አሁን ተይዘዋል። ከወዳጅነታችን የተነሳ “ተይዘዋል” አልን እንጂ እንደ አንዳንድ ወገኖች ብንሆን ኖሮ በቁጥጥር ስር ውለዋል” እንል ነበር። የህመማቸው መንስኤ ረጅም ጊዜ ያለ እረፍት መስራት መሆኑን ሀኪም ነገሯቸዋል። “ይረፉ” ሲልም አሳስቧቸዋል።

አሁንም ሌላ በነገራችን ላይ ህዝቡ መለስን “ይረፉ” ካላቸው ቆይቷል። በተለይ ደግሞ በምርጫ 97 “ብዙ ደከሙ ብዙ ለፉ! እስቲ ደግሞ ይረፉ” ብሎ ሊያሳርፋቸው ሞክሮ ነበር እርሳቸው ግን ምን ሲደረግ ብለው ይረፉ ያላቸውን ህዝብ ረፈረፉት።

ከዛ በኋላም አለም አቀፍ ተሸላሚው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፤ “ሌላ ምንም ምክንያት ሳያስፈልግ አቶ መለስ ያለ ምንም እረፍት ይሄንን ያህል ጊዜ መስራታቸው ብቻ ለኢህአዴግም፤ ለእርሳቸውም ሆነ ለህዝቡ በጎ ባለመሆኑ በቃዎ ሊባሉ ይገባል!” ብሎ ተናግሮ ነበር። ነገር ግን ይህንን ባለ በነጋታው የፖ`ሊስ ኮሚሽነሩ ጠርተው “ምን ሲደረግ እንዲህ ትላለህ... በዚህ የምትቀጥል ከሆነ ወዮልህ...! እኛ አንተን ማሰር ሰልችቶናል እስከዛሬ የደሃ ልጅ ነበር የምንደፋው አሁን ግን የመጀመሪያው አንተ ነህ!” አሉት። ልብ አድርጉ መለስ “ይረፉ” ባለ ነው ይሄ ሁሉ ዛቻ!

እዚህ ላይ የአሽሟጣጮች ስጋት ትመጣለች

እነዚህ ሰዎች ሃኪሞችን በሙሉ “እንዴት ይረፉ ይሏቸዋል!?” ብለው እንዳይዘምቱባቸው ያሰጋል። ብለው የሚጠረጥሩ ሽሙጠኞች አይጠፉም።

የምር ግን ወዳጄ ህዝቡ በዘጠና ሰባት በቀልድ አድርጎ የተናገራትን እኮ ነው ዛሬ የቤልጄም ሃኪሞች እየነገሯቸው ያሉት። ባለፈው ጊዜ እነ ውብሸት ታዬ በተከሰሱበት መዝገብ ራሱ ዋና የክስ ማስረጃ የነበረው “መለስ በቃ” ብላችኋል የሚል ነበር። ዛሬ እነ ውብሸት “መለስ በቃ ይረፉ” ማለታቸው ስለተረጋገጠ ሽብርተኛ ናቸው ተብለው ታስረዋል።

ይኸው ዛሬም ሐኪሞቹ እያሉ ያሉት ይህንኑ ነው። “መለስ ሆይ ደክሞዎታልና በቃዎ!” ብለዋቸዋል ልዩነቱ በእንግሊዘኛ መሆኑ ብቻ ነው። እንጂ የቤልጄም ሃኪሞች “21 ዓመት ያለማቋረጥ መምራትዎ ነው ለዚህ የዳረገዎት እና ይረፉ” ማለታቸውን ራሳቸው ጓደናቸው አቶ በረከት ነግረውናል።

ይሄን ጊዜ አቃቤ ህግ ሀኪሞቹን በሽብርተኝነት ለመክሰስ እየተሰናዳ ይሆናል! ብለን እናላግጥ ይሆን!?

በመጨረሻም

እመክራለሁ!

ያለ እረፍት መስራት አዎ ያሳምማል። መለስ ባለማረፋቸው በቃኝ ባለማለታቸው ይኸው አንጉል ሆነዋል። በቀጣይም ራሱ ኢህአዴግ እረፍት እንዲያደርግ እመክራለሁ። አለበለዛ በእረፍት እጦት ሳቢያ የአልጋ ቁራኛ ቢሆን የማን ያለህ ይባላል!? ጎበዝ የግድ ሐኪም እስኪነግረንማ አንጠብቅ እንጂ!

# የዛገው ሥርዓት ያረጁ ታክቲኮች ...

ከ ገፅ 5 የዞረ....

ከብሔር፤ ደሃን ከሀብታም፤ የተማረውን ካልተማረው ወጣቱ ከተቀረው ማህበረሰብ ሙስሊሙን ከክርስቲያኑ ሲከፋፍልና ለመከፋፈል ሲባዝን ነው የኖረው። አሁን ደግሞ በሀይማኖቱ በኩል የመከፋፈሉን ስራ ሌት ከቀን ወጥሮ እየሰራ፤ እያሴረ ይገኛል። እስላሙን ከክርስቲያኑ እስላሙንም ከእስላሙ ለመለየት ቆርጦ ተነስቷል። ለዚህ የብጥበጣ ስትራቴጂው ማስፈፀሚያነትም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን እና ሬዲዮ ፋናን እየተጠቀመ ይገኛል። ሀብትና ብጥብጥ የሚያስነሱ መልዕክቶችን ሳይታክቱ በሆዳም ጋዜጠኞቻቸው አማካኝነት ይለፍፋሉ። አንዳንዴም ረቀቅ ያለች መንገድ ይሞክራሉ። ለዚህ ማሳያው የነገ ሳምንት በሬድዮ ፋና የተላለፈው ውይይት ጥሩ ማሳያ ነው። ከአወያዮቹ አንዱ አቶ ብሩክ ከበደ ይባላል። ታዲያ ይህ ሰው ስሙ ሀይማኖቱን አይገልፀውም። ሙስሊም ነው። ውይይቱን የመራውም ሆንብሎ የሙስሊሞችን ልብ በክርስቲያን ወንድሞቻቸው ላይ ጭካኔን እንዲያረግዝ በማሰብ እንደሆነ መገመት አይከብድም። ኢህአዴግ ጥቅም እስካገኘ ድረስ ምንም ነገር ከማድረግ እንደማይመለስ የቀደመው በሀሪው ያሳያል።

ውጤቱ ምንም ይሁን አሁን ኢህአዴግ የሙስሊሙን ድጋፍ እያጣው እንደመጣና ወደፊትም በበለጠ እንደሚያጣው እርግጥ ነው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ሙስሊሙ ለኢህአዴግ ጥሩ ስሜት እንዳለው ነበር የሚነገረው። እንደውም የቀደመውንና አሁን ያለውን ሁኔታ በማነፃፀር ቴዲ አፍሮ “ያኔ ሲነግረኝ ሰው ፈርቶ . . .” የሚለውን ዘፈን ሰኞ የዘፈነው የሚሉ ሙስሊሞች በርካታ ናቸው።

አሁን በሀይማኖት መካከል ልዩነት ፈጥሮ ከልዩነቱ በማትረፍ ከዚህ ቀደም ያኮረፈውን ህዝብ ክርስቲያን (በተለይ ኦርቶዶክሱን) ለመታረቅና ከነሱም ትርፍን ማግኘት ያሰበ ይመስላል፡፡ እንዲህ ያለው ሙከራ ግን ፍፁም አሁን ባለው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የሚሳካ ብቻ ሳይሆን ጭራሽ የሚሞከር አይደለም። እንዲህ ያለውን የኢህአዴግ ሙከራ ሳስብ ትዝ ከሚሉኝ ታሪኮች አንዱ የአባ ዶዮ ታሪክ ነው። አባ ዶዮ የጂጋማ ኬሎ የአጐት ልጅ ናቸው። በአንድ ወቅት ጣሊያን ሀገሪቷን ወሮ በኢትዮጵያውያን መካከል መከፋፈልን ለመፍጠር ሙከራ ያደርግ ነበር። በተወሰኑ ቦታዎች ላይም ብሔርን ከብሄር በማጋጨት ተሳካለት። ተራው ደርሶ ባላባቱ አባዶዮ በአካባቢው ሰው “አማራውን እናጥፋው” የሚል ጥያቄ ይቀርብላቸዋል። እሳቸውም በቅድሚያ ለመጡት ሽማግሌዎች በሙሉ አንድ እፍኝ ጤፍ ሰጥተው በሉ ጥቁሩን ከነጩ ለዩልኝ” አሉ። ቀጥለውም “አማራን እንግደል ብላችሁ አይደል የመጣችሁት፤ በሉ ሌላ ቦታ ከመሄዳችን በፊት የልጆቼን አንገት በመቁረጥ ጀምሩ። እናታቸው የመንዝ አማራ ናት እኔ ደግሞ ኦሮሞ” ብለው ነገሩን አረገቡት። ከዚህ ግዜ በሁላም የሰላም አባት ይባሉ ጀመር።

ይህ የአባ ዶዮ ታሪክ ብዙ መልዕክቶችን ተሸክሟል። እኔ ግን ሁለት ነገሮችን ልምዘዝ፡፡ አንድም የኢትዮጵያን ሙስሊምና ክርስቲያን መለያየት ጠፉን አማራና ኦሮሞውን የመለየት ያህል አንዳንዴም ከዛ በላይ ከባድ ነው። በማንም አቅምም የሚቻል ነው ብዬ አላምንም። በተወሰነ መልኩ እንኳን ቢሳካ ብለን ብናስበው ላነሳ የፈለኩትን ሁለተኛ ነጥብ ያመጣብኛል። እነ አባዶዮን ሊያፋጅ የነበረው የጣሊያን መንግስት ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ግን እንዴት በዜጎቹ ላይ ይህ እንዲሆን ይፈቅዳል? በዚህ ጊዜ ደግሞ የኢህአዴግ መንግስትን ከኢጣልያ መንግስት ጋር ለማነፃፀር እገደዳለሁ።

እግረ መንገዴንም አንድ ጽሁፍ ልጋብዛችሁ፡፡ መጽሐፉ ገበያውን እየመራ ያለው የመሀመድ ስልሣን “ፒያሳ መሐሙድ ጋር ጠብቂኝ” የሚለው ነው። ካላነበቡት ግድ የሎትም ያንበቡት፤ ብዙ ቁም ነገሮች አሉት። በተለይ ደግሞ “ኬ መንደፈር በመርካቶ” የሚለው ሀሳቤን ይበልጥ ያጠናክርልኛል። በላዩ ላይ ደግሞ የተወዳጁን ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ “ኬ መንደፈር” ሙዚቃ በማወራረጃነት ያዳምጡት። ኢትዮጵያውያን ምን ያህል የት ድረስ እንደተሳሰርን ያሳዩናል።

“ተዋዶ ያለበት እስላም ክርስቲያኑ

ተዘነጋሽ እንዴ ኢትዮጵያ መሆኑ

አንቺም በሃይማኖትሽ እኔም በሃይማኖቴ

መኖር እንችላለን አይጠበንም ቤቴ”

ይህንን ሙዚቃ በፆታዊ ፍቅር ከገደብነው ትልቅ ስህተት ነው። ቤቱም የአንድ ጉረምሳ ቤት አይደለም። ኢትዮጵያ ነች ቤታችን። ሁላችንም በየእምነታችን የምንኖርባት። ከክርስቲያን ጓደኞቻችን፤ ጉረቤቶቻችን ሚስቶቻችን፤ ፍቅረኞቻችን፤ ጋር የምንኖርባት ናት። እና ታዲያ እንዴት ልጃችንን፤ ጓደኞቻችንን፤ ሚስቶችንን እንገድላለን? ኧረ እንዴትስ ክፉአቸውን ችለን እናያለን? “የማይመስል ነገር” ነው ሚባለው፤ ለማንኛውም ይህንን ተረት ለፈጣሪዎቹ ትቼላቸዋለሁ። ከክርስቲያኑ የሚፈለገው ጥገኝነትም ሆነ ሁለቱን እምነቶች በማፋጠጥ የሚደረገው የእድሜ ማራዘሚያ የሚሳካ አይደለም። መሐመድ ሰልማን እንደሚለው በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል ያለው ግንኙነት በመቻቻል ብቻ የሚገደብ አይደለም። ከዚህ በእጅጉ የሚልቅ መዋደድ እንጂ። ከሰሞኑ በተነሳው ግጭት የተስተዋለው የቤቱና የየፌስቡኩ መደጋገፍ ማሳያም ይሄው ነው። ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ በባሰ ብስጭት ውስጥ ነበር።

## ያረጀው ያፈጀው ታክቲክ

የኢህአዴግ መንግስት በዙፋኑ ላይ ዝጐ ነው ያለው። ማርጀት፤ መበስበስ፤ አለመገለበጥ፤ አንድ አቅጣጫ ላይ ተተክሎ መቅረት መደንዘዝ ተመሳሳይ የእድሜ /የስልጣን/ ማራዘሚያ መንገዶችን መጠቀም፤ በኢህአዴግ መንግስት ላይ ዝገትን አስከትሏል። ያረጁና ያፈጁ ተግባሮች ደግሞ ከዝገት ሊያላቅቁ አይችሉም።

የምርጫ የመሬት፤ የንግድ የደህንነት፤ የፕሬስ፤ ህጐች በሙሉ ሲወጡ የመጀመሪያው አላማቸው ገዢውን ፓርቲ መጥቀም ነው። “ህግ ወጣ” ሲባል የኢትዮጵያ ህዝብ ቀድሞ “ፀደቀ” ይላል። መፅደቁ አይቀርማ መጀመሪያም ህጉ የወጣው ገዢውን ፓርቲ የሚጠቅም በመሆኑ ነው። “ፓርላማው” ደግሞ ሌላኛው የኢህአዴግ ምክር ቤት ስራው እጅ አውጥቶ አጨብጭቦ ማፅደቅ ነውና ስራውን ይሰራል። አሁን እነዚህ ሁሉ አሰራሮች ከህዝብ በታች ከፓርቲው ሰዎች አቅም በላይ የሆኑ የቀሽም ደራሲ ፈጠራዎች ሆነዋል።

በምርጫ 97 የተጠቀመውን ታክቲክ አሁንም በድጋሚ በሙስሊሞች ላይ እየተገበረው ይገኛል፡፡ በምርጫ 97 ወቅት ቅንጅት አዲስ አበባ ውስጥ ሀገር ሰላም ብሎ ተረጋግቶ ሲተኛ ኢህአዴግ ካድሬውን በየገጠሩ አሰማርቶ ህዝቡን ሲሰበስብ፤ ሰብስባ ሲያስወጣ፤ ሰልፍ ሲያስወጣ፤ አበሳውን ሲያሳየው ቆይቶ በመጨረሻ መሪዎቹን ሰብስቦ አሰረ።

አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ ይህንኑ በሙስሊሞቹ ላይ እየተጠቀመው ነው። እርምጃም መውሰድ ጀምሯል። ይህ እንደሚሆን ግን እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ታሳሪዎቹም ተራው ህዝብም አውቆት በፌስ ቡክ ሲቀባበለው ነበር፡፡ ህዝቡ ፓርቲውን ቀድሞታል። እውነታውን የሚውጡት ግን አይመስሉም።

የሆነው ሆኖ ግን ጉዳዩ ከሀይማኖት ባለፈ የመንግስት ጉልህ ፍላጐት እንደነበረበት ምልክቶች መታየት የጀመሩት ቀደም ብሎ ነበር። በየመስጅዱ የሚያሰግዱ የሀይማኖት አባቶች ከወራት በፊት በግዳጅ ተሰብስበው የቀን አበል እየተከፈላቸው የፓርቲው ዲስኩር ተደስኩሮላቸዋል። አሁንም የተጠየቀው ጥያቄ ሳይመለስ ፋሽን የሆነው “አሸባሪ” የሚለው ፍረጃ ቀድሟል። የመንግስትና ሰዎቹ ፍላጐትም ለተውኔታቸው በሚመቸው ቀበሌ ብቻ ምርጫው መካሄድ አለበት በሚለው አቋማቸው ፀንተዋል፡፡ እስካሁን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻ ያ ሁሉ ህዝብ ተሰብስቦ በሰላም ድምፁን አሰምቶ የሚለያይበት መንገድ መንግስት በፈጠረው የስጋት ሴራ ተተብትቧል። በመጅሊሱ ላይ ጥያቄ ያነሱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞችንም በውሀብይነት፤ በአሸባሪነትና በሩዝ የተታለሉ በሚል መንግስት እየፈረጀቸው በስህተት ላይ ስህተት መደረቡን ቀጥሎበታል። የረመዳን ፆም ከገባም ይኸው ዛሬ አምስተኛ ቀኑ ነው፡፡ ከቀደመው የዋልድባ ችግር ጋር በተያያዘ በየቤተክርስቲያኑ፤ በየመስጅዱ ይለቀሳል። እምባው ይጠርጋል ተብሎ ይጠበቃል። በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያን ከተጋረጠባት አደጋ ይታደጋታል። ለማንኛውም ግን ተግቶ መፀለዩ ሳያዋጣ አይቀርም። መልካም የረመዳን ወር ይሁንልን።

# እውነት እውነት እላችኋለሁ እውነት ታወጣችኋለች



ደረጀ መላኩ

**እህህ! እህህ**

**ዘንድሮ ዘንድሮ ዘንድሮ፤**

**የስንቱ ተወርቶ የስንቱ ተነግሮ!!**

አርብ ሐምሌ 6/2004 ዓ.ም ከማለዳው ጀምሮ በታላቅ ተመስጦ እና ሀዘን ውስጥ ነበርኩ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በታዋቂ የሠላማዊ ትግል አርበኞች እና በተቺ ጋዜጠኞች ላይ ይተላለፋል የተባለው የመጨረሻው ፍርድ የሚሰጥበት እለት በመሆኑ ነው፡፡ አንድ ወዳጄ ስልክ ደውሎ አቶ አንዱዓለም አራጌ በእድሜ ልክ እስራት፣ አለም አቀፍ እውቅና ያለው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በ18 አመት መቀጣቱንና እንዲሁም የሌሎቹንና ከሀገር ውጪ ያሉትንም ተከሳሾች ቅጣት በዝርዝር አረዳኝ፡፡ በእውነቱ ለመናገር ይከብዳል፡፡ ለሠላማዊ ትግሉ አራማጆችም ሆነ ለነፃው ፕሬስ ቤተሰቦች ታላቅ መርዶ ነበር፡፡

ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔውን ካስተላለፈ በኋላ "እሰይ አበጀህ" ብሎ ያመሰገነው ሀገርም ሆነ አለም አቀፍ ድርጅት እስአሁን አልተገኘም፡፡ በአንፃሩ ልእለ ሀያል ሀገር አሜሪካን ጨምሮ በርካታ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች በሰዓታት ውስጥ የተሰጠውን የፍርድ ውሳኔ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ አውግዘውታል፡፡

የልእለ ሀያል ሀገሯ አሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት አፈ ቀላጤ የሆኑት ሰው ለአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ የሀገራቸውን ትክክለኛ አቋም አሰምተዋል፡፡ በወቅቱ አሜሪካ ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ አቋሟን አሰምታለች፡፡ ነፃ ፕሬስን ማፈን መድበለ ፓርቲ እንዳይኖር ጉድጓድ መማስ፣ ቅጠል መበጠስ ተቀባይነት እንደሌለው በአንክሮ ተናግረዋል፡፡ ታላቋ አሜሪካ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በጣሙን እንዳስደነገጣት ከገለፀች በኋላ ታሳሪዎች የሚፈቱበትን ዘዴ መላ እንዲፈለግለት ገልፃለች፡፡

ሂዩማን ራይትስዎች፣ የአለም አቀፉ የፕሬስ ተቋም (IPI)፣ የጋዜጠኞች፣ መብት አስጠባቂ ተቋም (CPJ)፣ የአለም አቀፉ የሰብአዊ መብት አስጠባቂ ድርጅት (Amnesty international)፣ የኢትዮጵያውን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ክፉኛ ነው የኮነኑት፡፡

ዘግየት ብሎ ደግሞ የጀርመን የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የኢትዮጵያ መንግስት እስረኞቹን እንዲፈታ ጥሪውን አስተላልፏል፡፡ ለምሳሌ ያህል የ(IPI) ዋና ዳይሬክተር የሆኑት አሊሰን ቤተል ማሲኬንዚ (Alison Bethel Mckenzie) እንዲህ በማለት ነበር ሐዘናቸውን ለአለም የተናገሩ፡- "እኛ" አሉ ዳይሬክተሯ "በዓለም አቀፍ ደረጃ ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ላይ በሚደርሰው ሰቆቃ ምክንያት በከባድ ሀዘን ውስጥ እንወድቃለን፣ እስክንድር ነጋ እና በውጪ የሚገኙ የሙያ አጋሮቹ የተፈረደባቸው በጊዜው ያለውን መንግስት (The government of the day) በብእራቸው ክፉኛ ስለተቹት ነው፡፡" ብለዋል፡፡

የCPJ ምስራቅ አፍሪካ አማካሪ የሆኑት Tom Rhodes በበኩላቸው በስድስቱም ጋዜጠኞች ላይ የተሰጠውን ብይን ካወገዙ በኋላ "የፀረ አሸባሪነት ህጉ በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቀውን ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ ነፃነት እና በአፍሪካ ቀንድ የምትገኘውን ሀገር ህገ መንግስት ሳይቀር የሚፃረር ነው" ብለውታል፡፡ አክለውም "ፍርዱ የፍርድ ቤትን ታማኝነት ያሳጣል" ሲሉ ለአለም መገናኛ ብዙሃን ሰጥተዋል፡፡

አዲሱን የፀረ አሸባሪነት ህግ በተመለከተ ከረር ያለ ትችቱን የሰነዘረው የሰብአዊ መብት አስጠባቂው ድርጅት (Human rights watch) ነበር፡፡ ድርጅቱ በአፍሪካው ክፍለ አለም ምክትል ዳይሬክተር በሆኑት ሌስሌ ሌፍኮው (Lesle Lefkow) እንዲህ ሲሉ ለአለም ህዝብ ሁሉ ትችታቸውን አሰምተዋል፤ "በ24ቱ ሰዎች ላይ የተሰጠው ፍርድ የሚያሳየን ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ መንግስት የልስላሴ መጠን (liberalism) ትችቶችን እንኳን ለመስማት እንደማይፈልግ ነው፡፡

የድራኮኒያን ህግ በመጠቀም (the use of draconian laws) መሠረት አድርጎ ክስ መመስረት ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት የሚያጠፋና ሠላማዊ የፖለቲካ ትግልን የሚገድል ነው" ሲሉ ምሬታቸውን አሰምተዋል፡፡

ሌላው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት አስጣባቂ ድርጅት አምነስቲ ኢንተርናሽናል የአርቡን የፍርድ ቤት ውሳኔ በተመሳሳይ መልኩ ኰንኖታል፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ በተጨማሪ የጠቀሰው ነገር ቢኖር የሚከተለውን ነው፤ "የእስክንድር፣ አንዱዓለም እና የናትናኤል መታሰር የሚያሳየን ነገር ቢኖር የእነርሱን ዱካ የሚከተሉትን ሠላማዊ ታጋዮች ዝም ጭጭ ለማሰኘት ነው፤ ሦስቱም ሰዎች የህሊና እስረኞች ናቸው፤ የተከሰሱትና የታሰሩት በሠላማዊና በህጋዊ መንገድ ተንቀሳቅሰው መብታቸውን ስለጠየቁ ነው፡፡ ስለሆነም በአስቸኳይና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ" ሲል ለኢትዮጵያ መንግስት ተማፅኖውን አሰምቷል፡፡ በተጨማሪም ‹‹የኢትዮጵያ መንግስት ሠላማዊ የትግል እንቅስቃሴ የአሸባሪነት እንቅስቃሴ›› በሚል እየፈረጀ ከቀጠለ ጋዜጠኞችና የሠላማዊ ፖለቲካ ፓርቲ አባላት እንቅስቃሴን ህጋዊነት ያሳጣዋል" ሲል ስጋቱን ገልጿል፡፡

በመጨረሻም "የፍርዱ ሂደት በተለያዩ መንገዶች ሲፈተሽ አለም አቀፍ ደረጃውን መጠበቅ ያልቻለ በመሆኑ እስር ቤት የገቡት ተከሳሾች የፍርድ ሂደታቸው እንደገና እንዲታይ አሊያም ከእስር ነፃ እንዲወጡ" ሲል ለኢትዮጵያ መንግስት በድጋሚ ተማጽኖውን አሰምቷል፡፡

የአሜሪካው ስቴት ዲፓርትመንት በበኩሉ በሰጠው መግለጫ "ጋዜጠኞቹም ሆኑ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች የፀረ አሸባሪነት ህግ ተጠቅሶ መታሰራቸው አሜሪካን ክፉኛ ያሳስባታል፤ ከዚህ ባሻገር በርካታ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ያድርጋል፡፡ ለምሳሌ ያህል በኢትዮጵያ ህገ መንግስት በግልጽ የተቀመጡት ሀሳብን በነፃነት የመናገር እና የመፃፍ መብቶች እንዴት ሊከበሩ ይችላሉ? የሚሉ እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች እኛን ያሳስቡናል" ብለዋል፡፡ ግራም ነፈሰ ቀኝ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብቶች መድበለ ፓርቲ ስርአት በአንድ ሀገር ላይ እውን እንዲሆኑ ዋስ ጠበቃ ነኝ የምትለው ታላቋ አሜሪካ የምትወሰደውን እርምጃ በጊዜ ሂደት የምናየው ይሆናል፡፡

## እነማን ታሰሩ?

እንደ ጎርጎሮሳዊያኑ አቆጣጠር ከመጋቢት እስከ መስከረም 2011 ባሉት ወራት ከ119 በላይ የተቃውሞ ፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች እንደታሰሩ የአመንስቲ ኢንተርናሽናል መግለጫ ያወሳል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አባላት ይገኙበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አለም አቀፉ የሰብአዊ መብት አስከባሪ ድርጅት አምነስቲ ኢንተርናሽናል የሚያውቃቸው ከ200 — 300 የሚደርሱ የኦሮሞ ተወላጆች ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ወደ እስር ቤት ገብተዋል፡፡

እ.ኤ.አ ሰኔ 19/2011 የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ምክትል አዘጋጅ የነበረው ውብሸት ታዬ ወደ ዘብጥያ ተወረወረ፡፡ ይሄን ተከትሎ አስተማሪና የሳምንታዊው ፍትህ ጋዜጣ አምደኛ የነበረችው ርእዮት አለሙ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራቲክ ፓርቲ ፕሬዘዴንት ዘሪሁን ገብረ እግዛብሄር እንዲሁም ደጀኔ ተፈራ የተባለ የፓርቲያቸው አባል በሽብርተኝነት ተጠርጥረው ዘብጥያ ተወረወሩ፡፡

በ2011 ጁላይ 1 (አንድ) ላይ ደግሞ ሁለት የሲውዲን ጋዜጠኞች /ማርቲን ሽበዬና ጆህን ፐርሰን/ መታሰራቸው ይታወሳል፡፡ ጳጉሜ መባቻ (sept 14/2011) ሲሆን ወደ ዘብጥያ የተጋዙት አለም አቀፍ እውቅና ያለው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ የአንድነት ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አንዱዓለም አራጌ፣ የትግል አጋሩ ናትናኤል መኰንን እንዲሁም በመስከረም ወር ክንፈ ሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) እስረኞቹን ተቀላቀለ፡፡

## ሀሳብን በነፃነት መግለጽ እንደ ማስረጃ መቅረቡ

እንደ ማስረጃ ሆነው የቀረቡት በጋዜጣና በድረ ገፆች ላይ የቀረቡ ተቺ ጽሁፎች እንደነበሩ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች በጊዜው በሰፊው ሄደውበታል፡፡ ለምሳሌ ያህል በእነ ርእዮት አለሙ፣ ውብሸት ታዬ፣ ዘሪሁን ገብረ እግዚአብሄር ላይ ከቀረቡት 51 ማስረጃዎች ውስጥ 21ዱ የተወሰዱት ከአቶ ኤልያስ ክፍሌ ዌብ ሳይት ኢትዮጵያን ሪቪው ነበር (Amnesty international 2012)፡፡ እነ አንዱዓለምም ቢሆኑ አብዛኛው የቀረበባቸው ማስረጃ በማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ የሰጡት ቃልና ፍርድ ቤት መመላለስ ከጀመሩ በኋላ እንደነበር ከላይ የተጠቀሰው ድርጅት ይከራከራል፡፡

ከዚህ ባሻገር የፀረ አሸባሪነት ህጉ አንዳንድ አንቀፆች (አንቀጽ3፣5፣6 እና 24) ሰፊ ትርጉም እንዳላቸው የህግ ምሁራን የገለፁት ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ ለማሰርና ለፍርድ ለማቅረብ የነበረው ከፍተኛ ፖለቲካዊ ፍላጎት (high level political interest in the Arrests & trials) እ.ኤ.አ ኦክቶበር 2011 ዓ.ም የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ለፓርላማቸው ምክር ቤት ሪፖርት ካቀረቡ በኋላ በብቸኛው የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ የፓርላማ ተወካይ ክቡር አቶ ግርማ ሠይፉ ስለ ታሳሪ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ "እነርሱን ለማሰር ከበቂ በላይ ማስረጃ ይገኛል" በማለት የተናገሩትን እናስታውሳለን፡፡ አያይዘውም "ሌሎች ከፍተኛ አመራር አባላት (ያልታሰሩትን ማለታቸው ነው) ማስረጃ እየተፈለገላቸው ነው" በማለት ተናግረዋል፡፡ ይህ አባባላቸው፡፡ አገዛዙ ጠንካራ የሰላማዊ ፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ለማሰር ወደኋላ እንደማይል በገደምዳሜ ያመላከተ ነው፡፡

## ከፍርድ በፊት የተፈፀሙ ጥሰቶች

በብዛኛው የማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ እነ እስክንድር፣ አንዱዓለም እና ሌሎች በትግል አጋሮቻቸው እንዳይጎበኙ ተደርጓል፤ አቶ ዘሪሁን ገብረ እግዛብሄር ለሁለት ወራት ያህል በቤተሰቦቻቸው ሳይቀር እንዳይጠየቁ ተደርጓል (Amnesty international 2012 መግለጫ)፡፡ አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚሐብሄር፣ ውብሸት ታዬ፣ እና ናትናኤል መኰንን በማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ድብደባ (torture) ተፈፅሞባቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻግር ናትናኤል ለ23 ቀናት ያህል የተዛባ የእንቅልፍ ጊዜያት አሳልፏል (Amnesty international 2012 መግለጫ)፡፡

ከፍርድ በኋላ የሀገር ውስጥ ጋዜጦች ምን ዘገቡ?

ሳምንታዊው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ካፒታል የአንድነት ፓርቲ ምክትል ፕሬዜዳንት አቶ አንዱዓለም አራጌ፣ የቀድሞው አዲስ ዜና ጋዜጠኛ የነበሩት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እና ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የእድሜ ልክ እስራት ተበየነባቸው ካለ በኋላ እስክንድር ነጋ እና ሌሎች ጋዜጠኞ ከ8 -18 ዓመት የሚደርስ የእስር ቅጣት ተሰጣቸው በማለት ሰፊ ዜና አቅርቧል፡፡ የማክሰኞዋ አዲስ ፕሬስ በበኩሏ የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሳኔ ታላቋን አሜሪካ እንዳስደነገጠ ዘግባለች፡፡

በውስጥ ገፁ ላይ "በእነ እስክንድር ላይ የተሰጠው ፍርድ አለም አቀፍ አካላትን አሣስቧል" በማለት ያስነበበን ደግሞ ሰንደቅ ጋዜጣ ነበር፡፡ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ በርእሰ አንቀፃD ላይ "ታጋይን በማሰር ትግሉን ማሰር አይቻልም" ከሚል ርእስ ተነስታ ጠንካራ ትችቷን ካቀረበች በኋላ "አውቀን እንታረም" የሚል ምክሯን አስነብባለች፡፡

## እንደማጠቃለያ

"ውሸት ለመናገር አትሻም ምላሴ፣

ለእውነት እሞታለሁ አልሳሳም ለነፍሴ"

በማለት ከዝነኛው የክቡር ዘበኛ ኦኬስትራ ጋር በዘመን አይሽሬ እና ጥዑም ዜማው አንቆርቁሮልን እንዳለፈው ጋሼ ጥላሁን ገሠሠ እስክንድር ነጋ፣ አንዱዓለም አራጌ፣ ናትናኤል ሌሎችም በሠላማዊ የፖለቲካ ትግል የቆረቡ ለእውነት ሲሉ በእውነት ኑረው በእውነት ምክንያት ስቃይን የተቀበሉ የመከራን ገፈት ቀማሾች ናቸው፡፡ ትውልድ የነሱን አርማ አንስቶ ትግሉን ያፋፍማል እንጂ በነሱ ላይ በተፈረደው ፍርድ ተሸማቆ ወደኋላ የሚያፈገፍግ አይኖርም፡፡ ይልቁንም ትግሉ የበለጠ ይቀጣጠላል እንጂ፡፡ ፍርዱ የሞኞች ወይንም ያፋኞች ፍርድ በመሆኑ ማንንም አያስደነብርም፡፡ እንዲያውም ለእልህ የሚጋብዝ ነው፡፡ በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ ታጋዮች መስእዋትነት ሥልጣን ላይ የተቀመጡት መሪዎች ቢሰሙም ባይሰሙም የምሰጣቸው ምክር እባካችሁ ይህቺን በድህነት የተተበተበች ሀገር ሞቷን በሚመኙ ታሪካዊ ጠላቶቿ ጋር ሆናችሁ ውድቀቷን አታፋጥኑት፡፡ በባዶ በፕሮፓጋንዳ ብቻ "ህዳሴ፣ ትራንስፎርሜሽን" ቢሉት አይሆንም፡፡

የሠላማዊ ፓለቲካ ፊት አውራሪዎችና ትንታግ ጋዜጠኞችን ወደ ጨለማ ቤት በወረወራችሁ ቁጥር ለጊዜው ፋታ ያገኛችሁ ቢመስላችሁም፡፡ በህዝብ ዘንድ የነበራችሁ ተቀባይነት ክፉኛ እየተሸረሸረ እንደሚሄድ አትዘንጉ፡፡ ደሞም ይቺን አለም የጀመራት እንጂ የጨረሳት የለም፣ በዚች ምድር ላይ ውለን እናድራለን እንጂ ዘላለም እንደማንኖርባት የሚያወሳውን የአባቶች ብሂል ማስታወሱም ተገቢም ይመስለኛል፡፡

ለማንኛውም በፊደል አረቂ የሰከነውን እውቅ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ በማርቲን ሉተር ኪንግ ሠላማዊ የፖለቲካ ትግል የቆረበውን አቶ አንዱዓለም አራጌ እና ሌሎች የህሊና እስረኞችን እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ አንድ ቀን ከልዩ ክብር ጋር ነፃ ይወጣሉ፡፡ ለማንኛውም "ሲነጋ ሲል ይጨልማል፤ የኢትዮጵያን ትንሳኤ ለማየት ያብቃን"

"እኔ የሀገሬን መሪዎች እወዳለሁ፤ ከእናንተ በላይ ግን እውነትን እወዳለሁ፡፡" (ሦቅራጥስ)

# መድረክ ወደ ግንባር መሸጋገሩን አበሰረ

## - ግንባሩ አዲስ የአመራር አባላት መርጧል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ከቅንጅት ወደ ግንባር ተሸጋገረ፡፡ መድረክ ቅዳሜ ሐምሌ 14 ቀን 2004 ዓ.ም 6 ኪሎ በሚገኘው ዋና ጽ/ቤቱ ባደረገው ጉባኤ የግንባሩን መመስረት ይፋ አድርጓል፡፡ ግንባሩ የተመሰረተው በስድስቱ አባል የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲሆን እነኚህም አንድነት፣ ኦፌዴን፣ ኢሶዴፓ፣ ዓረና ትግራይ፣ ደቡብ ህብረት እና ኦህኮ ናቸው፡፡ በዕለቱ የመድረኩ አባል ፓርቲዎችም የግንባሩን መመስረቻ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡

ከዚህ በኋላም መጠሪያው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (መድረክ) የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ግንባሩ ወጥ የሆነ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም እንዳለውም ተገልፃDል፡፡ ምንም እንኳ ግንባሩ ወጥ የሆነ መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም ቢኖረውም እያንዳንዱ አባል ፓርቲ የራሱ ህልውና እንዳለውም ተጠቁሟል ።

በዕለቱ የግንባሩ አመራር አባላትም ተመርጠዋል፡፡ በዚህም መሠረት አቶ ጥላሁን እንዳሻው ሊቀመንበር፣ ዶ/ር መረራ ጉዲና ም/ሊቀመንበርና የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ፐ/ር በየነ ጴጥሮስ ም/ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣ አቶ ገብሩ አስራት ም/ሊቀመንበርና የውጭ ጉዳይ ኃላፊ፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ም/ሊቀመንበርና የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ ዶ/ር ሞጋ ፉሪሳ ዋና ፀሐፊ ሆነው ተመርጠዋል፡፡

ለኦዲትና ኢንስፔክሽን ደግሞ ወ/ሮ ላቀች ደገፉ ሰብሳቢ፣ አቶ ደስታ ዲንቃ ፀሐፊ እና አቶ ኡርጌሳ ዋኬኔ አባል በመሆን ተመርጠዋል፡፡ በመድረኩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የአዲሶቹ የግንባሩ አመራሮች የስራ ጊዜ አንድ ዓመት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

መድረክ ከዚህ በፊት በቅንጅት ይሰራ እንደነበር በማስታወስ ወደ ግንባር መሸጋገሩ ምን የተለየ ጥቅም አለው? በሚልና ሌሎች በርካታ ጥያቄዎች ከጋዜጠኞች ተነስቶላቸው የወቅቱ የመድረክ ሊቀመንበር አቶ ጥላሁን እንደሻውን ጨምሮ ሌሎች አመራሮችም ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በተለይ በቅንጅት በሚሰሩ ወቅት አንድ ውሳኔ ለማሳለፍ ከ6ቱ አባል ፓርቲዎች አንዱ ቢቃወም ተፈፃሚ አይሆንም ነበር፤ አሁን ወደ ግንባር ከተሸጋገረ በኋላ ግን ማንኛውም ውሳኔ በ2/3ኛ አብላጫ ድምጽ ተቀባይነት ካገኘ ያልፋል፡፡ በዚህም የጋራ መተማመን በመፈጠሩ የተሻለ ስራ እንድንሰራ ያደርገናል ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በዕለቱም የአቋም መግለጫ ወጥቷል፡፡

# “በመጪው አርብ ጋዜጣችን ለአንባቢያን ትደርሳለች በሚል እምነት በመስራት ላይ ነን” የፍትህ አዘጋጆች

## - ዛሬ ፍ/ቤት ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል

## - የስፖርት ጋዜጦችም ሳይሰራጩ ቀርተዋል

በማስተዋል ህትመትና ማስታወቂያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ዘወትር አርብ በየሳምንቱ የምትታተመው “ፍትህ” ጋዜጣ አርብ ሐምሌ 13 ቀን 2004 ዓ.ም ለአንባቢያን ትደርሳለች ተብሎ ቢጠበቅም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሳለች ታግዳለች፡፡

ጋዜጣዋ እስካሁን ለገበያ ያልቀረበች ሲሆን የጋዜጣዋ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ስለጉዳዩ ጠይቀነው አቃቤ ህግ ያገደበትን ምክንያት ትናንት ሰኞ ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ክስ ይመሰርታል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልፆልናል፡፡ ጉዳዩ የደረሰው ፍ/ቤትም በፕሬስ ህጉ መሠረት ክሱ በቀረበለት በ48 ሰዓት ውስጥ መርምሮ ዛሬ ማክሰኞ ሐምሌ 17 ቀን 2004 ዓ.ም ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የዝግጅት ክፍሉም የፊታችን አርብ ለአንባቢያን እንድትደርስ መደበኛ ስራውን እየሰራ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

በተለይ እንደ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ገለፃ ከሆነ የታገደችው ጋዜጣ ከተለቀቀች በቀጥታ ገበያ ላይ እንደምትውልና ለአንባቢያን እንደምትደርስ በተለይ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፃDል፡፡ የፍትህ ሚኒስቴር በበኩሉ ጋዜጣዋ የታገደችው ለማጣራት እንደሆነ በሌላ የመገናኛ ብዙኃን መዘገቡ አይዘነጋም፡፡ ይሁን እንጂ የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ የፍትህ ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑትን አቶ ደሳለኝን ስለጉዳዩ ጠይቀናቸው “ከመ/ቤቱ ድህረ ገጽ ባለጉዳዩ ማወቅ ትችላላችሁ፡፡” ቢሉንም ከተጠቀሰው ድህረገጽ ግን የተባለውን መረጃ ማግኘት አልቻልንም፡፡

በተያያዘ ዜና ባለፈው አርብ ለአንባቢያን የሚደርሱ ዘ-ገነርስ እና ሀትሪክ የስፖርት ጋዜጦች ሳይወጡ መቅረታቸው ታውቋል፡፡ እነኚህ የስፖርት ጋዜጦችን የሚያትመው ሆራይዘን ማተሚያ ቤትም ታሽጐ እንደነበር የተጠቆመ ሲሆን ጋዜጦች ታትመው ባለመሰራጨታቸው አሳታሚዎቹ ላይ ከፍተኛ የገንዘብ ኪሳራ መድረሱ ተጠቁሟል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፈው አርብ የነበሩት የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮና አልጀዚራ ስርጭት ጃም መደረጋቸውን አድማጮች ገልፀዋል፡፡

# በተቃውሞ የተሳተፉ ሙስሊሞች በጅምላ እየታሰሩ ነው ተባለ

በታላቁ አንዋር መስጂድ አካባቢ አካባቢ የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ በተቃውሞ እንቅስቃሴው ላይ የጎላ ሚና የነበራቸው የሀይማኖት አዋቂዎና በተቃውሞ የተሳተፉ ሙስሊሞች በጅምላ መታሰራቸው ተጠቆመ፡፡

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት መታሰራቸውን ተከትሎ በአንዋር መስጂድ ከሶላት በኋላ የተካሄደው ተቃውሞ ወደ ግጭት በመሸጋገሩ ፖሊስ በተቃውሞ የተሳተፉ ምዕመናንን በቁጥጥር ስር አውሏል፡፡ በእለቱ የተፈጠረው ግጭት በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ፖሊስ በምእመናኑ ላይ ድብደባ ማድረሱን የሚያሳዩ የቪዲዮ ምስሎችን አሳይተዋል፡፡ መንግስትም ግጭቱን ተከትሎ አክራሪ ያላቸው አካላት በመስጂድ የነበሩትን ምዕመናና አግተው እንደነበር አሳውቋል፡፡

የአይን እማኞች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ከታላቁ አንዋር መስጂድና አካባቢው የታፈሱት ሙስሊሞች ቅዳሜ 14 ቀን 2004 ዓ.ም ከምሽቱ 3፡00 ላይ በሰባት አውቶብስ ተጭነው ወደ ሰንዳፋ እየተወሰዱ መሆናቸውን ለፍኖተ ነፃነት አስረድተዋል፡፡

የእስልምና እምነት ተከታዮች የኢትዮጵያ መንግስት በእምነታችን ጣልቃ እየገባ በመሆኑ ከድርጊቱ ይቆጠብ በማለት ለሰባት ወራት የዘለቀ ተቃውሞ ውስጥ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሲቭል የለበሱ ፖሊሶች መስጊዶችን እየሞሉ በማስቸገራቸው ሙስሊሙ ነፃነቱን እያጣ መምጣቱ ተጠቁሟል፡፡ ለፍኖተ ነፃነት ምስክርነታቸውን የሰጡ አንዳንድ አማንያን እንደጠቆሙት ከሆነ ቅዳሜ 14 ቀን 2004ዓ.ም “አንዳንድ አክራሪ ሀይሎች በሰጋጆች ላይ እገታ ለመፈፀም ሞክረዋል” የተባለው በተቃራኒው መሆኑንና አጋቾቹም የሲቭል ልብስ የለበሱ ፖሊሶች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ጉዳዩን ከአዲስ አበባ ፖሊስ ለማጣራት ያደረግነው ሙከራ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት ኃላፊም ሆነ ተወካያቸው በስራ ላይ ባለመኖራቸው ሊሳካልን አልቻለም፡፡

# በደቡብ ክልል ተደራጅተው የሚሰሩ መበተናቸውን ገለፁ

በደቡብ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር በሚገኙ ቦንጋ፣ ሚዛን ተፈሪ፣ እና ቴፒ ከተሞች በመናኽሪያ ጫኝና አውራጅነት በማኅበር ተደራጅተው የሚሰሩ “በማናውቀው ምክንያት በትነውናል” ሲሉ ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡ ሰራተኞቹ የተበተኑበትን ምክንያት በአካባቢው የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላት መጠየቃቸውን አስታውሰው “ማኅበራችሁ እንዲፈርስ የተደረገው ክልሉ አዲስ አዋጅ በማውጣቱ ነው” የሚል ምላሽ እንደተሰጣቸው ጠቁመዋል፡፡

የማኅበራቱ ሰራተኞችም አሁን ለችግር መጋለጣቸውን በመግለጽ ቀደም ሲል በህጋዊ መልክ ፈቃድ አውጥተው እና የግብር መክፈያ መለያ እንዳላቸው አስታውቀዋል፡፡

ይህንንም ለማጣራት የአካባቢው መስተዳደር ጋር ተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም አልተሳካም፡፡ ይሁን እንጂ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት የክልሉ መስተዳደር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑትን አቶ ንጉሴ አስረስን ጠይቀናቸው በተጠቀሰው ጉዳይ መረጃ እንዳልደረሳቸው፤ ጠቅሰው “በማኅበር ተደራጅተው የሚሰሩትን እንዲጠናከሩ እንፈልጋለን እንጂ ተበተኑ የሚል የተላለፈ አዋጅም ሆነ መመሪያ የለም” ብለዋል፡፡

ተበደልን የሚሉ የማኅበሩ አባላትም ጉዳያቸውን የከተማ መስተዳድሩና ዞኑ መፍታት ካልቻሉ በቀጥታ ከክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ጋር መነጋገር እንደሚችሉ አቶ ንጉሴ ጠቁመዋል፡፡

# ሁለት መቶ ኢትዮጵያውያን በኮንቴይነር ተጭነው ከሀገር ሊወጡ ሲሉ ተያዙ

በአፋር ክልላዊ መስተዳደር ስር በሚገኘው ኤሊዳአር በሚባል ወረዳ 200 ያህል ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በኮንቴይነር ተጭነው ወደ ጅቡቲ ሲሄዱ አካባቢው በሚገኙ የፀጥታ ኃይሎች መያዛቸውን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

ስደተኞቹ የተያዙት ሐምሌ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ እንደሆነ፤ በነዋሪዎች ጥቆማ የፀጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ስር ማዋላቸው ተገልፃል፡፡ ይህንን በሚመለከት የአፋር ክልላዊ መንግስት የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ የሆኑት አቶ መሐመድን ጠይቀናቸው ስለ ጉዳዩ የደረሰን መረጃ የለም ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

# በቃሊቲ ወህኒ ቤት ድንገተኛ ፍተሻ ተደረገ

ባለፈው እሁድ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ድንገተኛ ፍተሻ መደረጉን ምንጮቻችን ጠቆሙ፡፡ እሁድ ድንገተኛ ፍተሻ እንዲደረግ ትእዛዝ የተላለፈው በታሳሪዎቹ ማደሪያና በግቢው ውስጥ ሲሆን ፖሊሶቹ በግቢ ያገኙትን ድንጋይ ለቅመው አስወግደዋል፡፡ እንደምንጮቻችን ገለፃ ፍተሻው የተካሄደው እሁድ ጠዋት ታሳሪዎቹ ለቆጠራ በወጡበት ሰዓት ነው፡፡ የቃሊቲ ምንጮቻችን ጨምረው እንደገለፁት ፍተሻው ታሳሪዎቹ ሳያውቁ ለማካሄድ የተሞከረ ሲሆን በታሳሪዎቹ ማደሪያ ውስጥ የተገኙ አንዳንድ ቁሳቁሶችም በፍተሻው ወቅት ተወስደዋል፡፡

ምንጮቹ የፍተሻው ምክንያት ምን እንደሆነ ተጠይቀው ምክንያቱን በትክክል መግለጽ ባይችሉም በሀገሪቱ ከተከሰተው የፖለቲካ ውጥረት ጋር በተያያዘ ሊሆን እንደሚችል አስረድተዋል፡፡ በፍተሻው ወቅት በተለይም ከሴቶች ማደሪያ ለመክተፊያ የሚጠቀሙባቸው ቆርቆሮዎችና ታኮ ጨማዎች ሳይቀሩ ተሰብስበዋል፡፡

# በጊዶሌ ተማሪዎች በግዳጅ አባል እንዲሆኑ እየተደረጉነው ተባለ

በደቡብ ክልል ደራሼ ልዩ ወረዳ በሚገኘው ጊዶሌ ከተማ በሚገኙ ሁለት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ዕድሜያቸው ሳይደርስ የዓመቱ የትምህርት መገባደጃ ላይ በግድ የኢህአዴግ አባል እንዲሆኑ እና ቅጽ እንዲሞሉ መደረጋቸውን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡ ተማሪዎችም ከአሁኑ የኢህአዴግ አባል ካልሆኑ ወደፊት ሥራ መያዝ እንደማይችሉ እንደተነገራቸው ተገልፃDል፡፡ በዚህም ተማሪዎች በግድ የኢህአዴግ አባልነት ቅፅ እንዲሞሉ መደረጋቸውን ወላጆች መቃወማቸው እና በዚህም ቅሬታ እንዳደረባቸው ተጠቁሟል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የልዩ ወረዳው መስተዳድር ቢሮ በጊዶሌ ከተማ የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን “ሐምሌ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የፖለቲካ ፓርቲ የጋራ ምክር ቤት ይቋቋማል፤ ለዚህም ከሐምሌ 13-18 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ እንድትመዘገቡ” የሚል ማስታወቂያ መለጠፉም ታውቋል፡፡

በወረዳው የሚንቀሳቀሰው የአንድነት ፓርቲ በበኩሉ በዚህ ላይ ቅሬታ እንዳለውና በዚህ ላይ የዋና ጽ/ቤቱን መመሪያ ተከትለው እንጂ በዘፈቀደ ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችል ገልፃDል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የወረዳው መስተዳድር አስተያየት እንዲሰጠን ተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም ስልካቸው ባለመስራቱ አልተሳካም፡፡

ነፃ ሐሳብ

# የኤርትራው "ሳዋ" እና የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች የማስመረቅ ሂደት


ክብሮም ብርሃነ (ከመቐለ)

የዛሬው ፅሁፌ አላማ በነባርና በአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን እንዲሁም በኤርትራ "ሳዋ" የሚሰጠው ትምህርት የሚመሳሰሉበትን ቁልፍ ነጥቦች ማሳየት ነው።

የሀገራችን ነባር ዩኒቨርሲቲዎች ከህዝባችን ብዛት አንፃር ሲታዩ በጣም አነስተኛ በመሆናቸው በየጊዜው እየተገነቡ ያሉ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ገንቢ ሚና እንደሚኖራቸው አምናለው። ዩኒቨርሲቲዎቹ አገልግሎታቸው ምን ይመስላል? ለሚለው ግን ኋላ እናየዋለን።

## የስጋችን ቁራጭ ኤርትራ "ሳዋ"

የኤርትራ መንግስት እንኳን አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች ሊገነባ ሀገሪቱ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ጊዜ የተገነባው አስመራ ዩኒቨርሲቲን እንኳን ዝግ አድርጐ 11ኛ ክፍል የደረሰ ኤርትራዊ ወጣት ሁሉ በግድ "ሳዋ" ወደ ተባለው ወታደራዊ ተቋም ገብቶ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ስልጠና እንዲወስድ እያስገደደ ነው። በዚህ በኩል ኢትዮጵያ በደምብ አድርጋ ትበልጣለች። ቢያንስ እየተገነቡ ያሉ ዩኒቨርስቲዎች አንድ ቀን ተልእኳቸውን በተገቢ መንገድ ይፈጽማሉ የሚል እምነትና ተስፋ አለኝ።

## የዩኒቨርስቲዎቻችን ተልእኮ ምንድነው?

ማንም ኢትዮጵያዊ ወላጅ ልጆቹ ዩኒቨርሲቲ የመግባት እድል ደርሷቸው ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲልኳቸው እነዛ ልጆች አእምሮአቸውን በጽንሰ ሀሳብ ዳብሮ በተግባር ብቁ ሞያተኛ ሆኖ በመውጣት የራሳቸው፣ ህዝባቸውና ሀገራቸው ችግር ፈቺና በህዝባቸውና ሀገራቸው በእጅጉ ተንሰራፍተው የሚታዩት ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተግዳሮቶች በየዩኒቨርሲቲው የቀሰሙት ፅንሰ ሃሳብና ያዳበሩትን ሞያ ተጠቅመው ያንዣበቡትን ችግሮች ለመፍታት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወስዱ በእጅጉ ይጠብቃሉ። ይሄ ደግሞ የወላጆች ብቻ ሳይሆን የመላው ዜጋ ተስፋ ነው። ይሄ ሆኖ እያለ ነባሮቹና አዲሶቹ ዩኒቨርሲቲዎቻችን አቅጣጫቸውን ስተው የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ችሎታ ቢስ፣ የገዥው ፓርቲ ጥገኛና በራሱ (በእውቀቱ) የማይተማመን (self confidence) የሌለው ትውልድ ሆኖ እንዲወጣ የዩኒቨርስቲዎቻችን ትልቅ ታሪካዊ ስህተት እየፈፀሙ ይገኛሉ።

ተቋማቱ የሚፈለገው እውቀትና ችሎታ አስይዘው ከመመረቅ ይልቅ የኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች ማለትም ህወሓት/ኢህአዴግ፣ ብአዴን/ኢህአዴግ፣ ኦህዴድ/ኢህአዴግ ወዘተ አባል እንዲሆኑና የነዛ ፓርቲዎችን መዝሙር እንዲዘምሩ በተዘዋዋሪ መንገድ እየተገደዱ ነው ያሉት።

አባል ካልሆኑ በዜግነታቸውና ባላቸው ችሎታ ብቻ ተማምነው ስራ የማግኘት እድላቸው በጣም የወረደ ነው። በየዩኒቨርሲቲው ለዚህ ስራ በተመደቡ ካድሬዎች ውስጥ ለውስጥ ይነገራቸዋል።

አስራስድስትና አስራሰባት አመታት ተምሮ የማኔጅመንት፣ የኢኮኖሚ፣ የአካውንቲንግ፣ የግብርና፣ የማርኬቲንግ፣ የህግ፣ የኬሚስትሪ ወዘተ ባለሞያ ሆኖም ቢሆን ሌላ ቢቀር በማህበር ተደራጅተን በኮብልስቶ (ድንጋይ ጠራቢነት) እንስማራ ቢሉ እንኳን በየክልላቸው የፓርቲውን አባል መሆን የግድ ይሆንባቸዋል። ድንጋይ በመጥረብ ለምን ያን ያክል አመታት መማር አስፈለገ? የሚለው ለናንተ እተዋለሁ። ስራ መናቁ ሳይሆን በማንም ያልተማረ ሰው ሊሰሩ አይችሉም ወይ? የሚለው ጥያቄ በደምብ እሰቡበት።

ለምንድነው ኢህአዴግ የተማረ ሁሉ የአንድ ፓርቲ አባልና በአንድ ሳንባ እንዲተነፍስ ደፋ ቀና የሚለው? ለምንድነው ኢህአዴግ አማራጭ ሃሳብና ፖሊሲ መስማቱ ያስጠላው? ይህ ከሆነ ኢህአዴግ "ከሻዕቢያ" በምን ይለያል? ሻዕቢያ ወጣቱ ትውልድ "ብረት ይዞ" የስርዓቱ ጠባቂና ዘበኛ እያደረገ ነው ያለው። ኢህአዴግ ደግሞ ብረት ባያስይዘውም ህወሓት፣ ኦህዴድና ብአዴን የሚል "ባጅ" (ቀይ ካርድ) በግዴታም በውዴታም አስይዞ የኢህአዴግ የበላይ ዘበኛ እንዲሆን ከ97 ዓ.ም ማግስት ጀምሮ ደፋ ቀና እያለ ይገኛል።

በአጠቃላይ ስናየው ኢህአዴግና ሻዕቢያ መንገዳቸው (ሲስተማቸው) የተለያየ ቢሆንም መድረስ የሚፈልጉት ግን ወደ አንድ አደባባይ ነው። ይሄውም ዜጐች የአስተሳሰባቸውን አድማስ በመጋረድ እንደ ጋሪ ፈረስ ከኢህአዴግ ጋር ወይም ከሻዕቢያ ጋር ወደ ፊት እንዲጓዝ በማድረግ የግዛት ዕድሜቸውን የማራዘሚያ መንገዳቸው ነው።

አሁን አሁን ግን የሁለቱ ሀገሮች ዜጐች የገዢዎቻቸውን ዓላማ በመረዳት መንገዱ የማያዋጣ መሆኑን ተረድተው ከመንገዱ እየወጡ ይገኛሉ። ለምሳሌ ትጥቃቸውን ጥለው በሰሜን በኩል ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ በየቀኑ እየገቡ ያሉ የኤርትራ ወታደሮች የዚህ አመላካች ሲሆኑ የህወሓት ብአዴንና ኦህዴድን አባልነት አንፈልግም ብለው የአባልነት ካርዳቸው እየመለሱ ያሉና ራሳቸው ካርዱ እየቀደዱ ያሉት ኢትዮጵያን በተለይ "መምህራን" በቁጥር ቀላል አይደሉም።

መምህራን የተለየ የራሳቸው ምክንያት አላቸው። ያ ደግሞ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው ነው። "ሞያችን ክብር ይሰጠው፣ በስራችን ተመጣጣኝ የሆነ ደሞዝ ይሰጠን፣ የስራ ነፃነት ይኑረን ወዘተ" የሚሉትን የመብት ጥያቄዎች በህጋዊ መንገድ በመጠየቃቸው የማይገመትና የማይታሰብ ስድብና ንቀት እንዲሁም ከስራ ማባረር እንደደረሰባቸው የትናንት ሐቅ ነው። ለነገሩ የራሳቸው (የመምህራኑ) ችግር ነው። ለምን ብትሉኝ "ድርብያብር አንበሳ ያስር" በዚህ አይገልጠውም? መምህር ማለት እኮ ወላጅ፣ እህት፣ ወንድም፣ እንዲሁም ተማሪ ነው። ይህንን የህብረተሰብ ክፍል አጠቃልሎ የያዘ አካል (ባለሞያ) በምን መልኩ ይፈራል? ይናቃል? እንኳን ሊሰድብና ከስራ ሊባረር ቀርቶ ያቀረበውን ህጋዊ ጥያቄ ሳይመለስ ሊባረር ቀርቶ ያቀረበውን ህጋዊ ጥያቄ ሳይመለስ አንድ ሌሊት ባላደረ ነበር። ግን ምን ዋጋ አለው መቸ አበረና።

ከአባልነት የመውጣት ሂደት ግን በተለይ በትግራይ ክልል (የትግራይ መምህራን) ማለቴ ነው በሚያስገርም ሁኔታ በድፍረት "አንፈልጋቹሁም" በማለት እየለቀቁ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ እንዳሉት በሆዳቸው የሚያስቡ "የስልጣን ተስፈኞች" የሉም ግን አልልም? በአጠቃላይ ተደምሮ ተቀንሶ የመጨረሻ ውጤት ግን ኢህአዴግ ማለት ሻዕቢያ፣ ሻዕቢያ ማለት ኢህአዴግ ናቸው። አብረው የመጡ፣ አብረው ያሉ፣ አብረው የሚታመሙ አብረው መቃብር የሚገቡ ናቸው።

# ኢህአዴግ ከፈጠረው የኢኮኖሚ ...

ከ ገፅ 7 የዞረ....

መለስ ዜናዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ቢገነቡ ኖሮ፣ ለመከላካያ፣ ለደህንነት፣ ለፖሊስ እና ለሐሰት ፕሮፓጋንዳ የሚወጣው ገንዘብ ቢያንስ በግማሽ ይቀንስ ነበር።

አጠቃላዩን የኢኮኖሚ ሁኔታ ለመዳሰስ ስንሞክር ደግሞ በርካታ አሳዛኝ ክስተቶችን እናያለን። የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሰ በመሄዱ፣ በተጨባጭ መሬት ላይ የሚታየውን ልማት ለማጋነን ኢህአዴግ ለሐሰት የልማት ፕሮፓጋንዳ ከፍተኛ ገንዘብ ለማውጣት ተገድዶአል። ይህ የሚያመለክተው ኢህአዴግ በመንግሥት በጀት የሚጠቀመው የሀገሪቱ የልማት ቅደም ተከተል (development priorities) በሚጠይቀው መሠረት ሳይሆን፣ ለራሱ ሕልውና (በሥልጣን መቆየት) በሚያመቸው መንገድ መሆኑን ነው። ኢህአዴግ ከሕዝብ የሚሰበስበውን ገንዘብ ምርታማ ለሆኑ ጉዳዮች ስለማያውለው፣ ለልማት በቂ ገንዘብ ማግኘት አልቻለም። ለዚህ እንደ መፍትሄ አድርጐ የወሰደው ገንዘብ ማተምን እና ከውጭ ሀገር ዕርዳታ እና ብድር ማሰባሰብን ነው። ይህ የልማት ስልቱ ቢያንስ ሁለት አበይት ችግሮችን አስከትሏል። እነዚህም ከመጠን ያለፈ የዋጋ ንረት እና ከፍተኛ የውጭ ጥገኝነት ናቸው። የውጭ ጥገኝነቱ አንዱ አመልካች የሀገሪቱ የውጭ ዕዳ ጫና ከፍተኛ መሆን ነው።

ኢህአዴግ በኢትዮጵያ እና በሕዝቧ ላይ የሰራውን ደባ በልማት ለመሸፈን ሁሉንም የልማት ሥራዎች ራሱ አሠርቶ በቴሌቪዥን እያሳየ፣ ፖለቲካዊ ሕጋዊነት (legitimacy) ለማግኘት እንደሚጥር በሚገባ የሚታወቅ ነው። ይህ ድርጊቱ ሰፊውን ሕዝብ ከልማት ተሳትፎ አግልሎታል። እንደሚታወቀው መሬት የተባለ ሁሉ የኢህአዴግ ነው። ትላልቅ የባንክ ብድሮች የሚሰጡት ከኢህአዴግ ይሁንታ ሲያገኙ ብቻ ነው። ኢህአዴግ መሬት ከሕዝቡ ነጥቆ ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ በሊዝ ሽፋን እየሸጠ ነው። ሕዝቡ የሚሳተፍበት የአክስዮን ገበያ እንዲቋቋም ቢጠየቅ አሻፈረኝ ብሏል። ብዙ የተወራለት የኢህአዴግ የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራም "በድንጋይ ጠራቢነት" ተጠናቅቆአል። የምግብ ውጤቶችን ጨምሮ በሀገሪቱ የሚመረቱ ምርቶችን ሁሉ ወደ ውጭ በመላክ፣ ቀድሞውንም ያስራበውን ሕዝብ ይበልጥ እያስራበው ነው። ዘላቂነትና ፍትሐዊነት የሌለው "የኮንዶሚኒዬም" የመኖሪያ ቤት ሥራ ፕሮግራም አውጥቶ አብዛኛውን ሕዝብ ቤት አልባ እያደረገ ነው። "የደርግ መንግሥት ያደርግ እንደነበረው የጋራ መኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ በነፃ ስጠንና መኖሪያ ቤቶችን እኛው እራሳችን እንሰራቸዋለን" ብሎ ሕዝቡ ቢጠይቀው "ባለ ቤት ከሆንክማ መች ዝም ብለህ ትገዛልኛለህ" በሚል አስተሳሰብ በመኖሪያ ቤት እጦት ሕዝቡን እያሰቃየው ነው።

ለማጠቃለል የአቶ መለስ መንግሥት ወደብ አልባ አደረገን፤ በሻዕቢያ አዘረፈን፤ ከሕዝብ የሚሰበስበውን ገንዘብ የራሱን ሥልጣን ማስጠበቂያ አደረገው። ገንዘብ ስለማይበቃው ብር እያሳተመ ኢኮኖሚው ውስጥ ስለረጨው በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ ለማይታወቅ የዋጋ ንረት ዳረገን፤ የብር የመግዛት ኃይል ከመቼውም በባሰ ሁኔታ እንዲያሽቆለቁል አደረገ፤ የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ እና የጡረታ አበል የምግብ ወጪን እንኳን ለመሸፈን አልበቃ አለ፤ የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን ታይቶ በማይታወቅ መጠን አሽቆለቆለ፤ የደርግ መንግሥት በነፃ የሰጠንን መሬት ጭምር ነጠቀን፤ ሥራ አጦች አደረገን፤ ወጣት ምሁራንን በድንጋይ ጠራቢነት አሰማራ፤ በሥራ እና በችሎታ ፈንታ ሥልጣንን እና ታማኝነትን የብልጽግና ምንጭ አደረገ፤ ሙስናን የስርዓቱ ውስጣዊ ባሕሪይ አደረገው፤ በመደበኛ የመንግሥት ሥራ የሚገነቡትን መሠረተ ልማቶች በቴሌቪዥን እያሳየ ፖለቲካዊ ሕጋዊነት ማግኚያ ዘዴ አድርጐ ተጠቀመባቸው፤ በነጋዴዎችና በሠራተኞች ላይ ተገቢ ያልሆነ የታክስና የግብር ጫና ቆለለባቸው፤ እንደ እውነቱ ከሆነ የአቶ መለስ መንግሥት ያደረሰብንን የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ በደሎች ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም።

እንዲያውም ከእንግዲህ በደሎችን መዘርዘራችን አቁመን የእነዚህ ሁሉ ችግሮች መንስዔ የሆነውን የአቶ መለስ አምባገነን መንግሥት በሰላማዊ መንገድ ማስወገድ ያለብን ይመስለኛል። እንደ አንድነት ያሉት ተቀዋሚ ፓርቲዎች ለሥልጣን ከበቁ በመጀመሪያ ይወስዳሉ ብዬ የምገምተው እርምጃ መሬት የመንግሥት ብቻ ነው የሚለውን ሕገመንግሥታዊ አንቀጽ በማሻሻል፣ ዜጐች በሕጋዊ የመሬት ይዞታቸው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። መኖሪያ ቤት የሌላቸው ዜጐች የጋራ መኖሪያ ሕንፃ (apartment building) ለመሥራት የሚያስፈልጋቸው መሬት በነፃ ይሰጣቸዋል፤ የቢዝነስ ድርጅቶች ለመገንባት የሚያስፈልጋቸውም መሬት በአነስተኛ ክፍያ ይደለደልላቸዋል። የባንክ ብድር በኢንቨስትመንት ፕሮጀክት አዋጪነት መስፈርት ብቻ የሚሰጥበት ሕጋዊ ማዕቀፍ ይመሰረታል። በሙስና የተዘረፈ ገንዘብና ሀብት ለሕዝብ ይመለሳል። የአክስዮን ገበያ ይቋቋማል። የመንግሥት በጀት አጠቃቀም በሀገሪቱ የልማት ቅደም ተከተል (development priorities) መሠረት ብቻ ይሆናል። "ከፍተኛ ትምህርት ለድንጋይ ጠራቢነት" የሚለው የኢህአዴግ መፈክር ከተለጠፈበት የዩኒቨርስቲ ግድግዳ ላይ ተቀድዶ ይጣላል።

የተጨማሪ እሴት ታክስ ኢህአዴግ ከሰቀለበት አሥራ አምስት በመቶ ወደ ሰባት በመቶ ይቀነሳል። የኢህአዴግ የሊዝ አዋጅ ይሻራል። የወለድ ተመን አሁን ካለበት አምስት በመቶ ወደ ሰባት በመቶ ከፍ ይደረጋል። የመምህራንን ደመወዝ ጨምሮ፣ የመንግሥት ሠራተኞች እና የጡረተኞች ደመወዝ እና የጡረታ አበል በየዓመቱ በተወሰነ መጠን እንዲጨምር ተደርጐ በመካከለኛውና በረጅሙ ጊዜ ወደ ነበረበት የመግዛት ኃይል እንዲያንሰራራና ብሎም እንዲጨምር ይደረጋል። ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ የኢትዮጵያ የባህር በር የሆነውን የአሰብ ወደብ በማስመለስ ላይ ያነጣጠረ ድንበር የማካለል ሰላማዊ ድርድር ከኤርትራ መንግሥት ጋር ይጀመራል።

ከዚህ ሁሉ በፊት ግን በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ኢህአዴግ እንደ እነ አንድነት ላሉት ሐቀኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕድሉን መስጠት ይገባዋል፤ አሊያም እነዚህ ሐቀኛ ተቃዋሚዎች በተጠናከረ ሰላማዊ ትግላቸው ዕድሉን እራሳቸው መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። እስከዚያው ኢህአዴግ ያመጣብን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ቀውስ እየተባባሰ ይቀጥላል።

# ከአምስቱ ኢትዮጵያውያን አንዱ ለአእምሮ ህመም ተጋልጧል ተባለ

ብሩክ ከበደ

አንጋፋው የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር በአእምሮ ጤና ዙሪያና ተዛማጅ ችግሮች በተመለከተ ከሐምሌ 10-14 ቀን 2004 ዓ.ም በደብረዘይት ከተማ ለጋዜጠኞችና የሚዲያ ባለሙያዎች ያዘጋጀው አውደ ጥናት ተጠናቀቀ፡፡

በዚህ አውደጥናት ላይ ከዋናው የአማኑኤል ስፔሻላይዝድ የአእምሮ ህሙማን ህክምና መስጫ ሆስፒታል ጨምሮ ከተለያዩ ቦታዎች በማስተማርና ምርምር በማድረግ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ የዘርፉ ከፍተኛ ባለሙያዎች በአሁኑ ጊዜ አሳሳቢ ደረጃ ከመድረሱ የተነሳ ከአምስት ሰው አንዱ ከአእምሮ ህሙማን መሀል በአንደኛው ዓይነት ተጠቂ መሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልገው አበክረው አስገንዝበው ለዚህም ጉዳት አደገኛ እፆችና አልኮል መጠጦች ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዙ ገልፀዋል፡፡

ይህንኑ ምርምራቸውን በማስረጃ ለማስደገፍ ይረዳቸው ዘንድ በተለይ ቡታጅራን ማዕከል በማድረግ "ኢንሴኖ" በተባለች ሰፍራ ለአመታት በነዶ/ር ተሾመ ሽብሬ የተደረገው ጥናት የህመሙን መንስኤና የታማሚውን ሙሉ መረጃ የያዘ በመሆኑ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ከአለምም ቀዳሚ መሆኑን ዶክተሩ ከነ ምክንያቱና ውጤቱ አብራርተዋል፡፡

"በህይወቴ ከ43 አመታት በኂላ ቢሾፍቱ ላይ ጋዜጠኞች ሰብስቤ ስለ አእምሮ ህመም አወራለሁ ብዬ አስቤም አላውቅም" ሲሉ ንግግራቸውን የጀመሩት በአሜሪካ የአእምሮ ህሙማን ህክምና መስጫ ማዕከል የከፈቱትና በአሁኑ ጊዜ ወደ ሀገራቸው በመምጣት የጤና ጥበቃ ሚኒስትሩ አማካሪ የሆኑት ዶ/ር ተድላ ወ/ጊዮርጊስ ለ80 ሚሊዮን ህዝባችን ያሉን 40 ሳይካትሪስት ሐኪሞች ብቻ ስለሆኑ ከቤተሰብ ጀምሮ ጠቅላላ ማህበረሰቡ ህሙማኑን በመንከባከብ የበኩሉን እንዲወጣ አስገንዝበው ዘርፉንም በሰው ኃይልና በማዕከላት ግንባታ ለማጐልበት እየተሰራ ያለውን ሥራ አብራርተዋል፡፡

ሌላው ከጤና ረዳትነት ተነስተው እስከ ዶ/ር ደረጃ የደረሱትና ለ37 ዓመታት በማረሚያ ቤት ያገለገሉት ዶ/ር ዓለሙ አስገዶም "ፎረንስኪ ሳይካትሪ" ባለቤት የሌለው ነገር ግን በአማኑኤል ሆስፒታል በጐፈቃደኝነት 2 የሴት እና 11 የወንድ አልጋ የተሰጠው በመሆኑ በርካታ ሺዎች ቁጥር ያለው እስረኛ ጤነኛው ከአእምሮ ታማሚው የማይለይበት ሁኔታ በመፈጠሩ ተጨማሪ ጫና እየፈጠረ መምጣቱን በዝርዝር አብራርተው አሁን ግን ትኩረት እንዲሰጠው በመታሰቡ ለውጥ ይኖራል ብለው እንደሚገምቱ ተስፋ አድርገዋል፡፡

ባለሙያዎች "Mh GAP" የአእምሮ ህክምና ክፍተቱን በተመለከተ በሳይኮሲስ፣ ኤፒሊፕስ፣ ዲፕሬሽን፣ አልኮልና አደገኛ ዕፆችን በተመለከተ ፕሮጀክት ቀርፀው በመንቀሳቀስ ላይ ሲሆኑ በተለይ በየፀበል ቤቱ የአእምሮ ህሙማን ከፀበሉ ጐን ህክምና የሚያገኙበትን መንገድ ከሃይማኖት አባቶቻቸው ጋር ተነጋግረው እየሰሩት ያለው ሥራ አመርቂ ውጤት እያሳየ መምጣቱን ተናግረዋል፡፡

ህብረተሰቡ የአእምሮ ህመምተኞችን መንከባከብ እንዳለበትና ማግለል እንደማይገባው የሚመክሩት ባለሙያዎች ለዚህ ቁልፍ ሚና ያለው በጋዜጠኛው እጅ ነው ብለዋል፡፡ በዚህ አውደጥናት ላይ የኦስቲቲክ በሽታ ተጠቂዎች ትኩረት ከተሰጣቸው በአንድ ዘርፍ ከጤነኛ ሰው የተለየ ዕውቀት እንዳላቸው የውጪ ሀገራትን ተሞክሮ በመግለጽ ተብራርቶል፡፡

# በምዕራብ አርሲ ዞን ገበሬዎች ሊፈናቀሉ መሆናቸውን ገለፁ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ አርሲ ዞን ሶስት ወረዳ የተወከልን ነን የሚሉ ገበሬዎች ከሥራችንና ከመኗሪያችን እንድንነሳ እየተደረግን ስለሆነ ፍትህ ይሰጠን እያሉ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ፡፡ ከዞኑ ሦስት ወረዳዎች መወከላቸውን የገለፁ እነዚህ ገበሬዎች እንደሚሉት ‹‹ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ጀምሮ ተይዞ የነበረው ቀያችንን ‹ልቀቁና ሂዱ› በመባላችን እጅግ አዝነናል›› ሲሉ የተሰማቸውን ቅሬታ ገልፀዋል፡፡ በመፈናቀሉ ሂደትም ከ10 ሺህ ያላነሱ ሰዎች ሊነሱ እንደሚችሉ ተጠቁሟል፡፡

ከዚሁ ከምዕራብ አርሲ ዞን አርሲ ነጌሌ፣ ጂዳ አዳሚቱሉና አናሻላ ከሚባሉ ወረዳዎች ከ40 በላይ የሆኑ ገበሬዎች እንደሚናገሩት ‹‹የእርሻ መሬታችንን፣ ከብቶቻችን የሚውሉበትንና የመኖሪያ ቀያችንን ሳይቀር ‹ልቀቁ› ተባልን፡፡ በየቀበሌውና በየወረዳው የተመደቡ ካድሬዎች የዜግነት መብታችንን እየገፈፉን ናቸው፡፡ በየወረዳውና በዞናችን ላሉ ኃላፊዎች ብናመለክትም መፍትሔ አላገኘንም፡፡ ለአቤቱታችንም ምንም ዓይነት ግምት ባለመስጠታቸው በአግባቡ እንኳን ሊያናግሩን ፈቃደኞች አልሆኑም፡፡ በዞን ደረጃ ከሦስቱ ወረዳ 80 ሰው አቤቱታ አቅርበን ፍትህ ማግኘት ባለመቻላችን በክልል ደረጃ አቤቱታችንን ለማቅረብ ተገደናል፡፡ በዚሁ ምክንያት ቁጥራችን 40 የሚሞላ ተወካዮች አዲስ አበባ መጥተን ለሚመለከተው የመንግስት አካል የህዝቡን አቤቱታ አቅርበናል፡፡ የሚመለከታቸው የክልሉ ተወካዮችም ጉዳዩን ተመልክተው ውሳኔ ለመስጠት ለነገ ሐምሌ 18 ቀን 2004 ዓ.ም ቀጠሮ እንደተሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

ተበዳይ ነን የሚሉት እነዚህ አቤቱታ አቅራቢዎች ‹‹ህዝብን ከመኖሪያና ከሥራ ቦታ እያባረሩ ‹ለህዝብ ነው፤ ለልማት ነው› እያሉ በህዝብ እየቀለዱ ነው፡፡ ስለዚህ የሚመለከተው የመንግስት አካል ጉዳዩን በጥሞና ተመልክቶ ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲሰጠን ጩኸታችንን አሰሙልን፡፡›› ካሉ በኂላ በመቀጠልም ‹‹ህዝብን በመንግስት ላይ የሚያነሳሱ ካድሬዎችና ደህንነቶች ላይ መንግስት እርምጃ መውሰድ ካልቻለ ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰ ነው፡፡›› በማለት ሥጋታቸውን ገልፀዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ቅሬታዎች በተለመከተ የክልሉ ምዕራብ አርሲ ዞን ምክትል አስተዳዳሪና የግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ተሰማ ገ/መድኅም የሚፈናቀሉ እንደሌሉ ገልፀዋል፡፡

በተለይ እንደ አቶ ተሰማ ገለፃ ከሆነ የተጠቀሱት አካባቢዎች አቢያታና ሻላ ሐይቆች ዙሪያ ለረጅም ጊዜ በብሔራዊ ፓርኩ ክልል ውስጥ የኖሩ በመሆናቸው ፓርኩ ላይ ደግሞ የዳግም ከለላ እየተደረገ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ በጉዳዩ ዙሪያም የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ሽማግሌዎች፣ የሚመለከተው የመንግስት አካላት በጋራ መወያየታቸውን በመግለፅ የመፍትሄ አቅጣጫ መያዙን አስታውሰዋል፡፡

በውይይቱም መሰረት ሦሥት አማራጮች ቀርበው በሁለተኛው አማራጭ ላይ መስማማታቸውን፤ ይህም ነዋሪዎቹ ቀደም ሲሉ የሰፈሩ በመሆኑ ፓርኩን በማጥበብ ነዋሪውን ከፓርኩ ክልል ውጭ በማድረግ ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ለመስጠት መታሰቡን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ እስካሁን እልባት ያላገኘ መሆኑን ገበሬዎችም እንደማይፈናቀሉ አቶ ተሰማ ጠቁመዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በባሌ ብሔራዊ ፓርክ አካባቢም ተመሳሳይ የዳግም ከለላ ስራ ተሰርቶ መጠናቀቁን ኃላፊው አቶ ተሰማ ለዝግጅት ክፍላችን አስታውቀዋል፡፡

# አንድነት በወከባ ውስጥ ሆኖ በፈረንሳይ ለጋሲዮን ህዝባዊ ስብሰባ አደረገ

## - ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበሩ አባላት በተከታታይ ቀናት ታግተው ነበር

እሁድ ሐምሌ 15 ቀን 2004 ዓ.ም. በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የወረዳ 12/13 የምርጫ ክልል ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለፈረንሳይና አካባቢው ልዩ ስሙ ኬላ የልበ ብርሃንና ቀበና አቦ እድር አዳራሽ ውስጥ ህዝባዊ ስብሰባ አካሄደ፡፡ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባላትና የአካባቢው ህብረተሰብ የተሳተፉበት ህዝባዊ ስብሰባ በወቅታዊ የሀገራችን ጉዳዮች ላይ ያተኮረ እንደነበር ለመረዳት ተችሏል፡፡

በእለቱ የመክፈቻ ንግግር ያሰሙት የፓርቲው ከፍተኛ አመራርና የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ የሆኑት ኢ/ር ዘለቀ ረዲ ሲሆኑ በንግግራቸውም ኢህአዴግ በ21 አመታት ውስጥ ዜጎችን ከየስራቸው እና ከየመኖሪያቸው እያፈናቀለ ለከፍተኛ ችግር ማጋለጡን ገልፀዋል፡፡ ይህንን ፕሮግራም ያዘጋጁት የወረዳው አመራር አካላት በደህንነቶችና ሲቪል በለበሱ ፖሊሶች ከፍተኛ እንግልት እንደደረሰባቸው፤ ሀገሪቱ በህዝብ ይሁንታ ሳይሆን በግለሰቦች ፍላጎት እየተመራች እንደሆነ፣ የጠ/ሚኒስትሩን መታመም እንኳን የሰማነው ለአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ከመጡት የሴኔጋሉ ፕሬዝዳንት እንደሆነ እንደማሳያ ያቀረቡት ኢ/ር ዘለቀ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግር ለመቅረፍ ህዝቡ መወሰንና መደራጀት እንዳለበት እንደ መፍትሔ አስቀምጠዋል፡፡

ጥናታዊ ፅሁፋቸውን በወቅታዊው የኑሮ ውድነት ዙርያ ያቀረቡት ደግሞ የኢኮኖሚ ባለሙያ፣ ፖለቲከኛና የፓርቲው የኤዴቶርያል ቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ በላይ ፍቃዱም ኢህአደግ ባለፉት 21 አመታት ውስጥ ብቸኛው አምባገነን እንደነበርና ለ40 አመታትም ዋጋ እንዳስከፈለ፤ ለሀገራችን መሰረታዊ ምግብ የሆነው እንጀራ እንኳን የቅንጦት ምግብ እንደሆነ ፤ በወርሃዊ ደመወዝ መቆየት እንደማይቻል፤ 11 በመቶ አድገናል ቢባልም የእኛ ኑሮ ግን እንዳልተለወጠ፤ የዋጋ ግሽበትና ሙስና ከቁጥጥር ውጭ እንደሆነና በአጠቃላይ ዝቅተኛው የህብረሰተብ ክፍል የሲኦል ውስጥ ኑሮ እንዲኖር ተፈርዶበታል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም ለነጻነት የሚደረግ ትግል እንደነ ብርቱካን ሚደቅሳ፣ አንዱዓለም አራጌ ፣ እስክንድር ነጋ፣ በቀለ ገርባ፣ ናትናኤል መኮንንና ሌሎችንም ዋጋ ቢያስከፍልም ወጣቱ ቤቱ ከመቀመጥ ይልቅ በመውጣት ህወሓት ኢህአዴግን በሰላማዊ ትግል ማስወገድ አለበት በማለት መፍትሔውን ጠቁመዋል፡፡

ቀጣዩን ጥናታዊ ፅሑፍ በሊዝ አዋጁ ዙርያ ያቀረቡት አንጋፋው ፖለቲከኛና የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ኃይሉ አርዓያም የሊዝ አዋጁም አከራካሪ በሆነና መሻሻል ባለበት የህገ-መንግስት አንቀፅ ላይ የተመሰረተና በተፈጥሮ የተሰጠንን ሀብት የሚነጥቀን መሆኑ፤ መንግስት የስሌትና የህዝብ ስሜት የማንበብ ችግር እንዳለበት፤ መንፈሳዊ (ዴሞክራሲ ፣ ነጻነት…) ቁሳዊ (መንገድ፣ የጤና ተቋማት …) ልማቶች ቢኖሩም መንግስት ያተኮረው ግን ቁሳዊው ላይ ብቻ መሆኑን፣ የሊዝ አዋጁ ከመድበለ ፓርቲ ስርዓቱ ጋር እንደሚጋጭ፣ መሬትን የራሱ ያደረገ መንግስት በፍፁም ከሙስና ሊወጣ እንደማይችል፤ ህገ-መንግስቱ መንግስት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የፈለገውን መሬት የመውረስ መብት ሲሰጠው ተገቢውን ካሳ የመክፈል ግዴታን ቢጥልበት ይህ ግን ተፈፃሚ እየሆነ እንዳልሆነ ፤ መንግስት ፈጣን እድገት በማምጣት ስም መሬትን ቢወርስም 193 አባል ሀገራት ካሉት የተባበሩት መንግስታት መሬትን ከህዝብ የቀሙ ኮሚኒስቶች ተብለው የሚጠሩት አምስት ሀገራት ሲሆኑ እነዚህም የሚታወቁት በፈጣን እድገታቸው ሳይሆን በድህነታቸው ነው በማለት የመንግስትን የሊዝ አዋጅ ተችተዋል፡፡

ከተሳታፊዎችም የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፤ ከተነሱት ሀሳቦች መካከልም ህዝብ መደራጀትና መታገል ያለበት አሁን ነው፡፡ ኢህአዴግ ተቻችሉ ይለናል፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ተቻችለን ሳይሆን ከጥንትም ጀምረን ተፈቃቅረን የምንኖር ህዝብ ነን የሚሉ ሲሆን ፤ በታሰሩት ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ዙሪያም ፓርቲው ሁል ጊዜ ጋዜጣዊ መግለጫ ከመስጠት ሌላ ምን አስባችኋል? የሚል ጥያቄ የተሰነዘሩ ሲሆን ‹‹አንድነት ጉዳዮችን በሰከነ ሁኔታ በመመልከት አምባገነኑን መንግስት ለመለወጥ እንደሚሰራ እና መንግስት በኃይማኖት ውስጥ እያከናወነ ያለውን የእምነት ነፃነትና ጣልቃ ገብነት ግልፅ በሆነና በሰከነ መንገድ እየተከታተለው ሲሆን አቋሙንም ወቅቱን ጠብቆ ያሳውቃል በማለት ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡

በህሊና ፀሎት የተጀመረው ህዝባዊ ስብሰባው በወጣትና አንጋፋ ደራሲያን በቀረቡ ቀልዶች ፣ ንፅፅሮችና ግጥሞች የተዋዛ ሲሆን የፓርቲው የአዲስ አበባ ምክር ቤት ሰብሳቢ በሆኑት ዶ/ር ንጋት አማካይነት በተደረገ የመዝጊያ ንግግር ከቀኑ 7:30 ላይ ተጠናቋል፡፡

በተያያዘ ዜና በዚሁ በፈረንሳይ ለጋሲዮን የተዘጋጀውን ህዝባዊ ስብሰባ ለማደናቀፍ የፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ፖሊስ ማዘዣ ጣቢያ ህገወጥ ድርጊት መፈፀሙን የአንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸ[illegible]ል፡፡ ጽ/ቤቱ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጸው ‹‹ስብሰባው እንዲደረግ ከአዲስ አበባ መስተዳድር ህጋዊ ፍቃድ ተገኝቷል፡፡ ህጋዊ ፍቃዱን በእጃቸው ይዘው የአካባቢውን ህብረተሰብ እንዲወጣ ሲቀሰቅሱ የነበሩትን ስድስት የፓርቲውን አባላት ወ/ሮ እመቤት ኃይሌ፣ አቶ ነብዩ ባዘዘው፣ አበበ ቁምላቸው፣ ተፈሪ ተሾመ፣ ዘላለም ታደሰ፣ ዋለልኝ አልሞ ለቅስቀሳ መኪና ያከራይዋቸውን ሹፌር ከነመኪናው አግተው ስብሰባውን ለማደናቀፍ ሞክረዋል፡፡ ህጋዊ ፍቃድ እንዳላቸው ቢያሳዩም ፖሊስ ራሱን ከህግ በላይ አድርጎ በቅስቀሳ ላይ የተሰማሩትን የፓርቲውን አባላት ዐርብ ዕለት ለሁለት ሰዓትና በማግሥቱ ቅዳሜ ደግሞ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት አግተው አቆይተው ለቀዋቸዋል፡፡ የታገቱትን የፓርቲውን አባላት ለማስፈታት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከሄዱት የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች መካከል አቶ ደምሴ መንግስቱ (የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚና የህግና ስብአዊ መብት ጉዳይ ኃላፊ) ፖሊስ ጎትቶ በማስገባት በተመሳሳይ ሁኔታ ለ45 ደቂቃ ያህል አግቷቸው እንደነበር ተጠቁሟል ፡፡

በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡት አንድ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር እንደተናገሩት ‹‹ህግ እያስከበርን ነው›› የሚለው ፖሊስ በማንአለብኝነት ዜጎችን በአመለካከታቸው ብቻ እየነተቱ ማገቱ አገሪቱ ውስጥ ያለው የህግ የበላይነት አለመከበሩን ከማሳየቱም በላይ ፖሊስ የተሰማራበት ድርጊት አሳሳቢ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡›› ብለዋል፡

# የአርበኞች ማህበር አባላት …

ከ ገፅ 15 የዞረ....

የሚያግዳቸው የመንግስት አካል አልተገኘም፡፡›› በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

በማያያዝም ‹‹ማህበሩ ከአገር አቀፍ ማህበሩ ውጭ የየክፍለ ሐገሩ አርበኞች ማህበር ቅ/ጽ/ቤቶች አሉ፡፡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የራሳቸው አመራር፣ የራሳቸው የገቢ ምንጭ፣ የራሳቸው መዝናኛ ሥፍራ አላቸው፡፡ በዚሁ መሰረት የሸዋ አርበኞች ጽ/ቤት በካዛንችስ አለ፡፡ የማህበሩ ፕሬዝዳንት በአገር አቀፍ ማህበሩ ላይ ከሚፈጽሙት ወንጀል አልፈው ተርፈው በሸዋ አርበኞች ማህበር ውስጥ ገብተው ገቢውንና አመራሩ ላይ ችግር እየፈጠሩ ነው፡፡›› ይላሉ፡፡

በመጨረሻም እነዚህ አባት አርበኞች እንደሚሉት ‹‹ከብዙ ትግል በኂላ የአርበኛው የድጎማ አበል መጠነኛ ጭማሪ ተደርጓል፡፡ በቂ ነው ብለን ባናምንም የትግላችን ውጤት ነው፡፡ ጭማሪው ማንም በገፀ በረከት የሰጠው ስጦታ ሳይሆን እስከ ዛሬ ግለሰቦች ሲመዘብሩት የነበረው ገንዘብ መሆኑን በመረዳት አርበኛው ሙሉ በሙሉ መብቱና ጥቅሙ እስኪከበር ድረስ አቤቱታችንን አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡›› ብለዋል፡፡ በመቀጠልም ‹‹የአርበኛው ታሪክም ሆነ ንብረት የአገር ታሪክ ስለሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ስለሚመለከተው በተለይ ወጣቱ የአያቶቹና የአባቶቹ ታሪክና ንብረት በጥቂት ግለሰቦች ሲወድምና ሲዘረፍ ዝም ብሎ ማየት የለበትም፡፡›› በማለት ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

የማህበሩ ፕሬዚዳንት ሐሳብ እንዲሰጡ በተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ሐሳባቸውን ማካተት አልቻልንም፡፡

# ከሚወድቅ ሥርዓት ጋር አብረህ እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ

ሙሉጌታ ከበደ

ኢህአዴግ በአባላቱ ጭምር አመኔታ ካጣ ሰነባብቷል፡፡ አባላቱ በሚሰበሰቡበት መድረክ ሁሉ የአባልነት ስንብት (ቅጽ 06) እየሞሉ በመሠናበት ላይ እንደሆኑ ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ሹክ ብለውናል፡፡ ይህ የስንብት ደብዳቤ በመምህራን አካባቢ በእጅጉ የጐላ ነው፡፡ መምህሩና ተማሪው በአንድ ለአምስት ጥርነፋ ሥር ከወደቁ በኋላ ከፓርቲው የመልቀቅ ሁኔታ በእጅጉ ተባብሷል፡፡ በተለይም ባሳለፍናቸው ሳምንታት "ለግምገማ" በሚል በየአዳራሹ ሲገማገሙ የሰነበቱት መምህራን ሆድ ብሷቸዋል፡፡ የግምገማው ውጤት "A,B,C,D" የሚል ደረጃን የሚሰጥ አብሻቂና አሸማቃቂ እንደነበር እየተነገረ ነው፡፡ ከግምገማው ውጤት በኋላ በርካታ መምህራን የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አባል በመሆን የተነጠቁትን መብትና ነፃነት ለማስመለስ በአባልነት እየተመዘገቡ መሆናቸውም እልህ የፈጠረው ድንገተኛ ክስተት መሆኑ ነው፡፡

ይህ የሰሞኑ የመምህራኑ ውሎ ሲሆን ሌሎችም መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶችም ቅጥ ባጣው የአገዛዙ የግምገማ ፈሊጥ ሲታመሱ ሰንብተዋል፡፡ ከሐምሌ 2 -6/2004 ድረስ 3ኛ ዙር የቴሌ ሰራተኞች ግምገማ በአ.አ ዩኒቨርስቲ ስድስት ኪሎ ጊቢ በተለመደው የጥርነፋ ስልት ግምገማው ሲካሄድ ሰንብቶ ነበር፡፡ ዶ/ር ደብረፅዮን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ካሉበት ሆነው ባስተላለፉት ንግግር መሠረት ሰራተኛው በአንድ ጎበዝ አለቃ እየተመራ በጥርነፋው ህግ መሠረት የአንድ ሳምንት ግምገማውን አካሂዷል፡፡ ሃላፊው ካሉበት ሆነው የላኩት የተቀረፀው ምስል ከቢሯቸው ሆነው ይሁን ከቤታቸው አለመታወቁ አንዳንድ ተገምጋሚዎችን ቀልድ ያወራወረ ነበር፡፡

በግምገማው ላይ ሰራተኛው "ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ለመሆኑ ላጠፉት ጥፋት መቼ ይሆን ይቅርታ የሚል ቃል ካፉቸው የሚወጣው፡፡" በማለት ከመጠየቅ አልፎ "ጠ/ሚሩ ‹ኢትዮጵያ የማዳበሪያ ፋብሪካ አያስፈልጋትም› ሲሉ ከርመው፤ አሁን ደግሞ ‹የማዳበሪያ ፋብሪካ ከፈትን› ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ባለፉት አመታት በርካታ ስተቶችንና ውሸትን ለሕዝብ ሲቀርብ አንድም ባለስልጣን ‹ይቅርታ፤ ተሳስተናል› ብሎ የጠየቀ የለም፡፡ ኢህአዴግ ይቅርታ የሚባል ቃል አያውቅም ወይ? የትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ ሳይሳካ ቀረ ወይ? ምነው የቁጥር ጨዋታ አበዛችሁብን፡፡ መቼም የምንናገረውን አትሰሙንም፤ ቢያንስ ቢያንስ እርስ በርሳችን እንኳን እንተማማ" በማለት ሰራተኞቹ በኢህአዴግ አገዛዝ መማረራቸውን ያበጠው ይፈንዳ በሚል ብሶታቸውን ተናግረዋል፡፡

አሁንም ግምገማው በዙር እንደቀጠለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ 500 (አምስት መቶ) የሚሆኑ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ከፍተኛ ኃላፊዎች ባሳለፍናቸው ሳምንታት በዶ/ር ደብረፅዮን መሪነት ግምገማ ላይ መሰንበታቸውንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ግምገማው የኃላፊዎቹን ሞራል የነካና ስብዕናቸውን ጭምር ያዋረደ እንደነበር ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡ ተሰብሳቢዎቹ ከስብሰባው መጠናቀቅ በኋላ ደብረፅዮን "ቀኑን ሙሉ ሲሞልጩን ውለዋል ሲሉ ተደምጠዋል፡፡" የመብራት ኃይል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ምህረት ደበበ ግንባር ቀደም ተወቃሽ ሆነው የዋሉ ሲሆን "እናንተ ሚስ ክሊንተን መጥታ መብራት ያጠፋችሁብን ናችሁ፣ የኢህአዴግ ም/ቤት ስብሰባ ላይ ተቀምጦ መብራት የምታጠፉብን ናችሁ፤ ህዝቡ ኢህአዴግን እንዲያማርር በዐመት በአል ቀን እንኳን መብራት ታጠፉላችሁ፤ ለዚህ ለእናንተ አለቃ (ለአቶ ምህረት ደበበ ማለታቸው ነው) ነግሬዋለሁ" እያሉ በየንግግራቸው ጣልቃ ኃላፊውን ሲያሸማቅቁ ትንሽ እንኳን የማክበር ስሜት አይታይባቸውም ነበር፡፡ "ደግሞ ‹የቴክኒክ ችግር ነው" እያለ ይመልስልኛል በማለት ከፍ ዝቅ ሲያደርጓቸው ተሰብሳቢው በእጅጉ ተገርሟል፤ በእጅጉም አዝኗል፡፡

ሰራተኞቹ ግን ችግሩ መኖሩን አምነው ለችግሩ ተጠያቂው መንግስት ነው፡፡ በድርጅቱ የመለዋወጫ መሣሪያ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ አለ፡፡ የቅያሪ ፊዩዝ እንኳን የሌለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ የድርጅቱ ሰራተኞች መለዋወጫ መሣሪያ እና ትራንስፎርመር ለመጠገንና ለመስራት የሚያስችላቸውን ፕሮፓዛል አቃቂ ብረታ ብረት ፋብሪካ ድረስ ሄደው ያጠኑትን ጥናት የኢህዴግ አመራሮች ነጥቀው እንዳስቆሟቸው በምሬት ይናገራሉ፡፡

ጥናቱን መንጠቅ ብቻ ሳይሆን ለድርጅቱ የሚያስፈልጉ የመለዋወጫ መሣሪያዎች ከወጪ በጨረታ ለማስገባት የተደረጉትን ስምምነቶች በሙሉ የአገዛዙ ሃላፊዎች እንዲሰረዝ አድርገዋል፡፡ ስለዚህ መጋዘኖቻችን በሙሉ ባዶ ናቸው፡፡ የዕቃ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ ተቋርጧል፡፡ አሁን ድርጅቱ መለስተኛ ጥገና እንኳን የሚያደርገው በሰራተኛው ተነሳሽነት ነው፡፡ "ይህቺ ሀገር የኔም ናት" በማለት አሮጌ ትራንስፎርመር ከመጠገን ጀምሮ የወዳደቁ ዕቃዎችን በመጠቀም እስካአሁን አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ሲናገሩ ተደምጧል፡፡ ይህ የሆነው ለምድነው? ሲባሉ "መንግስት ያቋቋመው MTC (ሜቴክ) የተባለ ሀገር በቀል ድርጅት ያቀርብላችኋል" በማለት በየጊዜው መልስ ቢሰጥም፡፡ MTC እስከ አሁን አንዳችም ነገር ማቅረብ ያልቻለ በራሱ ችግር ያለበት ድርጅት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

MTC የሚመራው በባለስልጣናት እና በጀኔራሎች ልጆች ሲሆን ተቋሙ ስሙን አሳምሮ ያልተገባ ሥራ ነው የሚሰራው፡፡ የድርጅቱን የጥናት ፕሮፓዛል ተነጥቆ የተሰጠው ለዚሁ ድርጅት ነው፡፡ በድርጅቱ መጋዘን ውስጥ ያሉ አሮጌ ዕቃዎችም ሆኑ መኪናዎች ትክክለኛ አሰራርን ባልተከተለ መንገድ በትዕዛዝ እንዲወጡ ተደርጕ በፋብሪካው እንዲጨፈለቁ ይደረጋል፡፡ በተለይም አገልግሎት የሚሰጡ መኪናዎች መጨፍለቃቸው በሀገር ላይ ጉዳት መፈፀም ነው፡፡ "MTC አዲስ ትራንስፎርመር ሰርቶ ሸጠላችሁ" እንባላለን ስንገጥመው ግን ከሳምንት በላይ አያገለግልም ወዲያውኑ ነው የሚቃጠለው፡፡ ከእኛው የወሰደውን ትራንስፎርመር ቀለም ቀብቶ ለእኛው በውድ ዋጋ የሚሸጥልን የቻይናዎች አሻንጉሊት ድርጅት ነው፡፡ " በማለት ያማርራሉ፡፡

የ MTC ነውር ስራዎች እነዚህ ብቻ አይደሉም፤ በቀጣዩ ጽሁፌ ድርጅቱ እንዴት እንደተቋቋመ? በነማን እንደሚመራ? በህዝብና በሀገር ላይ የሚሰራቸውን አንጉል ሥራ በዝርዝር ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡

ለዛሬው መብራት ኃይልን እንደ ቴሌ ለመበተን ያመቸው ዘንድ መንግስት ድርጅቱን ከህዝብ ለመነጠል የተቀነባበረ ሴራ ተቀናባብሮ ተዘጋጅቷል፡፡ የድርጅቱም ሰራተኞች በቅርቡ ይበተናሉ የሚል ሥጋትን ፈጥሯል፡፡ የሴራው አካል የሆነው ግምገማ ባለፈው ሳምንት የተካሄደው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ለዛሬው ውድ አንባቢያንን የምሰናበተው ሐምሌ 11/2004 የዛፍ ችግኝ ለመትከል የወጣው የመብራት ኃይል ሠራተኛ እየተቀባበለ የተናገረውን ለእናንተ በማድረስ ነው፡፡ ወቅቱ ክረምት በመሆኑ መሬት በውሃ ጠግባለች፡፡ አልፎ አልፎ እግርን በማዳጥ ሳቅ የሚያደርጉ ገጠመኞች በችግኝ ተከላው ጊዜ የገጠሙ ክስተቶች ናቸው፡፡ ከማዳጡ ጋር አይይዞ ሠራተኛው "እረ ጉበዝ ከሚወድቅ ሥርዓት ጋር አብረህ እንዳትወድቅ ጠንቀቅ እንበል" በማለት ሁሉም ሠራተኛ ቃል በቃል እየተቀባበለው የሥርዓቱ ፍፃሜ መቃራቡን በሣቅ አጃቢነት ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

# እኛ የምንታገለው ለሥርዓት ...

ከ ገፅ 6 የዞረ....

የምንታገል መሆናችንን በቅን ልቦና ቢረዱልንና ቢገነዘቡልን ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም እኛ የምንሰራው ሰራዊቱንና የፀጥታ ኃይሉንም ጭምር ተጠቃሚ ለማድረግና የተረጋጋ ሕይወት እንዲኖር ነው፡፡

ገበሬው ደግሞ ምን ያህል እየተሰቃየና እየተጐዳ እንዳለ ሁሉም ያውቃል፡፡ ከዚህ በኋላ ከዚህ የባሰ ችግር ሳይመጣ የመሬቱ ባለቤት እንዲሆንና የመብቱ ተጠቃሚ ለመሆን በትግሉ በተጠናከረ መልኩ ሊያግዘን ይገባል፡፡ ምክንያቱም ገበሬው በአሁን ሰዓት የመሬቱ ባለቤት አይደለም፤ እኛ የምንታገለው አንዱ ገበሬው የመሬት ባለቤት እንዲሆን መሆኑን በሰነድ ማረጋገጣችንን አውቆ አብሮን ቢታገል ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

- የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጤንነት ዙሪያስ ምን ይላሉ?

እኛ ከግለሰብ ጋ ሳይሆን ጥላቻችን ከስርዓቱ ጋር ነው፡፡ በግል ከሳቸው ጋር ፀብ የለንም፤ በግሌም እንደ መድረክም እሳቸው ሰብዓዊ ፍጡር እንደመሆናቸው መጠን መልካም ጤንነትን እንመኝላቸዋለን፡፡ ድሮም ቢሆን እሳቸው ኖሩም አልኖሩም እኛ የግለሰብ ለውጥ ሳይሆን የስርዓት ለውጥ ነው የምንፈልገው፡፡

ነገር ግን እውነቱን ማወቃችን ሳይቀር የእሳቸው ጤንነት ተደብቆ መቆየቱ ትክክል አይደለም፤ ይሄ የገዥው ፓርቲ ባህሪ ነው ማለት ደግሞ ሌላው አሳፋሪ ነገር ነው፡፡ እሳቸው ክፉም ሰሩ ደግ ስለሳቸው ጤንነት ማወቅ ነበረብን እና ዘግይቶ መነገሩ ተገቢ አይደለም፡፡ አሁንም ቢሆን እኛ የምንታገለው ለሥርዓት ለውጥ መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡

- አሁን የተመረጣችሁ አመራሮች የስራ ጊዜያችሁ ምን ያህል ነው?

ለአንድ ዓመት ሲሆን በሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ደንቡን በማሻሻል ሊለወጥ ይችላል፡፡ በሚሰሩ ስራዎች እና በተመረጡ አመራሮች ላይም ክፍተት እና ድክመት ከታየ የሚለወጥ ነገር ይኖራል፡፡

- ከአዲሱ አመራርስ ህዝቡ ምን ይጠብቅ?

ያለፉ ድክመቶችን በማረምና በማሻሻል በሰነድ ላይ የሰፈሩትን ወደ ተግባር እናረጋግጣለን ብለን ሥራ ጀምረናል፡፡ በዚህም አባላት፣ ደጋፊዎችና ህዝቡ ከጐናችን በመሆን ስህተታችንን በማረም፤ ጠንካራ ጐናችንን በማበረታታት ለምናደርገው ትግል አብሮን መስራት አለበት፡፡ አለበለዚያ ከእኛ የሚጠበቀውን በእኛ አቅም ብቻ ማከናወን የማይቻል ነው፡፡ ትግሉም ለውጡም የጋራችን ነውና፡፡ ያኔ የቆምንለት ዓላማ እንደሚሳካ መጠበቅ ይቻላል፡፡

# ከአቶ በረከት...

ከ ገፅ 5 የዞረ....

፡ በጊዜ ያልተሰፈረው ዕረፍት ዘላለማዊ ዕረፍት ይሆን እንዴ? ብሎ መጠርጠር ሟርት አይደለም፡፡

የአቶ መለስን መታመም ለምን እንደደበቁ የተጠየቁት አቶ በረከት "ቴክኒካል" በሆነ መንገድ ለመመለስ ሞክረዋል፡፡ "የገዥውን ፓርቲ ባህል ማወቅ ጠቃሚ ይመስለኛል" በማለት፡፡ ጉዳዩ የተደበቀው ግን አቶ በረከት እንዳሉት ከፓርቲያቸው ባህል ጋር የተያያዘ ነው ለማለት ይከብዳል፡፡ ብዙ ነገር ላይ እጃቸውን ያስገቡት የአቶ መለስ በድንገት አልጋ መያዛቸው ከፍተኛ ድንጋጤ እንደሚፈጥር ሀቅ ነው፡፡ የሚያስተዳድረው "ሲስተሙ" ቢሆን ኖሮ ለከፍተኛ ድንጋጤ አይዳረጉም ነበር፡፡ ስለዚህ በሚስጥር መያዙ አንዳች ጥያቄ ያጭራል፡፡ አደጋ ውስጥ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡

በተጨማሪም አቶ በረከት ያረጋገጡት ኢህአዴግ አምባገነን መሆኑን ነው፡፡ አዎ ህዝብ የመንግስትን አስተዳደር የማወቅ መብት እንዳለው የሚገልፀውን አንቀጽ ጭምድድ አድርገው ከህዝብ መደበቅ የገዥው ፓርቲ ባህል እንደሆነ ነገሩን፡፡ ህዝብን የማይከብርና የማይጠቅም ባህል ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ አሮጌ ባህል የህዝብን የማወቅ መብት የሚገድብ፣ አምባገነንነትን የሚያረጋግጥና ያረጀ ነው፡፡ ሀገሬ የምትመራው በአረጀ አስተሳሰብ እንደሆነ የአቶ መለስ መታመምና ሚስጥር መሆኑ ያረጋግጥልናል፡፡ ፖለቲካዊ እናድርገው ብንልም ሚዛን አይደፋም፡፡

በአጠቃላይም የአቶ በረከት ማብራሪያ ተገቢውን ምላሽ የሰጠ አይደለም:: ይልቁንም "አርፈው ይሆን" የሚል ጥርጣሪያችንን የሚያጐለብት እንጅ፡፡ ዞሮ ዞሮ ጉዳዩ ቀላል ጉዳይ አይደለም፡፡ ግልጽነትንና መመካከርን ይጠይቃል፡፡ ከዚያ ሲሻገርም ሀገርን መውደድና ማዳንን፡፡ ጊዜ ይሄዳል ጊዜ ይመጣል፣ መሪ ይመጣል መሪ ይሄዳል፡፡ ቢያንስ ከዚህ በኋላ እንኳ ስለ ሀገራችን ጉዳይ በሰከነ መንገድ ብንነጋገር፡፡

# የድህረ መለስ ዜናዊ ኢህአዴግ ...

ከ ገፅ 2 የዞረ....

ጋር ቢወግን የወጣዋል፡፡ 245 ነገስታት ከጥንት እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ድረስ የነገሱ ሲሆን አብዛኛው ከሰሜኑ አከባቢ ነበሩ›› ይላሉ፡፡ ዶ/ር አማርኛ ተናጋሪው ‹‹ይልቅ ኢትዮጵያን ለማዳ ሽኩቻ ውስጥ ሳይገቡ አይቀርም›› ይላሉ፡፡

መምሬ ውለታው በበኩላቸው ‹‹ኃ/ማሪያም ለስልጣን ሩቅ ነው፤ ቀጣዩን መምረጥ የቅራኔ ምንጭ ሊሆን ይችላል፤ ኢህአዴ ‹harmony› የሌለው ቡድን ነው›› ካሉ በኋላ ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡ ‹‹ከንግዲህ መለስ የገነቡትን በማስፈራራት ውሳኔ እንዲቀበሉ የማድረግ ሂደት ከንግዲህ ባለመኖራቸው ይፈቱታል፡፡›› በተለይ ኦሮሞና አማራ ብሔርን እንወክለዋለን የሚሉት ሁለቱ ገዢ ፓርቲዎች አሁን የቁጥራቸውን ያክል የስልጣን ድርሻ እንደሚፈልጉ የገልጻሉ፡፡ ይህ ፌደራሊዝሙ የተሰራበትን ነጥብ የያዘ ነው፤ ከንግዲህ ህወሓት ወደስልጣን ከመጣ ሌላውን ያስኮርፋል፣ የአማራዎቹ መምጣትም "ነፍጠኞችን እንዋጋ" ከሚለው የህወሓትና ኦህዴድ መፈክር አንፃር ከባድ ሊሆን እንደሚችል ይነገራል፡፡

ያም ሆነ ይህ ከኦህዴድና ከብአዴን የአንዳቸው ወደ ግንባር መምጣት አናሳዎቹን የመዋጥ ዕድል እንዳለው ስለሚተነተን ህወሓት አጋር ቡድኖቹንም ከጎኑ የማድረግ አቅም አለው ተባሉ ይገመታል፡፡ በቅርብ ጊዜ ከፍተኛ ኃላፊነት የያዙት የኢህዴን ሰዎች ከ40 በላይ ብሔረሰቦችን የወከሉ ናቸው፡፡ ‹‹ኦህዴድ ለመሬት ቅርምት እና ለህወሓት እጅ አዙር አገዛዝሽፋን የቆመ ነው፡፡ እነ አባ ዱላ ሞራል ኖሯቸው ለስልጣን አይቀናቀኑም›› ይላሉ ዶ/ር ሙሉ፡፡

ኢህአዴግ የቀድሞውን ያክል አይሆንም በመለስ መታመም /መሞት የተነሳ ‹‹ከርሳቸው ውጭ ሰው የለም የሚሉት አባላት በድርጅቱ ላይ እምነት እንደሚያጡ ይነገራል፡፡ በተጨማሪም ተተኪ የሚሆኑ ሰዎች በአግባብ የተለዩ ከመሆናቸውም በላይ አቋማቸው በተግባር አልተፈተሸም፡፡ ሌላው መንገድ በህይወት ተርፈው ግን መስራት የማይችሉበት ሁኔታ (incapacitate) ከተፈጠረም ያው መሆኑ ይገመታል፡፡

ቀጣዩ ጠ/ሚኒስትርም የመለስ አይነት ስብዕና ለመገንባት አሁን ያለው የመለስ ድባብ (post humous) እንኳ ጥላ ያጠላበታል፡፡ በግለሰብ ደረጃም ቅራኔ ሊገጥመው ይችላል፡፡ ዶ/ር ሙሉ ‹‹መለስን ጨምሮ በፖለቲካ ሴራ የተካኑት አንጋፋዎቹ እያለፉ በመሆኑ አቶ በረከት ሰሞኑን እንዳሉት ፓርቲው ውስጣዊ ችግሮቹን እንደከዚህ ቀደሙ እዚያው ይዞ መፍታቱ ያበቃበት ዘመን ነው›› በማለት ይደመድማሉ፡፡

# የፀረ ሽብር ህጉ አገሪቱ ፈርማ የተቀበለችውን የሰብአዊ መብት ድንጋጌ እንደሚጥስ ሰመጉ ገለፀ

የፀረ ሽብር ህጉ ድንጋጌ ወትሮውንም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የማይመጣጠንና የዜጎችንም መብት እንደሚጥስ ሰመጉ አስታወቀ፡፡ ሰመጉ ይህንን ያስታወቀው ሰሞኑን "በፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና በነፃ ጋዜጣ አዘጋጆች ላይ ሲፈፀም የቆየው የፍርድ አሰጣጥ ሂደቱም ሆነ ውጤቱ ሰመጉን ያሳስበዋል፡፡ " በማለት ባወጣው መግለጫ ነው፡፡

መግለጫው እንደሚዘረዝረው፡- "የፀረ-ሽብር ህጉን" በመተላለፍ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ከዋሉ በኂላ ጉዳያቸው በፍ/ቤት ሲታይ የቆየው በእነ አንዱዓለም አራጌ የክስ ፋይል የተከፈተውም ሆነ ቀደም ሲል በተለያዩ ሌሎች የክስ ፋይሎች የተፈረደባቸው ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ከተለያዩ ምክንያቶች አንፃር እጅግ ያሳስበናል፡፡ ምንም እንኳን የፀረ -ሽብር ህጉ (አዋጅ ቁጥር 652/2009) ወትሮውንም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግሥት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የማይመጣጠንና የዜጎችንም መብት እንደሚጥስ ቀደም ባሉት ጊዜያት አቋማችንን የገለፅን ቢሆንም የፍርድ ሂደቱን መንፈስ ላለመበረዝ ተጨማሪ መግለጫዎችን ከማውጣት ተቆጥበን ቆይተናል፡፡

አጠቃላዩን ሂደት በቅርብ ስንከታተል ቆይተን በተለይም ሐምሌ 6 ቀን 2004ዓ.ም. ጥፋተኛ በተባሉት ወገኖች ላይ ከፍተኛ ቅጣት ሲፈረድባቸው ታዝበናል፡፡ ሰመጉ የተጠርጣሪዎችን የማረሚያ ቤት ቆይታ በባለሞያዎች አማካኝነት ለመታዘብ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደርን ጠይቆ በመከልከሉ፤ የእድሜ ልክና ሌላም ከፍተኛ ፍርደኞች ከተጠርጣሪዎች ጋር እንዲታሰሩ በመደረጉ በደረሰባቸው ድብደባ የአካል ጉዳትም በመድረሱ፤ የቅጣት ውሳኔ በተሰጠበቅ ቀን እያንዳንዱ በጥፋተኝነት የተፈረደበት ግለሰብ ስለቅጣቱ አስተያየት የመስጠት ህጋዊና ሰብአዊ መብቱ ስላልተጠበቀለት፤ ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግና በነፃ ጋዜጦች ሀሳብን በነፃነት ለመግለጽ የማያደፋፍር ድባብ እየተፈጠረ በመሆኑ ሰመጉን እጅግ ያሳስበዋል ብሏል በመግለጫው፡፡

የሰብአዊ መብቶች የጀርባ አጥንት የሆኑት ሀሳብን በነፃነት መግለጽና ተደራጅቶ በፖለቲካ ትግል መሳተፍ በህግም ሆነ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ሊታቀቡ እንደማይገባ አሁንም እንደገና ማስታወስ እንፈልጋለን፡፡ ከዚህ አንፃር ለዜጎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰትና የፍርሃት ድባብ ምንጭ የሆነው የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2009 እንደገና የሚታይበት ጊዜ አሁን መሆኑን ሰመጉ አበክሮ ያሳስባል፡፡ የተጠቀሰው አዋጅ አንዳንድ አንቀፆች ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት፣ ኢትዮጵያ ካፀደቀችው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ጋር እንደሚጣረስ ታምኖ፣ ከእውነተኛ አሸባሪ ይልቅ ንፁሃንና ሰላማዊ ዜጎቻችን እንዲያሸማቅቅ፤ ዴሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ መብቶችን እንዲገድብ ተደርጎ እየተተረጎመም ስለሆነ አንድ ሊባል ይገባል እንላለን በማለት መግለጫው አትቷል፡፡

# እነ ናትናኤል መኮንን ወደ ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ተዛወሩ

## -አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር ለብቻቸው ታሰሩ

በእነ አንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ተከሰው በቅርቡ የተፈረደባቸው የአንድነት ፓርቲ ብሔራዊ ም/ቤት አባል መምህር ናትናኤል መኮንን፣ የቀድሞ የፓርላማ አባል አቶ አንዱዓለም አያሌው የአንድነት ፓርቲ የባህር ዳር ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሻምበል የሺዋስ ይሁንዓለም፣ አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ/አበበ ቀስቶ/፣ አቶ ዮሐንስ ተረፈና አቶ ምትኩ ዳምጤ ከነበሩበት ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ከፍተኛ ጥበቃ ወዳለበት ቂሊንጦ ወደሚገኘው እስር ቤት መዛወራቸውን ቤተሰቦቻቸው ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡ ምንጮች እንደገለፁት በክስ መዝገብ ውሳኔ ከተሰጣቸው ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ቃሊቲ እስር ቤት ያሉት አቶ አንዱዓለም አራጌና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ናቸው ተብሏል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በእነ ኤልያስ ክፍሌ የክስ መዝገብ ተከሰው 17 ዓመት እስራትና 50 ሺህ ብር ቅጣት ተወስኖባቸው በቂልንጦ እስር ቤት የሚገኙት የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ /ኢብአፓ/ ፕሬዘዳንት አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር ከነበሩበት ዞን ሁለት እስር ቤት ወጥተው እዚያው ቂሊንጦ እስር ቤት በተለምዶ ግንቦት ሰባት በሚባል ግቢ ለብቻቸው ታስረው እንደሚገኙ ታማኝ ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡

የውስጥ አዋቂዎች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት ‹‹እዚህ ማረሚያ ቤት ውስጥ እስረኞችን ታሳድማለህ፤ እስላሞች እንዲበጠብጡ የምታስደርገው አንተነህ›› ተብለው ቢሮ ተጠርተው የተጠየቁ ሲሆን እሳቸው ‹‹እኔ ማንንም ለአድማ አልቀሰቀስኩም፤ እዚህ በእናንተ ጥበቃ ስር ማረሚያ ቤት ውስጥ ተቀምጬ ሙስሊሞችን የማደራጅበትና እንዲረብሹ የምቀሰቅስበት አቅምም መንገድም የለኝም፡፡ እኔን ማጉላላት የምትፈልጉበት ጉዳይ ካለ የምትፈልጉትን ማድረግ ትችላላችሁ ብለው›› መልስ ሰጥተዋቸዋል፡፡ ከዚያም ከነበሩበት እስር ቤት አውጥተው ልዩ እስር ቤት ውስጥ ለብቻቸው እንዲታሰሩ ተደርገዋል፡፡›› ብለዋል፡፡

ስለ ጉዳዩ የአቶ ዘሪሁን ቤተሰብ ሐሳብ እንዲሰጡን ብንጠይቅ ለብቻው መታሰራቸውን አምነው በሌላ ጉዳይ ምንም ዓይነት አስተያየት መስጠት እንዳማይፈልጉ ገልፀዋል፡፡

# የአርበኞች ማህበር አባላት ዛሬም በአቤቱታ ላይ ናቸው

የኢትዮጵያ ጥንታዊት አርበኞች ማህበር አባላት ዛሬም ‹‹የፍትህ ያለህ›› እያሉ መሆኑን ለዝግጅት ክፍሎችን አስታወቁ፡፡ በዕድሜ የገፉ የማህበሩ አባላት በተደጋጋሚ ዝግጅት ክፍላችን በመገኘት እንደገለጹት ‹‹ከአራት የማይበልጡ ግለሰቦች ተቧድነው በአርበኛው ስም የግል ጥቅማቸውን እያሳደዱና ወንጀል እየፈፀሙ ናቸው፡፡›› በማለት ያማርራሉ፡፡

አባት አርበኞቹ እንደሚሉት ‹‹የማህበሩ ፕሬዝዳንት የማህበሩን ህገ ደንብ ጨፍልቀው አመራሩንም በትነው እንደግል የንግድ ኩባኒያቸው ቆጥረውት የፈለጉትን እየሾሙ የማይፈልጉትን በማህበሩ ቅጥር ግቢም እንዳይገኝ እያስከለከሉ ነው፡፡ እየፈፀሙ ያሉትን ሙስናና ወንጀል በማስረጃ አስደግፈን ለዐቃቤ ህግና ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያሳወቅን ቢሆንም ፍትህ በመዘግየቱ ካፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ዓይነት እየተፈፀመ ያለው የወንጀል ድርጊት ተጠናክሮ ቀጥሎአል፡፡ ፕሬዝዳንቱም ሆኑ በዙሪያቸው የተሰባሰቡ ሦስት ግለሰቦች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ

ወደ ገፅ 13 ይዞራል....

# የሰው እጅ ጣቶች ...

ከ ገፅ 3 የዞረ....

ቢወረውርም ተተኪዎቹ አሸን ናቸው፡፡ የግብፁ ፈርኦን እስራኤላውያንን ለዘላለም በባርነት ለመግዛት ሲል የሚወለዱት የአይሁድ ልጆች ወንዶች ከሆኑ እንዲገደሉ ለአዋላጆች ያስተላለፈው ትዕዛዝ ለጊዜው የተሳካ ቢመስልም እ/ር በመጨረሻ ሙሴን ከሞት ታድጎት እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ነፃ እንዲያወጣ ሾመው፡፡ ዛሬም ክንዱ የማይዝለው የኢትዮጵያ አምላክ በርካታ ሙሴዎችን ያስነሳል፡፡ "መካሪ የሌለው ንጉስ . . ." እንዲሉ ኢህአዴግ ህልም ፈቺ ነብያትን፣ ሐቅ ነጋሪ ነብያትን፣ መንገድ ጠራጊ ነብያትን፣ የአይን ጉድፍ ተመልካች ነብያትን፣ ትንቢት ተናጋሪ ነቢያትን፣ እንደ ዘመነ ብሉይ ኪዳን ፈርኦኖች እያሳደደ ይገኛል፡፡ ብዙዎችን በፍርሃት ልባቸውን እያራደ ከአገር እንዲሰደዱ ሲያድርግ እንደ ሙሴ በፈርኦን ቤት ከሚገኝ ክብር ይልቅ ከእስራኤል ህዝብ ጋር መከራን ለመቀበል የመረጡትን ደግሞ ነብዩ ዳንኤል አንበሳ ጉድጓድ እንደተወረወረ ቃሊቲ እስር ቤት እየወረወራቸው ይገኛል፡፡ አንድ ቀን ግን የአንበሳዎቹን አፍ የዘጋው የዳንኤል አምላክ የቃሊቲን አፍ ይዘጋል፡፡ ነቢዩ ዳንኤል በተጣለበት የአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ ለሜደንና ፋርስ ህግ አሳልፈው የሰጡት መሳፍንትና አለቆች የአንበሳ ሲሳይ እንደሆኑት ሁሉ "በሰፈሩት ቁና . . ." መባሉ አይቀሬ ነው፡፡

የህወሓት /ኢህአዴግ መሪዎች ማስተዋላቸው ተጋርዶ እንጂ ቢያውቁበት ኖሮ ጋዜጠኞችና የሰላማዊ ትግል አቀንቃኝ ፖለቲከኞች ህልም ፈቺዎቹ ናቸው፡፡ እንከኑን የሚያሳዩት መስታወቶቹ ናቸው፡፡ በማንኛውም መስፈርት ስጋ ለባሽ ሁሉ ፍፁም አይደለም፤ "ሰው ምን ቢማር ቄስ እንጂ መልአክ አይሆንም" እንዲሉ፡፡ ይህ ሀቅ ነው ከመሪዎቻችን የተሰወረው፡፡ "ይሄ ተግባራችሁ ከህዝብ ጋር ያጋጫችኂል፡፡ በዚህ አካሄዳችሁ ህዝብ ይጣላችኂል፡፡ ይሄን ብታደርጉ ነው ለእናንተም በስልጣን ላይ መቆየትም ሆነ ለአገር እድገት የሚበጀው . . ." የሚሉ የዘመኑን ነቢያት ማሳደድ መሪዎቻችንን ከማይወጡት አጣብቂኝ ውስጥ ከቷቸዋል፡፡ ይሄ ልበ ደንዳናነት ለጥንቶቹ ናቡከደነፆርና ብልጣሶርም ሆነ በዘመናችን ለነገሱት ለግብፁ ሙባረክና ለሊቢያው ጋዳፊም አልበጃቸውም፡፡ ሁሉም የገጠማቸው አንድ ተራ ሰው ሊገጥመው ከሚችለው ውርደትና ቅሌት በእጥፍ የከፋ ነበር፡፡ ይህ እንዳይደርስባችሁ በሩቁ ለመከላከል ከሆነ ንፁሐን ዜጎችን እያነቃችሁ የምታስሩት ተሳስታችኂል፡፡ የምትሰፈሩበትን የግፍ ፅዋ ነው እያጠራቀማችሁ ያላችሁት፡፡ አንድ ቀን ምሬቱ ተጠራቅሞ ሲገነፍል የነሱ እጣ እንደሚጠብቃችሁ ልብ ልትሉ ይገባችኂል፡፡

ዛሬ በመሪዎቻችን ዙሪያ የተኮለኮሉት አማካሪዎች የሐሰተኛ ነብያትን ተግባር እየፈፀሙ ያሉ ይመስለኛል፡፡ የንጉሥ አርጤምስ አማካሪ የነበረው ሓማ አይሁድን ለማጥፋትና መርዶክዮስን ለመስቀል ንጉሱን እስከማሳመን ደርሶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እ/ር ታሪኩን ቀይሮ ለመርኮክዮስ ባዘጋጀው መስቀል ላይ አማካሪው ሐማ ተሰቀለ፡፡ ሀሰትን እውነት አስመስለው ለነገስታት ሲናገሩ የነበሩ ሀሰተኛ ነብያት ፍፃሜያቸው ውርደት እንደነበር መጽሀፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ ራሳቸው ስተው እ/ር የቀባቸውን መሪዎችም አስተው ፈጣሪን ሲበድሉ ይታያል፡፡ ሕዝቡም በእ/ር ላይ እንዲያጉረመርም አነሳስተዋል፡፡ እግዚአብሔርም እኩይ ምግባራቸውን እየተመለከተ አይቀጡ ቅጣት ቀጥቷቸዋል፡፡ የናንተም እጣ እንዲህ እንዳይሆንባችሁ የሚባለው ያጣን ሕዝብ አትበድሉት፤ አታስቃዩት፡፡

ሕዝብ በረሀብ አለንጋ እየተገረፈና ኑሮው የማይወጣ አቀበት ሆኖበት ሳለ "ጠግቦ እየበላ ነው"፤ ዜጎች የተቃውሞ ድምጽ እያሰሙ "ህዝብ ደግፎናል" የሚሉ አማካሪዎች ገለል ሊደረጉ ይገባል፡፡ ተግባራቸው ከአጥፍቶ ጠፊዎች አይተናነስምና፡፡ ይዘዋችሁ እንዳይጠፉ አስቡበት፡፡ ለደርግም አልበጁትምና፡፡

ዛሬም የሰው እጅ ጣቶች በአራት ኪሎው የንጉስ ቤት ላይ "ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ" ሲሉ እየፃፉ ነው፡፡ ሕልምን ለመተርጐም አዕምሮዎቻቸው አልዛሉም፣ ብዕራቸውም አልዶለደመም፡፡ ጣታቸው በንጉስ ቤት ግድግዳ ላይ ባሳረፉ ቁጥር ቃሊቲ ቢወረወሩም የኢትዮጵያ አምላክ እሳት ጎርሰው እሳት የሚተፉ ጽድቅን የሚያውቁ ኃጢአትን የሚኮንኑ፣ ለውስብስብ ችግሮች መላን የሚዘይዱ፣ ጨለማን ከብርሃን የሚለዩ ነብያትን በእጥፍ ያስነሳል፣ የትውልድ ጅረት ከመፍሰስ አይገደብምና፡፡

**የሳምንት ሰው ይበለን**

# ክቡር ሚኒስትር ...

ከ ገፅ 7 የዞረ....

ስጡና ልሰራቸው›› ይላል፡፡

ሰበብ ተፈልጉላቸው የሚታሰሩትን ቢያንስ ፍ/ቤት የመቅረብ እድሉ ይኖራቸዋል፡፡ አድራሻቸው ሊታወቅ ስለሚችል ቤተሰብ እና ዘመድ ሊጠይቃቸው ይችላል፡፡ ከዚህ የከፋው በአጋጣሚ በፌደራል ፖሊስ ተይዘው ከሥራ ቦታ ወይም ከመንገድ ላይ ታፍሰው የሚታሰሩት ሰዎች ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤት አይቀርቡ፣ በውሸት እንኳ የተፈበረከ ፋይል የላቸው፣ ቤተሰብ እና ዘመድ አይጠይቃቸው፣ አድራሻቸው አይታወቅ፡፡ በማያውቁት ምክንያት እድሜያቸውን በሥር ይገፋሉ፡፡ ይባስ ብሎም ወደ ቤተሰቦቻቸው ሳይመለሱ በሥር እንዳሉ ሊያሸልቡ ይችላሉ፡፡

ሌላው በአይሲሲ የተገለፀው ወንጀል አስገድዶ ከቀየ ማፈናቀል ነው፡፡ ይህ ሰውን አስገድዶ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር በኢትዮጵያ መንግስት የተለመደ ነው፡፡ እንዲያውም ወንጀል መሆኑንም የሚያውቁ አይመስለኝም፡፡ በዋናነት በጋምቤላ ክልል ኗሪዎች ላይ በኢንቨስትመንት ስም እየተፈፀመ ያለው ለዚህ ጥሩ ማሣያ ነው፡፡ በሌሎች ቦታዎችም ተመሳሳይ ነው፡፡ ተራውን ሕዝብ ይቅር እና ለአመታት የኖሩ ገደማትን ከማፍረስ እና መነኮሳቱን ከማባረርም ኢህአዴግ አላፈረም፡፡ በነገራችን ላይ ስለ ኢንቨስትመንት ስነሳ ቅድም ባርነት ላይ እገልፀዋለሁ ብዬ የዘነጋሁትን አስታወሰኝ፡፡ ኢህአዴግ ሁሌም ኢንቨስተሮችን ሲጋብዝ ከተመቻቸ ፖሊሲ ይልቅ ርካሽ የሰው ጉልበት መኖሩን ነው የሚገልፅላቸው፡፡ በእርግጥ ይህ እውነት ነው፡፡ አለም ያወቀው ሐቅ፡፡ ይህ ግን ሌላ መልክት አለው፡፡ እርካሽ የሰው ጉልበት መኖሩ ምን ያክል ህዝቡ የከፋ ድህነት ውስጥ እንዳለ አመላካች ነው፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ የሰው ጉልበት ርካሽ ከሆነ ዜጐች ለባርነት ለመደረግ ምቹ መንገድ ይፈጥራል፡፡ የዜጐችን ክብር እና ስብዕናንም ማቆሸሽ ነው፡፡

ለዚህ ሁሉ አይሲሲ ለዘረዘራቸው እና ሌሎች ወንጀሎች በሀገሪቱ ውስጥ እንዲፈፀሙ የተለያዩ የወንጀሉ ተባባሪ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ቢኖሩም የድርጊቱ ዋነኛ ተዋናይ ግን ጠ/ሚ መለስ ናቸው፡፡

ስለዚህ ከመሞታቸው በፊት ቶሎ ወደ አይሲሲ ቀርበው ቀኖና ተቀብለው ንስሀ ሊገቡ ይገባል፡፡ ሌሎች ተባባሪ ግለሰቦችም እንደየስራቸው ለንስሀ መቅረብ አለባቸው፡፡ በነገራችን ላይ ሰዎች ነን እና እንደ ሰው ማለት ያለብን እ/ር ይማራቸው ነው፡፡ እኔም ከህመምዎ እንዲፈወሱ ምኞቴ ነው፡፡ ከምንም በላይ ግን በአይሲሲ ቀሳውስት ፊት ቀርበው ቀኖና ተሰጥቶዎት ንስሀ ሲገቡ ማየት የዘወትር ምኞቴ ነው፡፡ ከተሰማም ፀሎቴ ነው፡፡

ዜና

# ዶ/ር ነጋሶ መደበኛ ሥራቸውን ጀመሩ

**- ህክምናቸውን በመልካም ሁኔታ አጠናቀዋል - ተከታታይ ሕክምና መውሰድ ይጠበቅባቸዋል**

**- በግልም በቡድንም ተደራጅተው የረዷቸውን አመስግነዋል**

የቀድሞ የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት፣ የወቅቱ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር፣ የመድረክ ም/ሊቀ መንበርና የፋይናንስ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሰቢ የሆኑት ክቡር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ህክምናቸውን አጠናቀው መደበኛ ሥራቸውን መጀመራቸው ታውቋል::

ስለ ጤንነታቸውና ስለህክምናቸው ጉዳይ ያነጋገርናቸው ዶ/ር ነጋሶ በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ እንደገለጹት ‹‹ከዚህ በፊት ሁለቱንም እግሬን ያመኝ ነበር:: ከ50 ሜትር በላይ መጓዝ አልችልም:: ጥቂት ተጉዤ ቆም ብዬ እረፍት ካደረኩ በኋላ ነው ጉዞ የምጀምረው:: የበሽታውን ሁኔታና የደረሰብኝን ህመም ደረጃም አላወኩም:: በእርግጥ የደም ግፊትና የስኳር ህመም እንዳለብኝ አውቅ ነበር:: በሥራ ጉዳይ ጀርመን ሄጄ ህመሙ ይበልጥ ባሰብኝ ፤ሐኪም ቤት ሄጄ ስመረመር በሁለቱም እግሬ ጉልበቴ ላይ የደም ዝውውሩ መቆሙ ተረጋገጠ:: ከዚያም በአስቸኳይ ህክምና መውሰድ እንዳለብኝ ተነገረኝ::›› በማለት ገልጸዋል:

ዶ/ር ነጋሶ ስለ ህክምናቸውም ሲያብራሩ ‹የሁለቱም እግሮቼ የደም ስሮቼ ተዘጋግቶ ስለነበረ በዘመናዊ ህክምና በአንድ ስፔሻሊት ፕሮፌሰር መታከም ችያለሁ:: በአሁኑ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ጤንነት ይሰማኛል:: እግዚአብሔር ካለና ዕድለኛ ከሆንኩ እስከ ዕድሜ ዘመኔ በጤንነት እኖራለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::›› በማለት ምኞታቸውን ገልፀዋል::

ስለ ህክምና ወጪያቸው ሁኔታ እንዲያስረዱን የጠየቅናቸው ዶ/ር ነጋሶ ‹‹ህክምናውን በአስቸኳይ ካልወሰድኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ የከፋ ችግር እንደሚገጥመኝ ተነገረኝ ፤ወዲያውኑ ለህክምናው ብቻ 8ሺህ ዩሮ ተጠየኩኝ:: ተበድሬ በመክፈል ህክምናውን አደረኩኝ:: በግለሰብ ደረጃ በጀርመንና በአንዳንድ ቦታ ያሉ ሰዎች ረድተውኛል:: በተደራጀ መልኩ ደግሞ በእንግሊዝ፣ በስዊዲን፣ በኖርዌና በዴንማርክ ያሉ የኢትዮጵያዊያን ኮሚኒቲ ረድተውኛል:: ከአገር ውስጥም እርዳታ ያደረጉልኝ እንዳሉ ተረድቼአለሁ:: እስከአሁን የተሰበሰበው ህክምናዬን ሸፍኗል:: ሆኖም ግን እንድወስድ የታሰበው የደም ማቅለጫ መድኃኒት ዋጋው ውድ ነው:: አሁን ለሦስት ወር የምወስደው መድኃኒት 2ሺህ ዩሮ ነው የገዛሁት፤ ይህ ከህክምናው ወጪ ተጨማሪ ነው ብለዋል:: አያይዘውም በየ6 ወሩና በዓመት አንድ ጊዜ ቼክ መድረግ እንደሚያስፈልገኝ ሐኪም አዟል ፤ለመድኃኒትና ለምርመራ የተወሰነ ገንዘብ ያስፈልገኛል:: በምግብና በግል ማድረግ ያለብኝን ጥንቃቄ የሐኪም ምክር ተሰጥቶኛል::›› በማለት ገልፀዋል::

በመጨረሻም ስለተደረገላቸው እርዳታ ሲገልጽ ‹‹በአጭር ጊዜ ውስጥ ርብርብ አድርገው ለረዱኝ ኢትዮጵያውያን ወገኞቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ:: ያሰባሰቡትን ገንዘብ በአድራሻዬ እንደሚልኩልኝ ቃል ለገቡልኝና ለላኩልኝ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቅርቡልኝ::›› በማለት ምስጋናቸውን አቅርበዋል::

# በለገጣፎ ሙስና ተንሰራፍቷል

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ ‹‹ሙስና በከፍተኛ ደረጃ ተንሰራፍቷል፣ ነዋሪዎች አገልግሎት ማግኘት አልቻልንም::›› ሲሉ አንዳንድ የከተማው ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ:: ነዋሪዎቹ እንደሚሉት ‹‹የከተማው መስተዳደር ግልጽነት የጎደለው የቦታ ሽንሽናና የካርታ ዕደላ እያደረገ ሲሆን፤የአካባቢው ተወላጆች ደግሞ ‹‹ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ጀምሮ ይዘው የቆዩትን ቦታ ህጋዊ ካርታ ማግኘት አልተቻልም::›› በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል::

የለገጣፎ ተወላጆች ነን የሚሉ ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት ‹‹ለገጣፎ በሐምሌ ወር 1998 ዓ.ም ከተማ መስተዳደር ሆነች፣ ከጥርና የካቲት 98 ዓ.ም ጀምሮ ካርታ መስጠት ተጀመረ፤ ስለካርታ አወሳሰድ ግልጽ የሆነ አሰራር የለም:: ሆኖም ግን አንዳንድ ሰዎች ካርታ ማግኘታቸውን አረጋግጠናል:: ከአርሶ አደሩ ላይ መሬቱ ሲነጠቅ ለአካባቢው ተወላጅ ወጣቶች ለመኖሪያ የሚሆን ለእያንዳንዱ 140 ካሬሜትር ይሰጣል ተብሎ 700 ወጣቶች ቢመዘገቡም ለ300 ወጣቶች ብቻ ተሰጥቶ ለሌላው እስከአሁን አልተሰጠም:: ነዋሪዎች የገዛ መሬታቸውን ካርታ ማግኘት እየተሳናቸው ሌሎች ግን የሚያገኙበት ሁኔታ ግልጽ አይደለም›› ብለዋል::

እነዚህ ነዋሪዎች እንደሚሉት ‹‹የከተማው መስተዳድር የከተማውን ነዋሪዎች ስብሰባ ሲጠራ ሁሉንም ነዋሪዎች አያካትቱም:: በከተማው ውስጥ ያለው የአቡነ ኪሮስ ቤተክርስቲን አካባቢ ህጋዊ ካርታ ያለው ቢሆንም የቦታው ይዞታ ግልጽነት የጎደለውና ላልታወቀ ሙስና የተመቻቸ ይመስላል:: በአሁኑ ጊዜ ካርታ መስጠት ቆሟል ቢባልም ባልታወቀ መንገድ እየተሰጠ ነው:: በምን አግባብ ተሰጠ? ብለን ስንጠይቅ የቆየ ካርታ ታድሶ ነው ይሉናል:: ምናልባትም ቀደም ሲል ካርታው ሲዘጋጅ በብዛት ተዘጋጅቶ ተቀምጦ አሁን በሙስና እየተቸበቸበ ነው የሚል ጥርጣሬ አለን::›› በማለት ስጋታቸውን ገልፀዋል::

እንደነዋሪዎቹ ገለፃ ከሆነ ‹‹በአንድ ወቅት የከተማው ነዋሪዎች ብዛት 17,236 ነው ተብሎ ተነግሮን ነበር:: የከተማው ነዋሪ ቁጥር ግን ይህንን ያህል አይደለም:: የከተማው ከንቲባ በአካባቢው ነዋሪ የተመረጡ ሳይሆኑ ከሰባት ዓመታት በፊት ከሌላ ሥፍራ በምደባ የመጡ ናቸው:: ነዋሪዎች በአገልግሎትና በመልካም አስተዳደር እጦት በየጊዜው ብሶት እያቀረብን ከቦታቸው የማይነሱበት ምክንያት አይገባንም፣ ከኦሮሚያ ክልል እስከ 60 ቦታ የወሰዱ ባለሥልጣናት እንዳሉ ይነገራል:: ምናልባትም ለሚፈጠረው ሙስናና ለጠፋው የመልካም አስተዳደር እጦት የእነዚህ ባለሥልጣናት እጅ ስለሚኖሩበት ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል::›› ብለዋል:: በጉዳዩ ላይ የከተማው ከንቲባ አስተያየት እንዲሰጡበት በስልካቸው ላይ ብንደውልም ስልኩን ባለማንሳታቸው ሐሳባቸውን ማካተት አልቻልንም:: ጥረታችንንም በመቀጠል ፅሐፊያቸው ዘንድ ደውለን ስናነጋግር በሥራ ምክንያት ከቢሮ መውጣታቸውን ገልፀውልናል::

## ዜና ስፖርት

# የሴቶች የአፍሪካ ዋንጫ ድልድል ይፋ ሆነ

ወንድሙ ደግፍ
Wondim7878@yahoo.com

### - ሉሲዎች በሞት ምድብ ተደለደሉ

በመጪው ዓመት በኢኳቶሪያል ጊኒ ለሚደረገው የአፍሪካ ዋንጫ የግብፅ ብሔራዊ ቡድንና የታንዛንኒያው አቻቸውን አሸንፈው ወደ አፍሪካ ዋንጫ የተቀላቀሉት ሉሲዎች የሞት ምድብ ውስጥ ተደልድለዋል:: 8ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የሚካፈሉት ቡድኖች ብዛት ስምነት ሲሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሴቶች ቡድን በምድብ ሁለት ሲደለደሉ በዚሁ ምድብ የምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች የተደለደሉ ሲሆን ያለፈው የአፍሪካ ዋንጫ ፍፃሜ የደረሰችው ካሜሩን፣ በተደጋጋሚ ዋንጫ በማንሳት የምትታወቀው ናይጄሪያና ኮትዲቫር ሲደለደሉ በምድብ አንድ አዘጋጇ ኢኳቶሪያል ጊኒ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሴኔጋልና ዲሞክራቲክ ኮንጎ ተደልድለዋል:: በዕጣ ድልድሉም መሠረት ኢትዮጵያ (ሉሲዎች) የመጀመሪያ ጨዋታቸውን ከኮትዲቫር አቻቸው ሲያደርጉ የ7ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የፍፃሜ ጨዋታ ተፋላሚ የነበሩት ናይጄሪያና ካሜሮንን እንደሚያገናኝ ታውቋል:: ስለዚህ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ሉሲዎች ከተደለደሉበት ምድብ አንፃር ብዙ እንደሚጠበቅ ግምት ውስጥ በማስገባት ቅድመ ዝግጅቱ ጠንካራና የኢንተርናሽናል ጨዋታዎች እንዲያደርጉ የማመቻቸት ኃላፊነት ወይም ድርሻ አለበት በመሆኑም ፌዴሬሽኑ ከአሁኑ ደፋ ቀና ማለት ይኖርበታል ምክንያቱም ሳይሰራ ውጤት መጠበቅ የዋህነት ነው::

### ለንደን . . . 3 ቀናት ብቻ!

የ30ኛው ለንደን ኦሎምፒክ ዝግጅቱ ተጠናቆ እንግዶቿን ለመቀበል ሽርጉድ ማለት ከጀመረች ሰነባብታለች:: የኢትዮጵያ ኦሎምፒያድ ወደ ስፍራው ዛሬ ያቀናል:: በቤተመንግስት ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ የመልካም ምኞት ሽኝት የተደረገላቸው የኢትዮጵያ ኦሎምፒያድ ልዑካን ከአሁን ቀደም ከነበሩ ወይም ከተከናወኑ የኦሎምፒክ ውድድሮች የተሻለ ውጤት ይመዘገባል ተብሎ ይጠበቃል:: የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም ቀደም ብሎ ከሳወቃቸው ተወዳዳሪዎች በተጨማሪ በወንድ የዋና ተወዳዳሪ የተጨመረ ሲሆን በለንደን ኦሎምፒክም ለመጀመሪያ ጊዜ የምንወዳደርባቸው አትሌቲክስ ዘርፎች በርክተዋል:: በተያያዘ ዜና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ባዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም በአጠቃላይ 46 ሚሊዮን ብር ገቢ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል:: ይህም ገቢ ከዚህ ቀደም ከተደረጉት የገቢ ማሰባሰቢያዎች የላቀ ወይም ብልጫ እንዳለው ታውቋል:: መልካም ውጤት ለኢትዮጵያ ኦሎምፒያድ::

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

## የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮግራም

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል:: ለትግሉ ስኬት የርሶ ድጋፍ ወሳኝ ነዉ::

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ የራት ዝግጅት ፕሮግራም አዘጋጅቷል:: መግቢያ ባለ 1,000፣ 500ና 300 ብር መግቢያ ካርዶች ተዘጋጅተዋል::

በራት ፕሮግራሙ ላይ ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ:: የራት ግብዣዉ ሐምሌ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ይደረጋል:: የሆቴሉ ስም ሐምሌ 24 በሚወጣዉ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ ይገለፃል::

በውጪ አገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ሀገር ውስጥ በሚገኙ ወዳጅ ዘመዶቻችሁ በኩል ካርዱን መግዛት ትችላላችሁ::

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዛት በሚከተለዉ አድራሻ ይጠቀሙ:-

በቢ.ሮ ስልክ ቁጥር:- 01 18 40 08 11

ሞባይል 0911 61 84 34

ኢ-ሜይል:-

andinetfinance@yahoo.com

andinet@andinet.org

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ

የሂሳብ ቁጥር 510

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት ሁላችንም ካርዱን በመግዛት ድርሻችንን እንወጣ!